# የጋፋት ኢንዶዉመንት

# ስትራቴጂክ ዕቅድ

## (እ.ኤ.አ ከ2021 እስከ 2025)

እ.ኤ.አ. ማርች/ 2021

<u>ባህር ዳር</u>

## ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


I. አጠቃላይ እይታ ..... 1
1.1. መግቢያ ..... 1
1.2. የኢንዶዉመንቱ ዳራ ..... 3
1.3. የስትራጅክ እቅዱ አስፈላጊነት ..... 4
1.4. የስትራቴጂክ እቅዱ ዓላማ ..... 5
1.5. የስትራቴጅክ እቅዱ አዘገጃጀት ስልት ..... 5
ክፍል አንድ፡ የሁኔታ ትንተና ..... 6
1.1. እ.ኤ.አ ከ2016-2020 የስትራቴጅክ እቅድ አፈጻጸም እንደ መነሻ ..... 6
1.1.1. የአቅም ግንባታ ስራዎች/Institutional Capacity/ ..... 6
1.1.2. ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት ..... 8
1.1.3. የማህበራዊ ልማት ስራዎች ..... 9
1.1.4. የኩባንያዎች አፈጻጸም ..... 10
1.1.5. የተጠቃለለ ፋይናንስ አፈጻጸም ..... 13
1.1.6. የተጠቃለለ ፋይናንስ አፈጻጸም ..... 14
1.2. የዉስጣዊ ሁኔታ ትንተና ..... 17
1.2.1. ስትራቴጅ (Strategy) ..... 17
1.2.2. አደረጃጀት (Structure) ..... 18
1.2.3. አሰራር ስርዓት (System) ..... 19
1.2.4. የጋራ እሴቶች (Shared Values) ..... 19
1.2.5. የአመራር ሁኔታ (Leadership Style) ..... 20
1.2.6. የሰዉ ኃብት (Staff) ..... 21
1.2.7. ክህሎት እና አመለካከት (Skill & Attitude) ..... 21
1.2.8. አገልግሎት አሰጣጥ (Service Delivery) ..... 22
1.2.9. የፋይናንስ አስተዳደር ..... 23
1.3. የዉጫዊ ሁኔታ ትንተና ..... 25
1.3.1. ፖለቲካዊ ሁኔታ ..... 25
1.3.2. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ..... 26
1.3.3. ማህበራዊ ሁኔታ ..... 27
1.3.4. ቴክኖሎጅያዊ ሁኔታ ..... 28
1.3.5. አካባቢያዊ ሁኔታ ..... 29
1.3.6. ህጋዊ ሁኔታ ..... 30
1.4. የጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚና ስጋት ትንተና ማጠቃለያ ..... 31
1.5. የአስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ማጠቃያ ..... 41

1.6. የተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ትንተና ....... 43
1.6.1. የተገልጋዮች፣ ባለድርሻ እና አጋር አካላት ፍላጎት ትንተና ....... 44
1.6.2. የደንበኞች/ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት ትንተና ማጠቃለያ ....... 48
1.7. ከሁኔታ ትንተና ተጨምቀዉ የወጡ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች (Strategic Issues) ....... 51
1.8. ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች ....... 52
ክፍል ሁለት፡- የትኩረት መስኮችና ስትራቴጅያዊ ዕይታዎች ....... 53
2.1. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ፡ ....... 53
2.2. የስትራቴጅያዊ የትኩረት መስኮች መግለጫ ....... 53
2.2.1. ተቋማዊ ልህቀት፡- ....... 53
2.2.2. ኢንቨስትመንት ተኮር ሀብት ፈጠራ፡- ....... 54
2.2.3. የዳበረ ማህበራዊ ልማት ....... 54
2.3. የአፈጻጸም አመላካች ዕይታዎች (Perspectives) ....... 54
ክፍል ሦስት፡- ስትራቴጅያዊ ግቦች ....... 55
3.1. ስትራቴጅያዊ ግቦች ከእይታዎች አንጻር ....... 55
3.1.1. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ አንድ፡- ተቋማዊ ልህቀት፡- ....... 55
3.1.2. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ ሁለት፡- ኢንቨስትመንት ተኮር ሀብት ፈጠራ ....... 58
3.1.3. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ ሦስት፡- የዳበረ የማህበራዊ ልማት ....... 60
ክፍል አራት፡- ስትራቴጅያዊ ማፕ ....... 61
4.1. ስትራቴጅያዊ ማፕ ከየትኩረት መስክ አንፃር ....... 61
4.2. የተጠቃለሉ ስትራቴጅያዊ ግቦች፣ የግብ መግለጫና ማፕ ....... 65
ክፍል አምስት፡- የአፈፃፀም መለኪያዎች እና ዒላማዎች ....... 69
5.1. መለኪያዎች ....... 69
5.2. የመለኪያዎች መግለጫ ....... 72
5.3. ኢላማዎች ....... 81
ክፍል ስድስት፡ ስትራቴጅያዊ እርምጃዎች ....... 84
6.1. ስትራቴጅያዊ እርምጃዎችና የግቦች ትስስር ....... 85
6.2. የስትራቴጂያዊ እርምጃዎች መግለጫ ....... 86
ክፍል ሰባት፡- አውቶሚሽን ....... 88
ክፍል ስምንት፡- ስትራቴጅዉን በየደረጃዉ ማዉረድ (Cascading) ....... 89
ክፍል ዘጠኝ፡- የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ....... 91
9.1. የአፈጻፀም ክትትትል ....... 91
9.2. የግምገማ ስርዓት ....... 91
II. ልዩ ልዩ አባሪዎች ....... I
2.1. ወደ ተቋማት የወረደ ዕቅድ ....... I

# I. አጠቃላይ እይታ

## 1.1. መግቢያ

*በአገራችን ኢኮኖሚያዊ እድገትን በማረጋገጥና ማህበራዊ ልማትን በማፋጠን የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በመንግስት በኩል የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀርጸዉ ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም በአንደኛዉና በሁለተኛዉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በኢኮኖሚ፣ በመሰረተ ልማት ግንባታ፣ በማህበራዊ ልማት፣ በአቅም ግንባታና መልካም አስተዳደር፣ በዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እንዲሁም በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ዙሪያ የተለያዩ ግቦችን በማስቀመጥ ዉጤት ለማስመዘገብ ሲሰራ የቆየ ሲሆን ተጨባጭ ዉጤቶችም ተመዝግበዋል (ኢፌዲሪ ፕላን ኮሚሽን, 2012)፡፡*

*በተመሳሳይ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት ከአገሪቱ የተቀዱ ፖሊሲና ስትራቴጅዊችን መነሻ በማድረግ የክልሉን ሁለንተናዊ እድገት ለማፋጥን የሚያግዙ በማህበራዊና ኢኖሚያዊ ዘርፎች የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የልማት እቅዶችን በማውጣትና በመተግበር ተጨባጭ ውጤቶችን ማስመዝገቡን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለተመዘገበዉ ዉጤት የመንግሥት ድርሻ ከፍተኛውን ሚና ቢይዝም በአገር አቀፍ እና በክልሎች የሚገኙ የልማት አጋሮች አስተዋጽኦ ጭምር የተገኘ ነዉ፡፡*

*ከእነዚህ የልማት አጋሮች መካከል ጋፋት ኢንዶዉመንት አንዱ ሲሆን ባለፉት ዓመታት ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር በማገናዘብ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ልማት ዘርፍ በመሳተፍ በክልላችን እንዲሁም በአገራችንም የማይናቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ኢንዶዉመንቱ ከኢንቨስትመንት እና ከለጋሽ አካላት የሚያገኘውን ሀብት በክልሉ ውስጥ ክፍተት በሚታይባቸውና የግሉ ዘርፍ በበቂ ሁኔታ ባልደረሰባቸዉ የስራ መስኮች ላይ መዋዕለ ንዋዩን በማፍሰስ በክልሉ ውስጥ ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የቴክኖሎጅና የእዉቀት ሽግግር በማምጣት፣ የዉጭ ምንዛሬ በማመንጨት እንዲሁም የማህበራዊ ልማት አገልግሎትን በማስፋፋት የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን የበኩሉን ሚና እየተወጣ ይገኛል፡፡*

*የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት የተቋቋሙበትን ዓላማ በማሳካት ተመራጭ፣ ብቁና ተወዳዳሪ ለመሆን በርካታ ውስብስብና ፈታኝ ሁኔታዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተቋማቱ ከሚያጋጥሟቸው ፈተናዎች መካከል የተመሰረቱበትን ተልዕኮና የሚጠበቅባቸውን ውጤት ማወቅና ይህንኑ ለማሳካት ምን ስልት*

መንደፍና መተግበር አንዱ ሲሆን ይህን ለመሻገርም በጥልቅ የተተነተነ እና መነሻና መድረሻን በግልጽ የሚያሳይ እቅድ አቅዶ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም ኢንዶውመንቱ ይዞት የተነሳውን ተልዕኮ ማሳካት የሚያስችለውን የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ እቅድ መቅረፅ፣ መተግበርና መገምገም አስፈላጊ በመሆኑ የመጀመሪያውን የአምስት አመት ስትራቴጅክ እቅድ (እ.ኤ.አ ከ2016-2020) በሚዛናዊ የውጤት ተኮር ስርዓት (BSC) የአስተቃቀድ ስልት በማዘጋጀት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህም በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፎች ተስፋ ሰጭ ዉጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የተገኙ ዉጤቶችን ይበልጥ አጠናክሮ ለማስቀጠል በመጀመሪያው የስትራቴጅክ እቅድ ዘመን የተተገበሩ ሥራዎችና ያስገኟቸዉን ዉጤቶች እንዲሁም በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ፈታኝ ሁኔታዎችን በመገምገምና የተለዩ እጥረቶችን ግምት ውሰጥ ባስገባ መልኩ የሁለተኛውን የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ ዕቅድ (እ.ኤ.አ ከ2021-2025) በBSC አስተቃቀድ ስልት እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የስትራቴጅክ እቅድ ሰነዱ በዘጠኝ ክፍሎች የተደራጀ ነው፡፡ ክፍል አንድ የሁኔታዎች ትንተና፣ ክፍል ሁለት ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስኮችና እይታዎች፣ ክፍል ሦስት ስትራቴጅያዊ ግቦች፣ ክፍል አራት ስትራቴጅያዊ ማፕ፣ ክፍል አምስት መለኪያዎችና ዒላማዎች፣ ክፍል ስድስት ስትራቴጅያዊ እርምጃዎች፣ ክፍል ሰባት የሚዛናዊ ውጤት ተኮር እቅድ ስርዓትን የመረጃ አያያዝና ፍሰት ስርዓት(Automation)፣ ክፍል ስምንት ስትራቴጅውን በየደረጃው ማውረድና ክፍል ዘጠኝ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማን እንዲይዝ ተደረጎ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. የኢንዶዉመንቱ ዳራ

ጋፋት ኢንዶውመንት በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሄር ህግ አዋጅ ቁጥር 165/1952 ዓ.ም አንቀጽ 483 እስከ 515 መሠረት ጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም በክልሉ ፍትህ ቢሮ ተመዝግቦና ህጋዊ እውቅና አግኝቶ ሲንቀሳቀስ የቆየና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ማህበራት መመዝገቢያና ማስተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር 194/2004 አንቀጽ 63(1) መሠረት የተመዘገበ መንግስታዊ ያልሆነ ዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅት ነው፡፡

ኢንዶዉመንቱ በኢትዮጵያ የቴክኖሎጅና የስልጣኔ ታሪክ ዉስጥ ልዩ ቦታ በሚሰጠዉና ሁሌም በትዉልዶች ዘንድ ሲታወስ በሚኖረዉና የዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስን ራዕይ በሚያንጸባርቀው በወቅቱ በሀገር ውስጥ የአዲስ የቴክኖሎጂ ጅምር የሆነዉን የሴባስቶፖል መድፍን ባሰሩበት ጋፋት በሚባለዉ ልዩ ቦታ የረጅም ጊዜ ራዕይ አንግቦና ስያሜዉን አግኝቶ የተቋቋመ የልማት ድርጅት ነዉ፡፡

ኢንዶዉመንቱን ከማቋቋም አኳያ ዋናዉንና ግንባር ቀደሙን ሚና የተጫወተዉ የአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት(አመልድ) ነዉ፡፡ አመልድ የአለም አቀፍ ተሞክሮዎችን መነሻ በማድረግ ጋፋት ኢንዶዉመንትን ለማቋቋም ሲያስብ ዋነኛ መነሻዉ የአማራ ክልል ህዝብን ከድህነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ በሚደረገዉ ርብርብ ዉስጥ በዉጭ ኃይሎች የበጀት ድጋፍ ብቻ ጥገኛ ከመሆን ተላቆ በሂደት የልማት ፕሮግራሞቹን በሀገር ዉስጥ የፋይናንስ አቅም ለማስኬድ የሚያስችለዉን ዓላማ አንግቦ ነዉ፡፡

ኢንዶዉመንቱ ሲቋቋም ከኢንቨስትመንትም ሆነ ከለጋሽ አካላት የሚያገኘውን ሀብት በክልሉ ውስጥ ክፍተት በሚታይባቸውና የግሉ ዘርፍ በበቂ ሁኔታ ባላለማቸው ስትራቴጅክ ዘርፎች ላይ መዋዕለ ንዋዩን በማፍሰስ በክልሉ ውስጥ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ የሥራ እድል መፍጠርና በሂደትም የቴክኖሎጅ ሽግግር ማምጣት ዓላማው አድርጎ ነው፡፡ ኢንዶዉመንቱ እ.ኤ.አ በ2007 ሲቋቋም ከነበረዉ አንድ ኩባንያ (ጣና ፍሎራ) በመነሳት በሂደት ሶስት የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን (ጢስ እሳት ውሃ ስራዎች፣ መቅደላ ኮንስትራክሽን፣ ላሊበላ የጥናት፣ ዲዛይ፣ እና ቁጥጥር ስራዎች) በመያዝ ዛሬ ላይ የአራት ገቢ ማመንጨት የሚችሉ ኩባንያዎች ባለቤት መሆን ችሏል፡፡ በተመሳሳይ እ.ኤ.አ በ2007 11 የሰዉ ኃይል ብቻ የነበረዉ ዛሬ ላይ ላልተወሰነ ስራ/ቋሚ 1,019 እና ለተወሰነ ስራ/ኮንትራት 354 በድምሩ ለ1,373 ግለሰቦች የስራ እድል መፍጠር ችሏል፡፡ ከካፒታል አኳያም ኢንዶዉመንቱ ሲቋቋም ከነበረዉ ብር 197,373,320 በመነሳት አሁን ላይ ብር 261,271,076.40 ደርሷል፡፡ በአንድ መቶ ሽህ ብር የተጀመረዉ የማህበራዊ ልማት ስራዎችንም ለዘርፉ በዓመት እስከ አምስት ሚሊዮን ብር ማድረስ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ኢንዶውመንቱ ባለፉት አስር አመታት በኢንቨስትመንት፣በአቅም ግንባታ፣ገቢን በማሳደግና በማህበራዊ ልማት የትኩረት መስኮች ስር ባከናወናቸው ተግባራት ተጨባጭ ለውጦችንና ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ በዚህም በቂ ነው ባይባልም ለክልሉ ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ይህን ይበልጥ አጠናክሮ በቀጣዮቹ አምስት አመታት የሚመራበትን ሁለተኛውን ስትራቴጂክ እቅድ አቅዷል፡፡

### 1.3. የስትራጅክ እቅዱ አስፈላጊነት

ከዚህ ቀደም በተዘጋጀውና ስራ ላይ በዋለው የኢንዶውመንቱ ስትራቴጅክ እቅድ የተቀመጡት ግቦች ኢንዶውመንቱን ዘላቂና አስተማማኝ የበጎ አድርጎትና የልማት ተቋም ከማድረግ አኳያ ተቀርጾ ሲተገብር የቆየና የተወሰነ ርቀት መራመድ የቻሉ ቢሆንም የሚጠበቅበትን ክልላዊ ሚና በብቃት እንዲወጣ በማድረግ የበለጠ አጠናክሮ መስራት የሚጠበቅበት በመሆኑ፤

ጋፋት ኢንደዉመንትም ይሁን መሰል ተቋማት በንግድና በአገልግሎት አሰጣጥ እንቅስቃሴ ተወዳዳሪና አሸናፊ ሆነው የሚዘልቁት በቁሳዊው ሀብት ላይ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስና በአግባቡ በማስተዳደር ብቻ ሳይሆን በይበልጥ በአእምሯዊ ሀብት ላይ ሰፊ ስራ በመስራት በዘላቂነት ሀብት በመፍጠር በመሆኑ ይህን ሊያስተሳስር የሚያስችል ስልት ቀይሶ መንቀሳቀስ ስለሚገባ፣ ከሀገራዊና ክልላዊ መሪ እቅድ ጋር የሚጣጣም ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት ወቅታዊ አስተሳሰብና ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ግብና ኢላማዎችን በመቅረጽ ኢንዶዉመንቱ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት ለማስቻል ነዉ፡፡

በመሆኑም ይህን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ጋፋት እንደ አንድ የክልሉ የልማት አቅም በክልሉ ልማት ላይ ሊኖረው የሚችለውንና የሚገባውን ድርሻ የሚመልስ የአምስት ዓመት ስትራቴጅያዊ እቅድ በባላንስድ ስኮርካርድ (BSC) ስልት ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

## 1.4. የስትራቴጂክ እቅዱ ዓላማ

የስትራቴጅክ እቅዱ ጥቅል ዓላማ ኢንዶዉመንቱ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች የሚያከናዉናቸዉን ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች እና የሚያሳካቸዉን ዉጤቶች በማስቀመጥና ተግባራዊ በማድረግ ተልዕኮና ራዕይ በብቃት ለማሳካት ማስቻል ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አካቷል፡፡

- በኢንዶውመንቱ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴቶች እና ዓላማዎች ላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻና አጋር አካላት ጋር የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ፤
- የኢንዶውመንቱን ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የረጅም ጊዜ ግቦችና ዒላማዎች በመለየት የተሻለ እና ቀጣይነት ያለው ውጤት ለማስመዝገብ፣
- በኢንዶውመንቱ የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች፣ በስራ አመራር ቦርድና በጽ/ቤቱ መካከል ስትራቴጂያዊ ትስስርን በመፍጠር ቅንጅታዊ አሰራር እንዲፈጠር ለማስቻል፣
- በየደረጃው የሚገኘውን የአመራርና ፈፃሚ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የእለት ተእለት ተግባራት ስትራቴጅው ጋር በማስተሳሰር ለተቋማዊ ስኬት የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ ለማሳደግ፤
- ቀጣይነት ያለው ውጤታማ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ለማድረግ፤

## 1.5. የስትራቴጅክ እቅዱ አዘገጃጀት ስልት

ስትራቴጅክ እቅዱ የሚከተሉትን ዋና ዋና ሂደቶች ተከትሎ ተዘጋጅቷል፡፡ እቅዱ በጋፋት ኢንዶዉመንት ደረጃ የተዘጋጀ ሲሆን ከቅድመ ዝግጅት አኳያ ሰነዱን ለማዘጋጀት ከኢንዶዉመንቱና ከኩባንያዎች የተወጣጣ የእቅድ ዝግጅት ቡድን በማዋቀርና አስፈላጊዉን የስራ አቅጣጫ በመያዝ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

ስትራቴጅክ እቅዱን ለማዘጋጀት ይረዳሉ ተብለው የታመነባቸው ሰነዶችን መዳሰስና መገምገም ተችሏል፡፡ በዚህም የኢንዶዉመንቱና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎችን ያለፉት ዓመታት እቅድ አፈጻጸም፣ የሌሎች መሰል ተቋማት ተሞክሮ እንዲሁም የመንግስት የልማት እቅዶችንና አቅጣጫዎችን በመፈተሸ እንደመነሻ ሀሳብ ተወስዷል፡፡ በዝግጅት ሂደት ቡድኑ የደረሰበትን ደረጃ ለበላይ አመራሩ በማቅረብ፣ በማስተቸትና ግብዓት በማሰባሰብ እንዲካተትና እቅዱ እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ የስትራቴጅክ እቅዱ የBSC አስተቃቀድ ስልትን የተከተለ ሲሆን የሁኔታ ትንተና፣ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች ልየታ፣ የኢንዶዉመንቱን ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች እንዲሁም የትኩረት አቅጣጫዎችንና ስትራቴጅያዊ ግቦችን፣ መለኪያዎችና ኢላማዎችን በመለየት እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ስርዓትን በማስቀመጥ ተዘጋጅቷል፡

# ክፍል አንድ፡ የሁኔታ ትንተና

## 1.1. እ.ኤ.አ ከ2016-2020 የስትራቴጅክ እቅድ አፈጻጸም እንደ መነሻ

### 1.1.1. የአቅም ግንባታ ስራዎች/Institutional Capacity/

ጋፋት ኢንዶዉመንት እ.ኤ.አ ከ2016 እስከ 2020 ድረስ የሚቆይ የ5 ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በስትራቴጅክ እቅዱ ላይ የማስፈፀም አቅም ግንባታ የመጀመሪያዉና ወሳኙ የእቅዱ የትኩረት መስክ ተደርጎ ተሰርቶበታል፡፡ በመሆኑም የተቋማትን ትርፋማነትና ተወዳዳሪነት ለማጎልበት በሚከተሉት አምስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ እነዚህም በሰዉ ኃብት ልማት፣ ስልጠና ምርምር፣ ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም፣ የአሰራር ስርዓት ማሻሻያዎች እንዲሁም ስነ-ምግባርና መልካም አስተዳደር ናቸዉ፡፡

በዚህም እንደ ኢንዶዉመንት በተቋቋሙት የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች የእዉቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ክፍተቶችን መሰረት ያደረጉ የአጭርና ረጅም ጊዜ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከረጅም ጊዜ ስልጠና አንጻር በቁጥር 87 ታቅዶ ወንድ 13፣ ሴት 6 በድምሩ 19(21.84%) ለሚሆኑ አመራሮችና ሠራተኞች በተቀመጠዉ መመሪያ መሰረት የረጅም ጊዜ ትምህርት እንዲገኙና አቅማቸዉን እንዲያሳድጉ ተደርጓል፡፡ ከአጭር ጊዜ ስልጠና አኳያም በቁጥር 9,360 በድግግሞሽ ለማሳካት ታቅዶ 2,249(24.03%) ለሚሆኑ ሰራተኞች የተለያዩ ስልጠናዎችን ለተከታታይ ዓመታት መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጣና ፍሎራ የሥራ ላይ የተግባር ስልጠና(on job training) በተከታታይ በመስጠት የሰራተኛዉን ክህሎት በማሳደግ አፈጻጸማቸዉን የማሻሻል ስራ ተሰርቷል፡፡ በተመሳሳይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሀገር ዉስጥ እና በዉጭ ሀገራት 87 እና 35 ታቅዶ በሀገር ዉስጥ 15(17.24%) እና በዉጭ ሀገር 12(34.29%) የልምድ ልዉዉጥ በማካሄድና ተሞክሮዎችን በመዉሰድ የሰዉ ኃብቱን የመፈፀም አቅም ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡

ከሰዉ ኃብት አቅም ግንባታ ጎን ለጎን ትኩረት ተሰጥቶት ባለፉት ዓመታት ሲተገበር የቆየዉ አሰራርን የመዘርጋትና የማዘመን ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ከጣና ፍሎራ አኳያ ምረታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የጉልበትና የግብዓት አጠቃቀም፣ የመሬት ምርታማነትና የወጪ አስተዳደር የሚያሻሽሉ ስታንዳርዶች ሥራ ላይ እንዲዉሉ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በተመሳሳይ በኮንስትራክሽን ኩባንያዎችም በጉድጓድ ቁፋሮ ዘርፍ የፈረቃ አሰራር፣ የትርፍ ሰዓት ሥራ፣ የሎጅስቲክስ አቅርቦትና አስተዳደር፣ የቁፋሮ ሳይቶች ቅድመ ዝግጅትና የሪግ ስምሪትና ጥገና፣ የግብዓትና የሰዉ ጉልበት አጠቃቀም ስታንዳርዶች ዝርጋታ፣ በፕሮጀክቶች የቀን ተቀን ትርፍና ኪሳራ ስሌት ስታንዳርድ፣ የማሽነሪና ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት እንዲሁም የነዳጅ አጠቃቀም ስታንዳርድ አሰራሮች ላይ እንዲዉሉ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም በኢንዶውመንት ደረጃ የተመረጡ የለውጥ መሳሪያዎችን ሥራ ላይ ለማዋል የካይዘን ፍልስፍናንና የBSC እንዲሁም ከአሰራር አኳያ የዓለም አቀፍ ፋይናንስ ሪፖርት ስታንዳርድ/IFRS/ አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ ለዉጥ ለማምጣት እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ከካይዘን አንጻር የከልቡ አደረጃጀቶችን በመጠቀም እንደ ተቋማቱ የስራ ባህሪ በሳምንት ደረጃ ሠራተኛዉ አፈፃፀሙን የሚገመግምበትና በሂደቱም አመራሩና ሠራተኛዉ እርስ በእራሱ የአመለካከትና የክህሎት ሽግግር የሚያካሂድበትና ብክነትን የሚከላከልበት ስርዓት በመሆን እንደ ማሳለጫ እንዲያገለግል ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ የዓለም አቀፍ ፋይናንስ ሪፖርት ስታንዳርድ /IFRS/ አሰራር ዉጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር ለሁለት ዓመታት የተደረገዉ እንቅስቃሴ አዝጋሚ ቢሆንም አሁን ላይ የመጀመሪያዉን ደረጃ አልፎ የማጠናቀቂያ ስራዎችን ከአማካሪ ጋር በመሆን ዳር ለማድረስ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም መረጃን ወጥነት ባለዉ መልኩ እስከ ፕሮጀክት ድረስ በተማከለ መንገድ ለማግኘት እና ለሚመለከታቸዉ አካላት ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ አያያዝና ቢሮ አስተዳደር ስርዓት(ERP) በጢስ እሳት የተዘረጋ ሲሆን ድህረ-ገጽን በየተቋማቱ ማልማትና መዘርጋት የተቻለ ሲሆን ከቴክኖሎጅ አኳያ በጢስ እሳት የጂ.ፒ.ኤስ(GPS) ቴክኖሎጅ በተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ላይ ተገጥሞ ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡

በሌላ በኩል በዓለም የአበባ ገበያ በስፋት ለመግባት የሚያግዙ ሰርቲፊኬቶችን ለማግኘት በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ኤም.ፒ.ኤስ-ጋፕ (MPS-GAP) እና ኤም.ፒ.ኤስ ኤቢሲ(MPS-ABC) የተባለ ዓለም ዓቀፍ ሰርተፊኬት ማግኘት የተቻለ ሲሆን የኤስ.ኪዉ (SQ) እና ደንበኞች የሚፈልጓቸዉን ሌሎች ሰርተፊኬቶችን ለማሟላት ሂደቱ ተጀምሯል፡፡

በአጠቃላይ በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ ከላይ በተጠቀሰዉ አግባብ ተቋማዊ አቅም ግንባታ ስራ በተለዩ ጉዳዮች ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህም ምንም እንኳ የወቅቱ የቢዝነስ አለም ካለበት እጅግ የተፎካካሪነት ባህሪ አንጻር ተቋማዊ አቅም ግንባታዉ ሙሉ በሙሉ ወቅቱ በሚጠይቀው ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት ባያስደፍርም የመፈጸም አቅሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡

### 1.1.2. ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት

አዳዲስ ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት አኳያ በተጠናቀቀዉ ስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ዓመት ላይ ከነበሩት ሦስት ኩባንያዎች በመነሳት እቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ ሰባት ለመጨመር እቅድ ተይዞ ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም አንድ የጥናትና ዲዛይን ሥራ የሚሰራ ኩባንያ ብቻ ማቋቋም የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም ከሌሎች ጋር በሽርክና የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ አንድ የበቆሎ ስታርች ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ለማቋቋም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በስትራቴጅ እቅድ ዘመኑ ዉስጥ ነባር የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎችን ከማጠናከር አኳያ በዘመናዊ መንገድ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትን በማካሄድ ተጨማሪ የኤክስፖርት ምርት ማግኘት እና በኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ሁለንተናዊ አቅም በማሳደግ የግንባታ ፈቃድ ደረጃቸዉን ለማሳደግ የሚያስችሉ የእቅድ ግቦች ተቀምጠዉ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በጣና ፍሎራ በ34.5 ሄ/ር መሬት ላይ ዘመናዊ የጠብታ መስኖ በመዘርጋት በቁጥር 13,100 የአቮካዶ ችግኝ ተከላ በማካሄድ እንክብካቤ እየተደረገ ሲሆን የአቮካዶ ተክሉ በጥሩ ቁመና ላይ ይገኛል፡፡ በጢስ እሳት ዉሃ ሥራዎች ደግሞ በማሽነሪ፣ በተሽከርካሪና በኮንስትራክሽን ቁሳቁሶች አቅሙን ከማሳደግ አኳያ አንድ የጥልቅ ዉሃ ጉድጓድ መቆፈሪያ ማሽን(ሪግ) እና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን በማሟላት ወደ ደረጃ አንድ ተቋራጭ ማሳደግ ተችሏል፡፡ መቅደላ ኮንስትራክሽን ለማጠናከር በተደረገዉ ጥረትም የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎችን (ማለትም ዶዘር፣ ግሬደር፣ ሮለር ወዘተ) በማሟላት የኩባንያዉን የግንባታ ፈቃድ ከደረጃ አምስት ወደ ደረጃ ሦስት ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭነት ማሳደግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ላሊበላ የጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑትን የሰዉ ኃይል፣ ተሽከርካሪዎችንና ቁሳቁሶችን በማሟላት ኩባንያዉን በህንፃ፣ መንገድና በዉሃዉ ዘርፍ ከደረጃ ሶስት ወደ ደረጃ አንድ ጠቅላላ አማካሪ መሃንዲሶች ማሳደግ ተችሏል፡፡

### 1.1.3. የማህበራዊ ልማት ስራዎች

ኢንዶዉመንቱ ባለፉት ዓመታት የገቢ ማስገኛ ተቋማቱ ባመነጩት የፋይናንስ አቅም መሰረት የማህበራዊ ልማት ፕሮጀክቶችን በአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት (አመልድ) በኩል ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በዚህ መሰረት ባለፉት ዓመታት ኢንዶዉመንቱ በበጎ አድራጎት መስክ ያከናወናቸዉን ተግባራት በሚመለከት በጣና ፍሎራ እርሻ ልማት አካባቢ ወንጀጣ ቀበሌ ለሚገኙ ነዋሪዎች በ500 ሺ ብር የመጠጥ ውኃ ተቋም ግንባታ፣ ደረጃዉን የጠበቀ አንድ ብሎክ ትምህርት ቤት በ1.93 ሚሊየን ብር ሰርቶ ያስረከበ ሲሆን በተጨማሪም በአበባ እርሻዉ አካባቢ የሚገኙ ነዋሪዎችን የመብራት ተጠቃሚ ለማድረግ 2.6 ሚሊዮን ብር ለመብራት ኃይል ክፍያ ተፈጽሞ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

በተመሳሳይ በዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞን ለሚገኙ ወጣቶች በ1 ሚሊዮን ብር በንብ ማነብ ስራ እንዲሰማሩ በማድረግ፣ ሰሜን ወሎ መቄት ወረዳ 100 ሺህ ብር በመመደብ ወጣቶች በበግ እርባታ የስራ እድል በመፍጠር፣ በደቡብ ጎንደር እብናት ወረዳ ለሚገኙ 200 ወጣቶች 5 ሚሊዮን ብር በመመደብ የንግድ ክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ በማድረግ የተወሰኑት የራሳቸዉን ቢዝነስ እንዲጀምሩ ሲደረግ ቀሪዎቹ ደግሞ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በመያዝ በተለያዩ ተቋማት እንዲቀጠሩ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ ኢንዶውመንቱ ከላይ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና የበጎ አድራጎት ስራዎች ለማከናወን ብር 161.38 ሚሊዮን አቅዶ ብር 11.200 ሚሊዮን ስራ ላይ አውሏል፡፡በማህበራዊ ልማት የበጎ አድራጎት ስራዎች 6,250 የሚደርሱ ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 1,258 (20.12%) የተከናወን ሲሆን በዚህም የስራ እድል ፈጠራ፣ የንጹህ መጠጥ ዉሃ እና የት/ት ተቋም ግንባታ በማከናወን ተጠቃሚ የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በተጨማሪም ኢንዶውመንቱ ለገቢ ማስገኛ በአቋቋማቸዉ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በኩል በ28 ማህበራት ለተደራጁ ወንድ 107 ሴት፣ 33 በድምሩ 140 ወጣቶች በተለያዩ ግንባታ ስራዎች ላይ በማሳተፍ በጠቅላላዉ ብር 38,779,471.34 ዉል በመስጠት ወጣቶቹን የስራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተመቻችቶላቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የተለያዩ የግንባታ ፕሮጀክቶች በሚከናወንባቸዉ አካባቢዎች ለሚገኙ ዜጎች 40,570 ጊዜያዊ የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ 64,936(160%) በድግግሞሽ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

በበጎ አድራጎት ስራዎች ዙሪያ ከላይ የተጠቀሱት ስራዎች አበረታች ቢሆኑም ኢንዶዉመንቱ በቀጣይ ለዘርፉ በቂ ፋይናንስ በመመደብና በመከታተል በኩል የሚታየዉን ክፍተት በመቅረፍ የበጎ አድራጎት ስራዉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

### 1.1.4. የኩባንያዎች አፈጻጸም

ጋፋት ኢንዶውመንት የአቋቋማቸውና ወደ ተጨባጭ ሥራ ገብተው የሚገኙት ኩባንያዎች አራት ሲሆኑ እነዚህም ጣና ፍሎራ፣ ጢስ እሳት ውሃ ሥራዎች፣ መቅደላ ኮንስትራክሽን እና ላሊበላ የጥ/ዲ/ቁ/ ስራዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር ናቸው፡፡ የኩባንያዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በማተኮር ኢ.ኤ.አ ከ2016 እስከ 2020 የነበራቸዉን አፈፃጸም በሚከተለው መልኩ በአጭሩ ቀርቧል፡፡

#### ሀ/ ጣና ፍሎራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ጣና ፍሎራ ኃ/የተ/የግል ማህበር በ40 ሄ/ር መሬት ላይ የአበባ ምርት፣ በ30 ሄ/ር መሬት ፍራፍሬ እና በ25 ሄ/ር መሬት ላይ አትክልትን በማምረት ምርቱን በዋናነት ለውጭ ሀገር ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት፣ በክልሉ ውስጥ ሠፊ የሥራ እድልን ለመፍጠር፣ በዘርፉ የቴክኖሎጅ ሽግግር ለማምጣት እና ሌሎች ባለሃብቶች በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ እንዲሳተፉ ፋና ወጊ ሆኖ እንዲመራ ታስቦ የተቋቋመ ኩባንያ ነው፡፡

በመሆኑም ኢ.ኤ.አ ከ2016-2020 ድረስ በአማካይ በ32.5 የአበባ ማምረቻ ቤቶች ዉስጥ 378,400,000 የአበባ ዘንግ ለማምረት ታቅዶ 225,492,638(59.59%) ተመርቷል፡፡ በስትራቴጅክ እቅዱ በካሬ ሜትር ደረጃ 943 አበባ ዘንግ ለምረት ታቅዶ 693.82(73.34%) ተከናዉኗል:: ከአበባ ምርት ሽያጭ አኳያም በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ 331,261,000 የአበባ ዘንግ ለመሸጥ ታቅዶ 145,618,159(43.96%) ተሸጧል፡፡

ኩባንያው ከውጭ ሀገር አበባ ሽያጭ በአምስት ዓመታት ያገኘዉ አማካይ ጥቅል ገቢ 21,704,923.87 ዩሮ ከአዉሮፓ እና 758,448.40 ዶላር ከመካከለኛዉ ምስራቅ ነዉ፡፡ ገቢዉ በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ዓመት እድገት ያስመዘገበ ቢሆንም በእቅድ ዘመኑ የመጨረሻ ዓመታት የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ ጣና ፍሎራ ኃ/የተ/የግል ማህበር በአበባ ምርትና ገበያ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እድገት እያሳዬ የመጣና ለሀገሪቱም የውጭ ምንዛሬ ከማስገኘት አኳያ የራሱን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡ ለዚህም እውቀትና ክህሎትን በመገንባት ምርትና ምርታማነትን እና የምርት ጥራትን ተከታታይነት ባለው መልኩ ለማሳደግ እንዲሁም የገበያ መዳረሻ ሀገሮችን ለማስፋት ሰፊ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ይሁንና ኩባንያዉን ይበልጥ ዉጤታማ ከማድረግ አኳያ እውቀትና ክህሎትን በመገንባት ምርታማነትን በማሳደግ፣ የአበባ ምርት ጥራትን ተከታታይነት ባለው መልኩ በማሻሻል፣ የተጠናከረ የገበያ ልማትና ሰርተፊኬሽኖችን በማሟላት የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የሚጠበቀዉን ዉጤት በማምጣት ረገድ ዉስንነቶች ስለሚስተዋሉ በቀጣይ እነዚህን እጥረቶች በመቅረፍ በሙሉ አቅም መንቀሳቀስ ይገባል፡፡

## ለ/ ጢስ እሳት ዉሃ ኃ/ሥ/ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ጢስ እሳት ውሃ ሥራዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር በክልሉ ውስጥ በውሃው ዘርፍ የሚታዬውን የግንባታ የተደራሽነት ክፍተት ለመሙላትና የህብረተሰቡን የንፁህ መጠጥ ውሃ እንዲሁም የመስኖ አዉታር ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ታልሞ የተቋቋመ ኩባንያ ነው፡፡

ኩባንያው ከተሰማራባቸው የሥራ ዘርፎች መካከል አንዱ የጥልቅና መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም እ.ኤ.አ ከ2016 እስከ 2020 በጀት ዘመን 1,049 ጥልቅና መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓዶችን ለመቆፈር ታቅዶ 24 ጥልቅና 574 መለስተኛ ጥልቅ በድምሩ 598(57%) የዉኃ ጉድጓዶችን መቆፈር ተችሏል፡፡

ኩባንያው የተሰማራበት ሁለተኛው የሥራ ዘርፍ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት እና የመስኖ አውታሮች ግንባታ ነው፡፡ በዘርፉ ኩባንያው ልምዱን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጠናከረ በመምጣቱ በየዓመቱ በርካታ የግንባታ ፕሮጀክቶችን መገንባት የቻለበትን አቅም ፈጥሯል፡፡ ከዚህ አኳያ ባለፉት አምስት ዓመታት 76 ንፁህ መጠጥ ውሃ እና 35 መስኖ ፕሮጀክቶችን ግንባታ ለማከናወን ታቅዶ 84(110.5%) ንፁህ መጠጥ ውሃ እና 17(48.5%)መስኖ ፕሮጀክቶችን ግንባታ አከናዉኗል፡፡

በመሆኑም ከዉሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ከግንባታ አኳያ ኩባንያው የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ባደረገው ጥረት በየዓመቱ አበረታች ውጤት እያስመዘገበና እድገት እያሳዬ የመጣ በመሆኑ ክልላዊና ሀገራዊ ተልዕኮዉን እየተወጣ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጅ በአለፉት ዓመታት የፕሮጀክት ሥራ አመራር ልምድ ማነስ፣ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ አለመኖር፣ ዉጤታማ የሀብት አጠቃቀም እና ወጭ ቆጣቢ አሰራርን አለመከተል፣ በተደራጀ መንገድ የገበያ ልማት ስራዎችን አለመስራት፣ በማሽነሪና ተሽከርካሪ የኩባንያዉን አቅም በሚፈለገዉ ደረጃ ማጠናከር አለመቻል የመሳሰሉ እጥረቶች የሚታዩ በመሆኑ በቀጣዮቹ ዓመታት ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ ያሳያል፡፡

## ሐ/ መቅደላ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር

መቅደላ ኮንስትራክሽን በክልሉ በግንባታዉ ዘርፍ የሚታየውን ክፍተት ለመሙላት የተቋቋመ ኩባንያ ነው፡፡ ኩባንያው በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ በድልድይ፣ በመንገድና በህንጻ ግንባታ የስራ መስኮች እንዲሁም በማሽነሪና ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት ተሳትፎ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም ኩባንያው ባለፉት አምስት ዓመታት በማሽነሪ፣ በተሽከርካሪና በሰዉ ኃብት ተቋማዊ አቅሙን በማጠናከር በግንባታዉ ዘርፍ ወደ ስራ በመግባት 1,600 ሊኒየር ሜትር ድልድዮች፣ 105 ኪ/ሜትር መንገድና 22 የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶችን ለማካሄድ ታቅዶ 11 ወይም 390 (24.4%) ሊኒየር ሜትር ድልድዮች፣ 23(21.9%) ኪ/ሜትር መንገድና 26(118.18%) የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶችን ግንባታ አከናዉኗል፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ በጠቅላላዉ 27 ፕሮጀክቶችን አጠናቆ ለአሰሪዎች ማስረከብ የተቻለ ሲሆን በተጨማሪም በማሽነሪና ተሽከርካሪ ዘርፍ 62,876 ሰዓት እና 150,000 ኪሎ ሜትር የኪራይ አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 10,835.84(17.23%) ሰዓት እና 54,283(36.19%) ኪሎ ሜትር የኪራይ አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

ኩባንያው ወደ ግንባታ ስራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በሂደት ልምድ እየቀሰመና አፈፃፀሙን እያሻሻለ በክልሉ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆን በተደረገዉ ጥረት ከድልድይ ግንባታ በመነሳት መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ያላቸዉን የህንጻ ግንባታ ፕሮጀክቶች ማከናወን የሚችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ይሁን እንጅ ባለፉት ዓመታት የፕሮጀክት ሥራ አመራር እዉቀት፣ ክህሎትና ልምድ ማነስ፣ ቁርጠኝነትና ቅንጅታዊ አሰራር በሚፈለገዉ ደረጃ አለመሆን፣ የተጠናከረና ችግር ፈች ክትትልና ድጋፍ አለማድረግ፣ ዉጤታማ የሀብት አጠቃቀም እና ወጭ ቆጣቢ አሰራርን አለመከተል፣ በተደራጀ መንገድ የገበያ ልማት ስራዎችን አለመስራት ክፍተቶች የተስተዋሉ ሲሆን በሌላ በኩል በማሽነሪና ተሽከርካሪ የኩባንያዉን አቅም በማጠናከርም ከደረጃ አምስት ወደ ደረጃ ሦስት የደረሰ ቢሆንም የሚፈለገዉን የግንባታ ፈቃድ ደረጃ አንድ ለማድረስ በቀጣዮቹ ዓመታት ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ ያሳያል፡፡

**መ/ ላሊበላ ጥ/ዲ/ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**

ላሊበላ የጥናት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች በክልሉ ዉስጥ በጥናት፣ ዲዛይንና ኮንትራት አስተዳደር ዘርፍ የሚታየዉን የገበያ ጉድለት ለመሙላት እና በዚህ ዘርፍ ሙያዊ ስነ-ምግባርን በተላበሰና ጥራትን ማዕከል ባደረገ አግባብ መንቀሳቀስ የሚችል ኩባንያ ለመፍጠር ታስቦ በስትራቴጂክ እቅድ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ የተቋቋመ ነዉ፡፡ ኩባንያዉ የተቋቋመበትን ተልዕኮ እንዲያሳካ ተቋማዊ አደረጃጀት በመዘርጋት በዘርፉ የተሻለ እዉቀትና ክህሎት ያላቸዉን ባለሙያዎች በመያዝ ወደ ስራ ገብቷል፡፡

ስለሆነም ተቋሙ በህንጻ፣ በመንገድና ድልድይ፣ በንጹህ መጠጥ ዉሃ፣ በመስኖ ድሬይኔጅ፣ በሃይድሮ-ጅኦሎጅና ጅኦ-ቴክኒክ እንዲሁም በፕሮጀክትና የአካባቢ ተፅኖ ግምገማ ዘርፎች 540 ፕሮጀክቶችን ለማከናወን አቅዶ 149(27.59%) አከናዉኗል፡፡ በተመሳሳይ የቁጥጥርና ማማከር ስራዎችን በሚመለከት በህንጻ፣ በመንገድና ድልድይ፣ በንጹህ መጠጥ ዉሃ፣ በመስኖ ድሬይኔጅ 579 ፕሮጀክቶችን ለማከናወን ታቅዶ 109(18.83%) ማከናወን ችሏል፡፡

ኩባንያዉ ከተቋቋመበት አጭር ጊዜ አንጻር ራሱን በሰዉ ኃብትና በቁሳቁስ አደራጅቶ ፈጥኖ ወደ ስራ በመግባት በፕሮጀክት ቁጥር፣ በስራ ጥራት እና በወቅቱ በማጠናቀቅ ያሳየዉ አፈጻጸም የሚበረታታ ነዉ፡፡ ነገር ግን ኩባንያዉ በዘርፉ በክልሉ ያለዉን ክፍተት ለመሙላት ይዞት ከተነሳዉ ዓላማ አንጻር የሰዉ ኃብቱን በአመለካከትና በክህሎት አንጻ ስራዎችን በጥራትና በፍጥነት በማከናወን ከሌሎች መሰል ተቋማት ልቆ በመገኘት፣ የተጠናከረና ችግር ፈቺ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ በተደራጀ መንገድ የገበያ ልማት ስራዎችን በመስራት እንዲሁም ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ ጠቃሚ አሰራሮችን በመዘርጋት በኩል ያሉ ክፍተቶችን ለመቅርፍ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

### 1.1.5. የተጠቃለለ ፋይናንስ አፈጻጸም

ጋፋት ኢንዶውመንት እና ኢንዶዉመንቱ ኢንቨስት ባደረገባቸው ኩባንያዎች የፋይናንስ አስተዳደሩን በሥርዓት ለመምራት በሁሉም ተቋማት የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ያለፉትን አምስት ዓመታት የፋይናንስ አፈጻጸም በሚከተለዉ ሰንጠረዥ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 1.1.6. የተጠቃለለ ፋይናንስ አፈጻጸም

| የሥራ ዘመን | የሂሳቡ ዓይነት | ጣና ፍሎራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | | | | ጢስ እሳት ው/ሥ/ኃ/የተ/የግ/ማህበር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | ዕድገት /ቅናሽ/በ% | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | ዕድገት /ቅናሽ/በ% |
| Dec.31/2016 | ገቢ | 190,216,643 | 150,979,359.0 | 79.4 | | 130,327,715 | 183,568,328.7 | 140.9 | |
| | ወጪ | 159,542,290 | 134,965,296.0 | 84.6 | | 97,745,786 | 143,125,643.4 | 146.4 | |
| | ትርፍ | 30,674,653 | 16,014,063.0 | 52.2 | | 32,581,929 | 40,442,685.3 | 124.1 | |
| Dec.31/2017 | ገቢ | 232,327,143 | 131,957,762.0 | 56.8 | (12.6) | 162,909,643 | 230,860,471.7 | 141.7 | 25.8 |
| | ወጪ | 195,786,960 | 116,697,105.0 | 59.6 | (13.5) | 122,182,232 | 183,853,794.3 | 150.5 | 28.5 |
| | ትርፍ | 36,540,183 | 15,260,657.0 | 41.8 | (4.7) | 40,727,411 | 47,006,677.4 | 115.4 | 16.2 |
| Dec.31/2018 | ገቢ | 241,245,743 | 162,280,887.0 | 67.3 | 23.0 | 203,637,053 | 367,410,947.7 | 180.4 | 59.1 |
| | ወጪ | 201,348,786 | 140,098,053.0 | 69.6 | 20.1 | 152,728,127 | 302,557,424.6 | 198.1 | 64.6 |
| | ትርፍ | 39,860,957 | 22,182,832.0 | 55.7 | 45.4 | 50,908,926 | 64,853,523.1 | 127.4 | 38.0 |
| Dec.31/2019 | ገቢ | 270,015,443 | 89,551,338.0 | 33.2 | (44.8) | 254,546,316 | 330,373,642.3 | 129.8 | (10.1) |
| | ወጪ | 218,553,989 | 117,385,100.0 | 53.7 | (16.2) | 190,909,737 | 302,376,277.3 | 158.4 | (0.1) |
| | ትርፍ | 51,461,454 | (27,833,762.0) | (54.1) | (225.5) | 63,636,579 | 27,997,365.0 | 44.0 | (56.8) |
| Dec.31/2020 | ገቢ | 203,537,916 | 163,619,105.5 | 80.4 | 82.7 | 428,515,071 | 457,735,978.8 | 106.8 | 38.6 |
| | ወጪ | 187,628,356 | 143,682,039.7 | 76.6 | 22.4 | 393,515,070.7 | 425,485,441.4 | 108.1 | 40.7 |
| | ትርፍ | 15,909,559 | 19,937,065.8 | 125.3 | (171.6) | 35,000,000 | 32,250,537.4 | 92.1 | 15.2 |
| ሀባትና እዳ | ሃብት | | 169,659,346 | | | | 451,954,429 | | |
| | ዕዳ | | 87,613,204 | | | | 310,383,746 | | |
| ድምር | ገቢ | 1,137,342,887.6 | 698,388,451.5 | 61.4 | | 1,179,935,797.7 | 1,569,949,369.2 | 133.1 | |
| | ወጪ | 962,860,381.4 | 652,827,593.7 | 67.8 | | 957,080,952.7 | 1,357,398,580.9 | 141.8 | |
| | ትርፍ | 174,446,806.3 | 45,560,855.8 | 26.1 | | 222,854,845.0 | 212,550,788.3 | 95.4 | |
| አማካኝ አፈጻጸም | በገቢ | 227,468,577.5 | 139,677,690.3 | 61.4 | | 235,987,159.5 | 313,989,873.8 | 133.1 | |
| | በወጪ | 192,572,076.3 | 130,565,518.7 | 67.8 | | 191,416,190.5 | 271,479,716.2 | 141.8 | |
| | በትርፍ | 34,889,361.3 | 9,112,171.2 | 26.1 | | 44,570,969.0 | 42,510,157.7 | 95.4 | |

የቀጠለ.........................

| የሥራ ዘመን | የሂሳቡ ዓይነት | መቅደላ ኮን/ማሽ/አከ/ኃ/የተ/የግ/ማህበር | | | | ላሊበላ የጥ/ዲ/ቁ/ኃ/የተ/የግ/ማህበር | | | | ኢንዶዉመንት ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | ዕድገት /ቅናሽ/በ% | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በ% | ዕድገት /ቅናሽ/በ% | ዕቅድ | ክንውን | ክንውን በ% |
| **Dec.31/2016** | ገቢ | 65,320,408 | 32,141,812.8 | 49.2 | | 30,365,000 | 6,356,182.8 | 20.9 | 0.0 | 416,229,766.0 | 373,045,683.3 | 89.6 |
| | ወጪ | 54,472,905 | 27,954,322.5 | 51.3 | | 17,923,732 | 5,568,665.7 | 31.1 | 0.0 | 329,684,713.0 | 311,613,927.5 | 94.5 |
| | ትርፍ | 10,847,503 | 4,187,490.4 | 38.6 | | 12,441,268 | 787,517.1 | 6.3 | 0.0 | 86,545,353.0 | 61,431,755.8 | 71.0 |
| **Dec.31/2017** | ገቢ | 161,420,408 | 68,375,710.8 | 42.4 | 112.7 | 65,449,017 | 30,251,169.3 | 46.2 | 375.9 | 622,106,211.0 | 461,445,113.8 | 74.2 |
| | ወጪ | 136,559,584 | 50,248,280.4 | 36.8 | 79.8 | 44,869,516.53 | 18,607,553.0 | 41.5 | 234.1 | 499,398,292.5 | 369,406,732.7 | 74.0 |
| | ትርፍ | 24,860,824 | 18,127,430.4 | 72.9 | 332.9 | 20,579,501.47 | 11,643,616.3 | 56.6 | 1,378.5 | 122,707,919.5 | 92,038,381.1 | 75.0 |
| **Dec.31/2018** | ገቢ | 229,928,000 | 102,641,183.5 | 44.6 | 50.1 | 133,785,918 | 40,667,658.9 | 30.4 | 34.4 | 808,596,714.0 | 673,000,677.2 | 83.2 |
| | ወጪ | 194,464,830 | 106,067,772.2 | 54.5 | 111.1 | 80,319,558.59 | 30,724,417.5 | 38.3 | 65.1 | 628,861,301.6 | 579,447,667.3 | 92.1 |
| | ትርፍ | 35,463,170 | (3,426,588.7) | (9.7) | (118.9) | 53,466,360.41 | 9,943,241.4 | 18.6 | (14.6) | 179,699,413.4 | 93,553,007.9 | 52.1 |
| **Dec.31/2019** | ገቢ | 296,166,000 | 143,226,739.3 | 48.4 | 39.5 | 216,975,684 | 54,389,388.1 | 25.1 | 33.7 | 1,037,703,443.0 | 617,541,107.7 | 59.5 |
| | ወጪ | 251,081,150 | 131,231,308.0 | 52.3 | 23.7 | 124,150,142.91 | 42,375,872.3 | 34.1 | 37.9 | 784,695,018.9 | 593,368,557.6 | 75.6 |
| | ትርፍ | 45,084,850 | 11,995,431.3 | 26.6 | (450.1) | 92,825,542.09 | 12,013,515.8 | 12.9 | 20.8 | 253,008,425.1 | 24,172,550.1 | 9.6 |
| **Dec.31/2020** | ገቢ | 279,671,660 | 125,912,963.0 | 45.0 | (12.1) | 79,943,752.00 | 53,525,568.1 | 66.95 | (1.6) | 991,668,398.6 | 800,793,615.3 | 80.8 |
| | ወጪ | 259,138,353 | 135,322,887.2 | 52.2 | 3.1 | 67,220,476.00 | 43,419,312.0 | 64.6 | 26.3 | 907,502,256.3 | 747,909,680.3 | 82.4 |
| | ትርፍ | 20,533,307 | (9,409,924.2) | (45.8) | (178.4) | 12,723,276.00 | 10,106,256.1 | 79.4 | (15.9) | 84,166,142.3 | 52,883,935.1 | 62.8 |
| **ሀባትና እዳ** | ሃብት | | 161,013,230.4 | | | | 56,878,056.6 | | | | 839,505,062.2 | |
| | ዕዳ | | 140,735,926.3 | | | | 23,174,529.2 | | | | 561,907,404.9 | |
| **ድምር** | ገቢ | 1,032,506,476.3 | 472,298,409.5 | 45.7 | | 526,519,371.0 | 185,189,967.2 | 35.2 | | 3,876,304,532.6 | 2,925,826,197.3 | 75.5 |
| | ወጪ | 895,716,822.3 | 450,824,570.2 | 50.3 | | 334,483,426.0 | 140,695,820.5 | 42.1 | | 3,150,141,582.4 | 2,601,746,565.4 | 82.6 |
| | ትርፍ | 136,789,654.0 | 21,473,839.2 | 15.7 | | 192,035,948.0 | 44,494,146.7 | 23.2 | | 726,127,253.3 | 324,079,630.0 | 44.6 |
| **አማካኝ አፈጻጸም** | በገቢ | 206,501,295.3 | 94,459,681.9 | 45.7 | | 105,303,874.2 | 37,037,993.4 | 35.2 | | 775,260,906.5 | 585,165,239.5 | 75.5 |
| | በወጪ | 179,143,364.5 | 90,164,914.0 | 50.3 | | 66,896,685.2 | 28,139,164.1 | 42.1 | | 630,028,316.5 | 520,349,313.1 | 82.6 |
| | በትርፍ | 27,357,930.8 | 4,294,767.8 | 15.7 | | 38,407,189.6 | 8,898,829.3 | 23.2 | | 145,225,450.7 | 64,815,926.0 | 44.6 |

ከላይ በሰንተረዡ እንደተመለከተዉ ገቢን በተመለከተ የኢንዶውመንቱ የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ኢ.ኤ.አ ከ2016 እስከ 2020 ድረስ ብር 3,876,304,532 ገቢ ለማመንጨት ዕቅድ ይዞ በጥቅሉ ብር 2,925,826,197.3(75.5%) ገቢ አከናዉኗል፡፡ የእያንዳንዱን የገቢ ማስገኛ ኩባንያ የገቢ አፈፃፀም ድርሻ ስናይ ጣና ፍሎራ ብር 23.87%፣ ጢስ እሳት ብር 53.66%፣ መቅደላ ብር 16.14% እና ላሊበላ 6.33% ይይዛሉ፡፡

ይህ የገቢ አፈጻጸም እንደሚያሳየዉ በየዓመቱ ጥቅል እድገት እያሳየ የመጣ ቢሆንም ከኩባንያ ኩባንያ የሚለያይና በአምስት ዓመቱ ካስቀመጡት እቅድ አንጻር ሲመዘን በሚጠበቀዉ ደረጃ አልደረሰም፡፡

ከወጪ አኳያ የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች እንደ ኢንዶዉመንት በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ ብር 3,150,141,582.4 ወጪ ለማድረግ ታቅዶ ብር 2,601,746,565.4 (82.6%) ወጪ ተደርጓል፡፡ የገቢ ማስገኛ ኩባንያ የወጭ አፈፃፀም ድርሻ ሲታይ ጣና ፍሎራ 25.09%፣ ጢስ እሳት 52.17%፣ መቅደላ 17.33% እና ላሊበላ 5.41% ይይዛሉ፡፡ የወጪ አፈጻጸሙ ከገቢ አፈጻጸም ጋር ሲታይ ጭማሪ እንዳለዉ የሚያሳይ ሲሆን ለዚህም በምክንያትነት የሚጠቀሱት ጉዳዮች ወጪ ቆጣቢ የሆነ የግዥ ሂደት እና ዉጤታማ የሃብት አጠቃቀም አለመከተል፣ የአየር መንገድ መጓጓዣ ዋጋ በየጊዜዉ መጨመር፣ የዉጭ ምንዛሬ ተመን ማሻሻያ መደረጉ፣ የተረጋጋ የገበያ ሁኔታ አለመኖር፣ በየጊዜዉ የተከሰቱ የጸጥታ ችግሮች፣ የኮቪድ-19 መከሰት የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በኢንዶዉመንት ደረጃ ከግብር በፊት ትርፍ ብር 726,127,253.3 ለማግኘት ዕቅድ ተይዞ ብር 324,079,630(44.6%) እንደተገኘ መረጃዉ ያሳያል፡፡ በኩባንያ ደረጃ የትርፍ አፈፃፀም ድርሻ ሲታይ ጢስ እሳት 65.59%፣ ፍሎራ 14.05%፣ ላሊበላ 13.73% እና መቅደላ 6.63% ጣና ይይዛሉ፡፡ የገቢ ማስገኛ ተቋማቱ በቀጣይ ለኢንዶዉመንቱ ዓላማዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን ሃብት ከማመንጨት አኳያ የሚታዩባቸዉን ክፍተቶች ማለትም የግዥ ስርዓቱን በእቅድ በመምራት፣ ወጪ ቆጣቢ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋትና በመተግበር፣ ውጤታማ የሆነ የገበያ ልማት ስራን በመስራት፣ የግብዓት አጠቃቀምን በማሻሻል፣ የመፈፀም ብቃትን በማሳደግ እና ሌሎች ተግባራትን አቀናጅቶ በመፈፀም በአስተማማኝነት ትርፍ ወደ ማመንጨት መሸጋገር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኢ.ኤ.አ በ2020 በጀት ዓመት ማጠቃለያ ላይ በቀረበው የኩባንያዎች የሃብትና ዕዳ መግለጫ መሠረት ጣና ፍሎራ አጠቃላይ ሃብት ብር 169,659,346፣ ዕዳ ብር 87,613,204፣ በጢስ እሳት አጠቃላይ ሃብት ብር 451,954,429፣ ጠቅላላ ዕዳ ብር 310,383,746፣ መቅደላ አጠቃላይ ሃብት ብር 161,013,230.40 ፣ ጠቅላላ እዳ 140,735,926.30 እንዲሁም ላሊበላ አጠቃላይ ሀብት ብር 56,878,056.60፣ ጠቅላላ ዕዳ 23,174,529.20 ብር ሲሆን አጠቃላይ ዕዳ ከሃብት ጋር በንጽጽር ሲታይ

በጣና ፍሎራ 51.64%፣ በጢስ እሳት 68.67%፣ በመቅደላ 87.4% እና ላሊበላ 40.74% በዕዳ ወይም በተከፋይ ሂሳብ እንደተያዘ ያሳያል፡፡ ተቋማቱ አሁን ላይ ዕዳቸውን ለመክፈል ያሉበት ደረጃ ከከፍተኛው ወደ ዝቅተኛው ሲታይ ላሊበላ፣ ጣና ፍሎራ፣ ጢስ እሳት እና መቅደላ ተብሎ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ መረጃዉ እንደሚያሳየዉ መቅደላና ጢስ እሳት ከአጠቃላይ ሀብታቸዉ ዉስጥ ከፍተኛ ተከፋይ ዕዳ ያለባቸዉ ሲሆን ጣና ፍሎራ ግማሽ ሀብቱ እንዲሁም ላሊበላ አነስተኛ ሀብቱ በእዳ እንደተያዘ ያመላክታል፡፡

ኢንዶውመንቱ ባለፉት አምስት ዓመታት በዋናነት በገቢ ማስገኛ ኩባንያዎቹ አማካኝነት የፋይናንስ አቅሙን ለማሳደግ በሁሉም ደረጃ ጥረት ሲያደርግ የቆየ ቢሆንም አሁንም ድረስ የመስሪያ ገንዘብ እጥረት ለተቋማቱ ማነቆ ሆኖ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ኢንዶዉመንቱ እንደየተቋማቱ ተጨባጭ ሁኔታ ይህን ማነቆ ሊቀርፉ የሚችሉ ስልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 1.2. የዉስጣዊ ሁኔታ ትንተና

የኢንዶዉመንቱን ዉስጣዊ ሁኔታዎች ከስትራቴጅ፣ አደረጃጀት፣ አሰራር ስርዓት፣ የጋራ እሴቶች፣ የአመራር ሁኔታ፣ የሰዉ ኃብት ክህሎትን ማዕከል በማድረግ በዋናነት በ7`S ሞዴል እንደሚከተለዉ ተተንትኗል፡፡

### 1.2.1. ስትራቴጅ (Strategy)

ኢንዶውመንቱ የተቋቋመበትን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት ይችል ዘንድ በስትራቴጅ መመራት አስፈላጊ በመሆኑ እ.ኤ.አ ከ2016-2020 የሚቆይ የ5 ዓመት እቅድ በባላንስድ ስኮር ካርድ(BSC) የአስተቃቀድ ስልት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ከኢንዶዉመንቱ ስትራቴጅክ እቅድ በመነሳት ኩባንያዎች ድርሻቸዉን በመለየት ከራሳቸዉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የአምስት ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ በማዘጋጀት ተግብረዋል፡፡ ስለሆነም ተቋማቱ በስትራቴጅክ እቅድ እንዲመሩ ለማድረግ ከኢንዶዉመንቱ ወደ ኩባንያዎች ተሸንሽኖ (Cascade) ተደርጎ የወረደበት መንገድ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡

ይሁን እንጅ ከሚዛናዊ ዉጤት ተኮር አስተቃቀድ አኳያ በተቋም ደረጃ የተዘጋጀዉን ዕቅድ ለሥራ ክፍሎችና ለፈፃሚዎች ማውረድ(Cascading) ላይ ከተቋም ተቋም የሚለያይ ሆኖ በጥቅሉ በዚህ ረገድ እንደኢንዶዉመንት ክፍተት ነበረበት፡፡ በሌላ በኩል በስትራቴጅዉ ትግበራ ወቅት እቅዱን በየጊዜዉ ከነባራዊ ሁኔታዉ ጋር በማጣጣም እየፈተሹ መከለስ አለመቻል፣ ትግበራዉን ውጤታማ ለማድረግ የባላንስድ ስኮር ካርድ አውቶሜሽን ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ አቅዱን እስከ ግለሰብ ፈጻሚ ድረስ ማዉረድና በአፈጻጸም ዉጤት መሰረት ከሽልማት ጋር አለማስተሳሰር እንዲሁም ስትራቴጅዉን

ለማስፈጸም መዘጋጀት ያለባቸዉ ስትራቴጅያዊ እርምጃዎችን(Strategic Initiatives) በተሟላ መንገድ መዘርጋትና መተግበር አለመቻል ዋና ዋና ክፍተቶች ናቸዉ፡፡

### 1.2.2. አደረጃጀት (Structure)

ጋፋት ኢንዶዉመንት በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ማህበራት መመዝገቢያና ማስተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር 194/2004 መሰረት ዘላቂ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሩበት ህግና አዋጁን መሰረት ባደረገ አግባብ የተቋቋመና ዘጠኝ አባላት ባሉት የሥራ አመራር ቦርድ የሚመራ ነዉ፡፡ ከሥራ አመራር ቦርዱ ቀጥሎ የኢንዶዉመንቱን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚመራና ኩባንያዎችን በበላይነት የሚያስተባብር ጽ/ቤት ያለዉ ሲሆን በዋና እና በምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ የሚመራ ነዉ፡፡ በኢንዶዉመንቱ ስር ያሉት የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ደግሞ በራሳቸዉ ዋና እና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም የስራ ክፍሎችን በሚመሩ ባለሙያዎች የተዋቀሩ ናቸዉ፡፡

የኢንዶዉመንቱ መዋቅር ከላይ በተጠቀሰዉ መልኩ ሲሆን ከወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታዉ ጋር ሊሄድ የሚችል በጥናት ላይ የተመሰረተ የመዋቅር ማሻሻያዎችን በተለያየ ጊዜ አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ ኩባንያዎችም ተግባርና ኃላፊነታቸዉን በሚፈለገዉ ደረጃ ለመወጣት የሚያስችላቸዉን የአደረጃጀት፣ የመዋቅርና ደመወዝ ማሻሻያዎችን አድርገዋል፡፡ ይህም በየተቋማቱ የተሳለጠና ዉጤታማ ስራ በመስራት ብቁና ተወዳዳሪ ለመሆን፣ በስራ ላይ ያለዉን የሰዉ ኃይል ለማቆየትና የተሻሉ ባለሙያዎችን ወደ ተቋማቱ ለመሳብ እገዛ ያደረገ ሲሆን በዚህ ዙሪያ የተሰራዉ ስራ በጥንካሬ የሚወሰድ ነዉ፡፡

ከላይ በጥንካሬ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆኖ የኢንዶውመንት ጽ/ቤቱንና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎችን አደረጃጀቱን መሰረት በማድረግ የተሟላ የፈጻሚ ቁጥር እንዲኖር አለማድረግ (ለአብነት የቢዝነስ አማካሪ፣ የፕሮጀክት ጥናትና ክትትል፣ የበጎ አድራጎት ስራዎች ክትትልና ድጋፍ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተሟላ አደረጃጀት የሰው ሃይል አለመኖር)፣ ተቋማት የሰው ሃይሉን በብቃትና ለተልእኳቸው በሚመጥን አግባብ ማድረስ አለመቻል፣ የገበያ ልማት ስራዎችን በባለቤትነት ይዞ ሊመራ የሚችል የተጠናከረ አደረጃጀት አለመኖር፣ በአበባ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ ቴክኒካል አማካሪ እንዲኖር የሚያስችል አደረጃጀት አለመኖር የሚታዩ ክፍተቶች ናቸው፡፡

### 1.2.3. አሰራር ስርዓት (System)

የየተቋማቱን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገምና በየተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ኩባንያዎቹን ተወዳዳሪና ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ የግዥና ፋይናንስ፣ የሰዉ ኃብት አስተዳደር፣ የሃብት አስተዳደር፣ የስራ ስታንዳርዶችን፣ እንደኢንዶዉመንት ጠንካራ የክትትክልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት፣ የለዉጥ ስራዎችን በመተግበር፣ የመረጃና የቴክኖሎጅ አጠቃቀም በማሳደግ፣ የአሠራር ስርዓቶችን በመለየት ከነባራዊ ሁኔታቸው ጋር በማዛመድ ተግባራዊ ለማድረግ ባለፉት አምስት ዓመታት የተሄደበት ርቀት በጥንካሬ የሚወሰድ ነዉ፡፡

የአሠራር ስርዓቶችን ከማሟላት አኳያ ከላይ በተገለጸዉ አግባብ በርካታ በየጊዜዉ ማሻሻያ እየተደረገባቸዉና በአዲስ እየተዘረጉ የመጡ ቢሆንም እነዚህን የአሰራር ስርዓቶች አሟልቶ በመተግበር ረገድ በኩባንያዎች በኩል የተሟላ አልነበረም፡፡ ለአብነትም የሰዉ ኃብት ስምሪትና አስተዳደር ላይ የሚታይ ክፍተት፣ በግብዓት አቅርቦትና ስርጭት፣ በግዥ በኩል የሚታይ ቅንጅትና ቅልጥፍና የጎደለዉ መሆን፣ የተዘረጉ የስራና የሀብት አጠቃቀም ስታንዳርዶችን በሚፈለገዉ ደረጃ ዉጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ አለማድረግ፣ በፕሮጀክቶች ደረጃ የሚደረገዉ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ክፍተት ያለበት መሆኑ፣ የለዉጥ ስራዎችን(ካይዘንና BSCን) በአመለካከትና በቁርጠኝነት ይዞ ተግባራዊ በማድረግ ተቋማዊ ሆነዉ የሚዘልቁበትን ሁኔታ መፍጠር አለመቻሉ፣ የአበባ ዝርያ ቅየራ ማድረግ አለመቻ፣ መካከለኛው ምስራክ ገበያ በስፋት ለመግባት የሚያስችል አሰራር ቀይሶ ወደ ስራ መግባት አለመቻል፣ የአበባ ገበያ መዳረሻን ለማስፋት የሚያግዙ የሰርተፊኬሽን ስታንዳርዶችን በወቅቱ አሟልቶ አለመገኘት የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ እንደኢንዶዉመንት ባለፉት ዓመታት ከአሰራር ስርዓት ግንባታ አንጻር የተሰራዉ ስራ ብዙ ርቀት የተሄደበት ቢሆንም ተቋማት የአሰራር ስርዓቶችን በተሟላ ሁኔታ ፈጥኖ በመዘርጋት፣ በማሻሻልና በመተግበር በኩል ክፍተቶች ተስተዉለዋል፡፡

### 1.2.4. የጋራ እሴቶች (Shared Values)

ጋፋት ኢንዶዉመንት የተቋቋመበትን ተልዕኮ በመፈጸም ራዕዩን ለማሳካት የሚያግዙትን እሴቶች በመቅረጽ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አኳያ ተቋማት የጋራ የሚያደርጋቸዉና ለአንድ ዓላማ የሚያሰልፋቸዉ ተቋማዊ እሴት ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡ በመሆኑም እሴቶችን በስትራቴጂ ዘመኑ እንደየተቋማቱ የስራ ባህሪ በመቅረጽ በየደረጃው በሚገኘዉ አመራርና ፈፃሚ አካላት ዘንድ እንዲታወቁና የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመሰረትባቸዉ መርሆዎችና በተቋሙ ዉስጥ የሰረጹ እምነቶች፣ አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን የሚያንጸባርቁ ተቋማዊ የአሰራር ፍልስፍና መገለጫዎች

እንዲሆኑ ለማስቻል የተደረጉት ጥረቶች በጥንካሬ የሚወሰዱ ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም ተቀራራቢ ተቋማዊ አስተሳሰብ ለመፍጠር የሚያስችሉ እና የሰራተኞችን መስተጋብር ሊያሳድጉ የሚችሉ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች(መረዳጃ ማህበር፣ የሰራተኞች ቁጠባና ብድር ማህበር) መኖራቸዉ ለእሴት ግንባታ አቅም የሚፈጥሩ ናቸዉ፡፡

ነገር ግን ተቋማዊ እሴቶቹ አሁንም ድረስ እንደኢንዶዉመንት በአመራሩና በፈጻሚዉ ዘንድ በሚፈለገው ደረጃ ሰርፀው የዕለት ተዕለት የሥራ ባህልና መመሪያ ሁነዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ከዚህ አኳያ በቀጣዩ የስትራቴጅክ እቅድ ዘመን እሴቶችን በይበልጥ በማስረፅ የሚፈለገዉን ዉጤት ለማምጣት የእሴት መገንቢያ ስልቶችን በየተቋማቱ ነድፎ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡

### 1.2.5. የአመራር ሁኔታ (Leadership Style)

በጋፋት ኢንዶውመንት በየደረጃዉ የሚገኝ አመራር ከሚጠበቅበት ተግባርና ኃላፊነቶች አንዱ አሳታፊ በሆነ መንገድ ዕቅድ በማዘጋጀት በየደረጃው ላሉ ፈፃሚ አካላት ማውረድና እዉቅና መፍጠር፣ በአፈፃፀም ሂደት ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል ማድረግ እንዲሁም የሚጠበቀው ውጤት መገኘቱን በማረጋገጥ ተገቢውን አቅጣጫ መስጠትና ጉድለቶች ሲገኙ የማስተካከያ እርምጃ መዉሰድ ነዉ፡፡

በዚህ ረገድ በየደረጃዉ የሚገኘዉ የኢንዶዉመንቱ አመራር ዕቅድን አሳታፊ በሆነ አግባብ እንዲዘጋጅ የማድረግና ሥራዎችን ከፋፍሎ የመስጠትና በጋራ እየገመገሙ የመምራት አቅም፣ የፈፃሚ ኃይሉን ክፍተት የመለየትና ጉድለቱን ለመሙላት እያዳበረ የመጣዉ የአመራር ልምድ፣ ለውጤት ሊያበቃ የሚያስችል የድጋፍና ክትትል ስርዓት መዘርጋቱ፣ የስራ ግብዓቶችን ለማሟላት የሚያደረገው ጥረት፣ የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋት፣ በማሻሻልና በመተግበር በአመራሩ በኩል በጥንካሬ የሚወሰዱ ናቸው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰዉ በአመራሩ ዘንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እና ተደማሪ ዉጤቶች እየታዩ የመጡ ቢሆንም አሁንም እንደ ኢንዶዉመንት በቀጣይ ሥራ የሚጠይቁ ጉድለቶች ይስተዋላሉ፡፡ አመራሩ በገበያ ዉድድር መርህ ላይ ተመስርቶ ቀጣይነት ባለዉ መልኩ ቢዝነስ ለመምራት የሚያስችል አመለካከትና ክህሎት በአግባቡ የያዘ አለመሆኑ፣ ዉሳኔ በሚያስፈልጋቸዉ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት በመያዝ በቁርጠኝነት አለመወሰን፣ የለዉጥ መሳሪያዎችን በትኩረት ይዞ አለመምራት፣ የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱን ችግር ፈቺ በማድረግ የተግባራት በወጣላቸዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተሟልተዉ እንዲፈጸሙ አለማስቻል፣ ፈፃሚውን በሚፈለገዉ ደረጃ አለማብቃት፣ የኩባንያዎችን ሁለንተናዊ አቅም በሰዉ ኃይል፣ በማሽነሪና ተሽከርካሪ፣ በአሰራር ስርዓቶችና በሌሎችም መስኮች በማሳደግ በአጠቃላይ ተቋማቱ ህልዉናቸዉ አስተማማኝና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ እንዲሄድ በማድረግ ስትራቴጅክ ሆኖ ተቋማትን በመምራት ረገድ ጉድለቶች ይስተዋላሉ፡፡

### 1.2.6. የሰዉ ኃብት (Staff)

የኢንዶዉመንቱና የኩባንያዎችን የሰዉ ኃብት እ.ኤ.አ. 2020 በጀት ዘመን መጨረሻ ድረስ በቋሚ እና ኮንትራት 2,689 ለማድረስ ታቅዶ 1,373(51.06%) የደረሰ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ 577(42%) የሚሆኑት ሴቶች ናቸዉ፡፡ የሰዉ ሀብቱን የትምህርት ደረጃ ስንመለከት ሁለተኛ ዲግሪ 70(5.1%)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ 326(23.74%)፣ ዲፕሎማ 144(10.49%)፣ ሰርተፊኬት 13(0.95%)፣ እንዲሁም 12ኛ ክፍል እና በታች 820(59.72%) የትምህርት ደረጃ ያላቸዉ ናቸዉ፡፡ የሰዉ ኃብቱ፣ በቁጥር፣ በሙያ ስብጥርና በትምህርት ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እድገትና መሻሻል እያሳየ መጥቷል፡፡

በዚህም ኢንዶዉመንቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የቻለ እና በቀጣይም የሚያስፋፋቸዉንና የሚያቋቁማቸዉን ኩባንያዎች መሰረት በማድረግ ይህን ተግባር አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

### 1.2.7. ክህሎት እና አመለካከት (Skill & Attitude)

በማምርትም ሆነ አገልግሎት በመስጠት የተቋቋመ ማንኛዉም ድርጅት የተወዳዳሪነት ብቃቱን በማጎልበት ዘላቂ ሆኖ ለመቀጠልና ተልዕኮዉን ለማሳካት የሰዉ ሀብት የማይተካ ሚና አለዉ፡፡

ኢንዶዉመንቱና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች በምርትም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጣቸዉ የተሻሉ ሆነዉ በገበያ ላይ በዘላቂነት ተወዳዳሪና አትራፊ መሆን እንዲችሉ የሰዉ ሀብቱን በአመለካከትና በክህሎት ቀጣይነት ባለዉ መንገድ መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ብቁና ተወዳዳሪ የሰዉ ሀብት በተቋማቱ ዉስጥ መፍጠር ካልተቻለ ምርትና አገልግሎትን በጥራትና በቅልጥፍና በሚታሰበዉ መልኩ ማምጣት አይችልም፡፡

በመሆኑም ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የተለያዩ ስልቶችን ማለትም የአጭር፣ የረጅም ጊዜ እና የስራ ላይ ስልጠናዎችን እንዲሁም የልምድ ልዉዉጥ በማካሄድ በየደረጃዉ የሚገኘዉን የኢንዶዉመንቱን አመራርና ፈጻሚ አካል አመለካከት እና ክህሎት ለመገንባት ጥረት በመደረጉ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች ታይተዋል፡፡ በዚህም በአመራሩ በኩል ሊያሰራና ለውጤት ሊያበቃ የሚያስችል የድጋፍና ክትትል ስርዓት መዘርጋቱ፣ የስራ ግብዓቶችን ለማሟላት የሚደረገው ጥረት፣ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ረገድ የታየው ጅምር እንቅስቃሴ የሚበረታታ መሆኑ በአመራሩ ዘንድ እየታዩ ያሉ ጅምር ጥንካሬዎች ናቸዉ፡፡ በተመሳሳይ በፈጻሚዉ በኩልም በአበባ አመራረትና አያያዝ፣ በመስኖና ንፁህ መጠጥ ዉሀ ተቋማት ግንባታ ጥራት፣ ጥናትና ዲዛይን በጥራትና በፍጥነት ሰርቶ በማጠናቀቅ፣ የዉሃ ጉድጓድ ቁፋሮና የግንባታ ስራዎች ጥራት መሻሻል፣ በማሽነሪና ተሽከርካሪ ጥገና ክህሎት ማደግ በአመራሩና ፈጻሚው ዘንድ እውቀትና ክህሎት እየተሻሻለ መጥቷል፡፡

ይሁን እንጅ በአመራሩና በፈጻሚዉ ዘንድ አሁንም ድረስ የሚስተዋሉ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶች አሉ፡፡ በአመራሩ በኩል የፕሮጀክት አስተዳደር ክህሎት ጉድለት መኖሩ፣ ዉጤታማ የሚያደርጉ አዳዲስ አሰራሮችን ለመተግበር የሚያስችሉ እዉቀት ክፍተት መኖር፣ በየደረጃዉ የሚገኝ አመራር በስሩ ያለዉን ሰራተኛ ክፍተቶችን ለይቶ በመሙላት በኩል ዉስንነት መኖር፣ የገበያ ልማት ክህሎት ክፍተት፣ በየጊዜዉ የሚያጋጥሙ ዉስጣዊና ዉጫዊ ፈታናዎችን የመፍታት ክህሎትና ልምድ የዳበረ አለመሆን የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

ከፈጻሚዉ አንጻር ከላይ የተጠቀሱት ጥንካሬዎች ቢኖሩም በእቅድ የመመራት፣ ስራዎችን በተቀመጠው የጊዜ መርሃ ግብር የማጠናቀቅ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ከብክነት የፀዳ የግብዓት አጠቃቀም በመከተል፣ የተዘረጉ ስታንዳርዶችን በመተግበር የቀን ተቀን ትርፍና ኪሰራ እየተነተኑ በማስቀመጥ፣ የድርጊት መርሃ-ግብር እና የክፍያ ሰነድ ዝግጅት የሚስተዋሉ የክህሎት ክፍተቶች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም እነዚህን የክህሎት ክፍተቶች እየሞሉ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም፣ የለዉጥ መሳሪዎችን ባለቤት በመሆን አስተሳስሮ በመስራት፣ ከብክነት የጻዳና በተቆርቋሪነት ስሜት የታነጸ የሀብት አጠቃቀም በመከተል፣ ብልሹ አሰራርንና አላግባብ ተጠቃሚነትን በመጸየፍ፣ ችግሮችን ወደ ዉስጥ አይቶ በመፍታትና ከጠባቂነት ተላቆ በራስ ተነሳሽነት በመስራት ረገድ በፈጻሚዉ በኩል የሚታዩ የአመለካከት ጉድለቶች በመሆናቸዉ መታረም ይገባቸዋል፡፡

### 1.2.8. አገልግሎት አሰጣጥ (Service Delivery)

በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጸ የሰዉ ኃብት መገንባት እና ምቹ የሥራ አካባቢን መፍጠር ለላቀ አገልግሎት አሰጣጥ ቁልፍ ድርሻ አላቸዉ፡፡ ከዚህ በመነሳት አመራሩ የኢንዶውመንት ጽ/ቤቱንና የኩባንያዎችን አሰራር ግልፅነትና ተጠያቂነት የተከተለ እንዲሆንና በየተቋሙ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ለማድረግ እና የስነ-ምግባር ግንባታን በእቅዱ ዉስጥ አካቶ በትኩረት መሰራቱ በጥንካሬ የሚወሰድ ነዉ፡፡

ነገር ግን በሰራተኞች አጠቃላይ አያያዝ፣ ጥቅማጥቅም አከፋፈል፣ የሰራተኛ ቅጥርና ስንብት፣ ዋስትና አያያዝ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ አዋጆችን፣ ደንቦችን እንዲሁም በየተቋማቱ የተቀመጡ መመሪያዎችንና አሰራሮችን ጠብቆ በመስራት ረገድ ክፍተቶች በመስተዋላቸዉ የቅሬታ ምንጭ እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ የዉጭ ደንበኞችና አጋር አካላት በኩባንያዎች ሁለንተናዊ አገልግሎት አሰጣጥና አፈፃፀም ዙሪያ ያላቸውን አተያይ በግልጽ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን እድል እንዲያኙ መድኮችን በማመቻቸት በኩባንያዎች በኩል ጅምር እንቅስቃሴ አለ፡፡ በዚህም አልፎ አልፎ የሚነሱ ቅሬታዎችና ጥያቄዎች ቢኖሩም በጥቅሉ ሲወሰድ ደንበኞችና አጋር አካላት ለኢንዶዉመንቱና ለገቢ ማስገኛ ተቋማቱ የተሻለ እይታ አላቸዉ፡፡ ይሁን እንጅ የደንበኞችን እርካታ ከዚህ በተሻለ ሁኔታ

ለማረጋገጥ በሁሉም ተቋማት ደረጃ የደንበኞችን አስተያየት ለመቀበል የሚያስችሉ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የሀሳብ መስጫና የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት በመዘርጋት እንዲሁም የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ረገድ ክፍተቶች ይታያሉ፡፡

ስለሆነም በዚህ መስክ የተጀማመሩ ስራዎችን በማስቀጠል ከሙስናና ብልሹ አሰራር ተቋማቱን በተቻለ መጠን ነፃ ማድረግና ለሥነ-ምግባር ግንባታ ቅድሚያ ትኩረት መስጠት እንዲሁም ከደንበኞች ጋር በተያያዘ ወቅቱ የሚጠይቀዉን አሰራር መዘርጋትና ተጠያቂነትን በማስፈን በኩል በልዩ ትኩረት ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡

### 1.2.9. የፋይናንስ አስተዳደር

ኢንዶዉመንቱ ለአዳዲስ ኢንቨስትመንት ማቋቋሚያ እና ለነባር ኩባንያዎች ማስፋፊያ የሚሆን ፋይናንስ ከባለሀብቶች በሪኢንቨስትመንት፣ ከለጋሽ አካላት እና ከፋይናንስ ተቋማት ብድር በመዉሰድ የፋይናንስ እጥረቱን ለማሟላት ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ  ከላይ የተጠቀሱ የፋይናንስ ምንጮች በታሰበዉ ልክ ስላልተገኙ ኢንዶውመንቱ ተልዕኮዎቹን በአግባቡ ከማሳካት አኳያ የፋይናንስ እጥረት በመፈጠሩ በስትራቴጅ እቅድ ዘመኑ የታሰበዉን የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ስራዎች በሚፈለገዉ ደረጃ ማከናወን አልተቻለም፡፡ ለዚህም ኢንዶዉመንቱ በገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ያለውን የትርፍ ክፍፍል ድርሻ በወቅቱ ተከታትሎ ገቢ ባለማድረግ፣ ከለጋሽ አካላት የተጠበቀዉ ገንዘብ አለመገኘት፣ በባንኮች በኩል የሚታየዉ ቀልጣፋ ያልሆነ የብድር ሂደት በምክንያትነት ተጠቃሾች ናቸዉ፡፡ በተመሳሳይ በኩባንያዎች የመስሪያ ገንዘብ እጥረቱ በግብዓት አቅርቦትና በሌሎች የስራ እንቅስቃሴ ላይ ጫና በመፍጠሩ ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ገንብቶ ለማስረከብ ማነቆ ሁኖ ቆይቷል፡

በሌላ በኩል በኢንዶውመንቱና በኩባንያዎች የፋይናንስ አስተዳደሩን በሥርዓት ለመምራት በሁሉም ተቋማት የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን በየጊዜዉ ክፍተታቸዉ እየተፈተሸ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ የፋይናንስ አስተዳደር በጥቅል ሲታይ በገቢ አሰባሰብና ክትትል፣ በሒሳብ ምዝገባና ሪፖርት አያያዝ፣ ህጋዊ ሰነዶችን አሟልቶ በመያዝና የሒሳብ ሰነዶችን በማወራረድ፣ ልዩ ልዩ ተከፋይ ሒሳቦችን በወቅቱ አለማሳወቅና ክፍያ አለመፈጸም ላይ ባለፉት ዓመታት ጉድለቶች የታዩ በመሆኑ በቀጣይ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ከብድር ከማግኘት አንጻር ሲታይ ኩባንያዎቻችን በስትራቴጂክ ዘመኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት ከባንክ ብድር የማግኘት አቅማችዉ እየተጠናከረ መጥቷል። ለዚህም

ለኩባንያዎች የሥራ ማስኬጃያ እና ለኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ገንዘብ በብድር በመስጠት አብሮ በጋራ ለመስራት ያላቸው ፍላጎት ከጊዜ ውደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ ኩባንያዎች ከባንክ የሚያገኙትን ብድር በወቅቱ የመመለስ አቅማቸው ከዓመት ዓመት መሻሻል አሳይቷል። ይሁን እንጅ በኩባንያዎች ላይ ከፍተኛ የዕዳ ጫና የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ በባለሃብቶች በኩል ከብድር ይልቅ ሪኢንቨስትመንት ላይ ትኩረት አድርጎ በመስራት የዕዳ ጫናውን መቀነስ እንደሚገባ ያመላክታል፡፡

በአጠቃላይ በስትራቴጂ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ የነበረው የረጅም ጊዜ ብድር(Long term laibilities) መጠን ብር 154,946,436.12 የነበረ ሲሆን በ2020 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 43.3 በመቶ በመጨመር ወደ ብር 222,040,558.06 ከፍ ብሏል። ስለሆነም በቀጣይ ተቋማት ወደ ብድር ሲገቡ የብድር ጫና ዉስጥ እንዳይገቡ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ መመዘኛዎች ኩባንያዎች ያሉበትን ደረጃ መፈተሸ ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም ኢንዶዉመንቱና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች በራሳቸዉ የዉስጥ አቅም ኦዲት የሚያከናዉኑ ሲሆን በየዓመቱም በዉጭ ኦዲተር ሒሳባቸዉን ኦዲት በማስደረግ በኦዲት ግኝቱ በተሰጠዉ አስተያየት መሰረት የማስተካከያ ስራ መሰራቱ በጥንካሬ የሚወሰድ ነዉ፡፡ ተቋማቱ ከስራ እንቅስቃሴ ከሚያገኙት ሽያጭና ትርፍ ለመንግስት የሚጠበቅባቸዉን ግብር በመክፈል ግዴታቸዉን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡

### 1.3. የዉጫዊ ሁኔታ ትንተና

የዉጫዊ ሁኔታዎች በኢንዶዉመንቱና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ስትራቴጅያዊ እቅድ ትግበራ ላይ ሊኖራቸዉ የሚችለዉን መልካም አጋጣሚና ስጋት ለመለየት ትንተና ማካሄድ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የሚደረገዉ ትንተናም እንደየቅርበታቸዉ የሚታዩ በመሆኑ ለተቋማቱ ቅርብ በሆኑት ዓለማቀፋዊ፣ ሀገራዊና ክልላዊ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም ትንታኔዉ በBSC አስተቃቀድ ስልት ላይ የተቀመጠዉን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ቴክኖሎጅያዊ፣ አካባቢያዊና ህጋዊ (PESTEL) ትንተና ዘዴን በመጠቀም ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

#### 1.3.1. ፖለቲካዊ ሁኔታ

በኢኮኖሚያቸው ያደጉና በፍጥነት በማደግ ላይ ያሉ አገሮች በዓለም ፖለቲካ ላይ ያላቸው ተጽእኖ እያደገ በመምጣቱ ዓለማችን ፖለቲካዊ ብዝሃነትን እያስተናገደች ትገኛለች፡፡ በዚህ ነባራዊ የዓለም ፖለቲካዊ ሁኔታ የሀገራችን ፖለቲካዊ ግንኙነት ለንግድና ኢንቨስትመንት በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ተጽኖ ይኖረዋል፡፡ በዚህም በጋፋት ኢንዉመንት ስር የሚገኙ ኩባንያዎች እንደ አትራፊ ድርጅት ከዓለማቀፍ የፖለቲካ ሁኔታ በኢንቨስትመንትና የገበያ እንቅስቃሴያቸዉ ላይ በአንድም ይሁን በሌላ በተፅዕኖ ዉስጥ ይወድቃሉ፡፡ በዚህ ረገድ ሀገራችን ከተለያዩ ሀገሮች ጋር የሚኖራት መልካም ግንኙነት በቀጣይ ለኢንዶዉመንቱ ምርቶችና አገልግሎቶች ሰፊ የገበያ  እድል ሊፈጥር ይችላል፡፡

ከላይ የተገለጹት ምቹ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአዉሮፓ፣ በእስያና በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ሀገራት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ለመያዝ የሚያደርጉት የእርስ በርስ ሽኩቻ፣ በመካከለኛዉ ምስራቅ ሀገራት ያለዉ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እንዲሁም በጎረቤት ሀገራት በተለይም በግብጽ በኩል የሚታየዉ ጫና ለማሳረፍ የሚደረግ ሙከራ እና የመሳሰሉት ዓለማቀፋዊ የፖለቲካ ሁኔታዎች በተለይ በአበባ ገበያ መዳረሻዎች ላይ የጎላ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

በሀገር ደረጃ እየተካሄደ ያለዉ የፖለቲካ ለዉጥ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የሚስችሉ ልዩ ልዩ የማበረታቻ ስርዓቶች እንዲዘረጉ ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በክልል ደረጃም የክልሉ መንግስት ኢንዶዉመንቱንና በስሩ የተደራጁትን የገቢ ማስገኛ ተቋማትን እንደ አንድ የልማት አቅም በመቁጠር በማንኛዉም መልኩ ለመደገፍና አብሮ ለመስራት እያሳዩ ያለዉ አቋም ለተቋማቱ እድገት ሌላዉ መልካም አጋጣሚ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል በአሁኑ ሰዓት በሀገር ዉስጥ የሚታየዉ የሰላም እጦትና አለመረጋጋት፣ የከፍተኛ ፖለቲካ አመራሩ ቶሎ ቶሎ መቀያየር፣ በየደረጃዉ የሚገኝ አካል ፈጣን ዉሳኔ መስጠት አለመቻል እንዲሁም

በውቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ ምክንያት የክልሉ ተቋማት ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች የሚሆን የካፒታል በጀት አለመመደብ የመሳሰሉት ሁኔታዎች በጋፋት ደረጃ ለሚካሄዱ የእንቨስትመንት መስፋፋትና በኩባንያዎች ለሚደረገዉ የስራ እንቅስቃሴ ፈተናዎች ይሆናሉ፡፡ በተመሳሳይ አሁንም ድረስ በሀገራችን በተለይም በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚታየዉ ሙስናና ብልሹ አሰራር በኢንዶዉመንቱ የስራ እንቅስቃሴ ላይ ስጋት ሆኖ ሊቀጥል ይችላል፡፡

## 1.3.2. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ዓለም በተወሰኑ ሀገራት ስትመራ ከነበረበት የኢኮኖሚ የበላይነት ወጥታ ኢኮኖሚያቸው በፍጥነት እያደጉ ባሉ አገሮች ጭምር ተጽእኖ እያረፈባት መጥቷል፡፡ ይህም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገራት የተለያዩ አማራጮችንና ልምዶችን በኢንቨስትመንት፣ በቴክኖሎጂ፣ በእውቀትና ክህሎት ግንባታ እንዲሁም በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር ለመፍጠር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ ኢንዶዉመንቱም ከዚህ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስሩን ለማጠናከርና የሚገጥሙ መሰናክሎችን በጋራ ለመቋቋም የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የትብብር ስምምነቶች መፈረማቸዉ ለኢንቨስትመንትና ንግድ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህም ኢንዶዉመንቱ ከዉጭ ባለሀብቶች ጋር በሽርክና ኢንቨስትመንትን እና የገበያ መዳረሻዎችን ለማስፋፋት የሚችልበት እድል ይኖረዋል፡፡

ይሁንና በዓለም አቀፍ ደረጃ በየጊዜዉ የሚፈጠረው የኢኮኖሚ አለመረጋጋት፣ በኃያላን ሀገራት መካከል እየታየ ያለዉ የንግድ ጦርነት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጉ ህጎች፣ ስምምነቶች እና የንግድ ግንኙነቶች ሚዛናዊ አለመሆን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተዉ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የንግድ እንቅስቃሴ መስተጓጎል የመሳሰሉት በዚህ የሚቀጥሉ ከሆነ በንግድና ኢንቨስትመንት ላይ በቀጣይም አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠራቸዉ አይቀርም፡፡

በተመሳሳይ ሀገሪቱ ባለፉት ዓመታት ሁለት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶችን በመተግበር የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ የተቻለ ሲሆን በዚህም ትልልቅ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች (የመንገድ፣ የኃይል አቅርቦት፣ የቴሌኮም ወዘተ) መስፋፋት፣ በተመረጡ ቦታዎች ላይ ኢንዱስትሪዉን ለማሳደግ የተገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዲሁም በኮንስትራክሽን ዘርፍ እያደገ የመጣዉ የመልማት ፍላጎትና የተሰጠዉ ትኩረት ኢንዶዉመንቱ በተሰማራባቸዉ የስራ መስኮች ሰፊ የገበያ እድል የሚፈጥር መሆኑ፣ በክልላችን በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ኢንቨስትመንት እየተሰማሩ ያሉ ባለሀብቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣ በርካታ የኢንቨስትመንት አማራጮችና ጸጋዎች መኖራቸዉ፣ ለአምራች ዘርፉ የብድር አቅርቦት መኖር ለኢንዶዉመንቱ ኩባንያዎች የስራ እንቅስቃሴ

አጋዥ ሁኔታዎች ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡ በቀጣይም በሀገር ደረጃ እስካሁን የተመዘገቡ ዉጤቶችን አጠናክሮ ሊያስቀጥል የሚችል ሀገራዊ የአስር ዓመት መሪ እቅድ በማዘጋጀት እና በመተግበር የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ከላይ የተጠቀሱ አበረታች ሁኔታዎች ቢኖሩም በተቃራኒዉ አሉታዊ ተጽኖ የሚያሳድሩ ስጋቶች መኖራቸዉ አልቀረም፡፡ ከእነዚህም መካከል የዉጭ ምንዛሬ በየጊዜዉ ማደግና የምንዛሬ አቅርቦት እጥረት ከዉጭ ሀገር በሚገቡ ግብዓቶች ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ማሳረፉ፣ የኢንቨስትመንት ወጭ በየጊዜዉ መጨመር፣ ጤናማ ያልሆነ የግብይት ስርዓት መስፈን፣ በየጊዜዉ የሚከሰተዉ የዋጋ ግሽበት፣ መሰረተ-ልማት በበቂ ሁኔታ አለመሟላት፣ የኃይል አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለመኖር እንዲሁም የአበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት ለኢንቨስትመንትና ለመስሪያ ብድር ለማቅረብ የብድር ፖሊሲያቸዉ ዉጣ ዉረድ የበዛበት መሆኑ የመሳሰሉት ማነቆዎች እስካልተፈቱ ድረስ በኢንዶዉመንቱ እና በገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ቀጣይ  እንቅስቃሴ ላይ ተጽኖ ይኖራቸዋል፡፡

### 1.3.3. ማህበራዊ ሁኔታ

በሀገራችንም ሆነ በክልላችን በህብረተሰቡ ዘንድ ሰርቶ ለመለወጥና ኑሮውን ለማሻሻል  ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣና መንግስትም ይህንን ለመደገፍ የሚተጋበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ አንጻር በመንግስት በኩል የትምህርትና የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የጤና፣ የአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች መስፋፋት በተለያዩ ሙያዎች የሰለጠነ፣ ጤነኛና አምራች የህብረተሰብ ክፍል ለመፍጠር የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቂ አምራች የሰዉ ኃይል መኖር፣ የህብረተሰቡ አብሮ የመኖርና የመረዳዳት ባህል፤ ሰርቶ የመለወጥ ፍላጎት፤ በየአካባቢው ለልማት አጋዥ የሚሆኑ አደረጃጀቶች ለምሳሌ የወጣቶች፤ የሴቶች እንዲሁም የህብረት ስራ ማህበራትና ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች (እቁብ ፤ እድር …ወዘተ) መኖራቸው  የኢንዶውመንቱ  የገቢ ማስገኛ ተቋማት ለሚያካሂዱት ኢንቨስትመንት እንደ ምቹ ሁኔታ የሚታይ ነው፡፡

ይሁን እንጅ የህብረተሰቡ የስራ ባህል በሚፈለገው ደረጃ አለማደግ፤ የጊዜ አጠቃቀም ባህሉና ግንዛቤ አናሳ መሆን፤ ወጣቱ በተለያዩ መጤ ባህሎች ሰለባ መሆንና የውጭ ባህል ወረራ ተጠቂ መሆን፤ አደንዛዥ እጽ መስፋፋት፤ በሃገር ሰርቶ ከመለወጥ ይልቅ ስደትን መምረጥ፤ ብልሹ አሰራርና ሙስናን ከመታገል አኳያ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ንቃተ-ህሊና በሚፈለገው ደረጃ የደረሰ አለመሆን፤ በጣና ፍሎራ አበባ እርሻ አካባቢ ያሉ አርሶ አደሮች በመሬት ካሳዉ ላይ ቅሬታ የመያዝና በአሁኑ ሰዓት እየታየ ካለዉ ፓለቲካዊ አለመረጋጋት እና የሰላም እጦት ጋር ተያይዞ አጋጣሚዉን ተጠቅሞ የአበባ እርሻዉን በማዉደም መሬቱን በጉልበት ለመንጠቅ እየታየ ያለ አዝማሚያ፤ የሃይማኖታዊ

በዓላት አከባበር፣ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስርጭት መስፋፋት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየጨመረ የመጣው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሃገር፣ በክልል ብሎም በኢንዶውመንቱና ኩባንያዎቹ የስራ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖራቸዋል፡፡

### 1.3.4. ቴክኖሎጅያዊ ሁኔታ

በአለንበት ዘመን በቴክኖሎጅ በመታገዝ ምርትና አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ ፈጣን የመገናኛ አውታር በመዘርጋት በመረጃ ልውውጥና በንግድ እንቅስቃሴ ትስስር በመፍጠር ዓለም ወደ አንድ መንደር እየተለወጠች ትገኛለች፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ዘርፉን ከምርምርና ከትምህርት ተቋማት ጋር በማስተሳሰር ተገቢዉን የእዉቀትና የቴክኖሎጅ ሽግግር ለማምጣት በመንግስት በኩል እየተደረገ ያለዉ ጥረት እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ የሚወሰድ ነዉ፡፡

ስለሆነም በቴክኖሎጅ መስፋፋት አገራችንም ሆነ ኢንዶውመንቱና ኩባንያዎቹ እንደ ተቋም ተጠቃሚ የሚሆኑበት እድል ሰፊ እንደሚሆን ይታሰባል፡፡ ከዚህ አንጻር የማያቋርጥ የቴክኖሎጅ እድገት መኖር፣ በሀገራችን ለሳይንስና ቴክኖሎጅ መስፋፋትና መጠናከር የተሰጠዉ ልዩ ትኩረት፣ የቴክኖሎጅ አቅራቢ ተቋማት እየተስፋፉ መምጣት፣ ቴክኖሎጅን አላምዶ ለመጠቀም የሚቻልበት እድል መኖሩና መሰል ጉዳዮች ሥራን በተቀላጠፈ ሁኔታ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ይሁን እንጅ ቴክኖሎጅን ለመጠቀም የግንዛቤና እውቀት ውስንነት መኖር፣ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አገራዊ የእዉቀት ዉስንነት መኖር፣ የቴክኖሎጅ በፍጥነት መለዋወጥና ዋጋ መናር፣ የኃይልና ቴሌኮም አገልግሎቶች መቆራረጥ፣ መሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታ ባልተስፋፋባቸዉ አካባቢዎች ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ ስራን ለማሳለጥ ዉስንነት የሚታይ በመሆኑ በቀጣይ ስራዎች ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ ይችላሉ፡፡

### 1.3.5. አካባቢያዊ ሁኔታ

በዚህ ዘመን በዓለማችን እየታዩ ካሉ ችግሮች መካከል አንዱ የአየር ንብረት መዛባት ነዉ፡፡ ይህም በዋናነት የኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና የካርበን ልቀት መጨመር ሲሆን በዚህም ሳቢያ፣ የኦዞን መሳሳትና መሸንቆር፣ የዓለም ሙቀት መጠን መጨመር፣ የበረዶ ግግር መቅለጣና የባህር ወለል ከፍታ ማደግ፣ የጎርፍ አደጋ መከሰት የመሳሰሉት የተፈጥሮ አደጋዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመሆኑም የአካባቢ ጉዳይ የዓለም አጀንዳ እየሆነ የመጣ ሲሆን በአገራችንም ሆነ በክልላችን የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጅ ማዕከል በማድረግ ሰፊ የሆነ የአካባቢ ልማትና የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተሠሩ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ማንኛውም የልማት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ተገቢው የአካባቢ ተጽኖ እየተገመገመ የመሥራት ባህል እየተሻሻለ መምጣቱ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀምና ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ በሚያስችል አግባብ ለመሥራት ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል፡፡

እንደ ሃገር እየተከተልን ያለነዉ የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ኢንዶዉመንቱ ይዞት ከተነሳው ዓላማ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ለትግበራዉ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ከአበባ ምርት ሂደት ጋር ተያይዞ የምንጠቀማቸዉ ኬሚካሎችና ማዳበሪያዎች በአካባቢ ላይ የጎላ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩ ለማድረግ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተቀርጸዉ ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሰሩ ተቋማት በተሰማሩባቸዉ የስራ ዘርፎች ከአካባቢ ልማትና ጥበቃ ህጎች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑና በአካባቢ ላይ የጎላ ተጽዕኖ እንዳያስከትሉ ለማድረግ በትኩረት ተይዘዉ እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል በዓለም ላይ ያለው ፍትሃዊ ያልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣ ተፈጥሮን ግምት ውስጥ ያላስገባ የልማት እንቅስቃሴ፣ መጠነ ሰፊ የካርቦን ልቀት ተፅዕኖ ለምድራችን ከምንጊዜውም በላይ አስከፊ ደረጃ ላይ መገኘቱ አገራችን ከፍተኛ ስጋት ተጋርጦባታል፡፡ በመሆኑም የአየር ንብረት መዛባት፣ ለተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ተጋላጭነት መጨመር፣ የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውሃ መጠን እየቀነሰ መምጣት፣ የተፈጥሮ ሃብት መቀነስ፣ የዝናብ መጠንና ስርጭት ወቅት መዛባት፣ የበርሃማነት መስፋፋት ወዘተ… ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ማንኛዉንም ልማት ለማካሄድ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በኢንዶዉመንቱ ስር ያሉ ተቋማት የሚያከሂዱቸዉ ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ የሚደርሱትን እንዲሁም አካባቢዉ ፕሮጀክቶች ላይ የሚያሳድረዉን ተጽኖ ከመከላከልና ከመቀነስ አኳያ ቀድሞ በዲዛይንና በእቅድ ከማካተት ባለፈ በትግበራ ወቅትም ተገቢዉን ክትትልና የእርምት እርምጃ መዉስድ ይገባል፡፡

### 1.3.6. ህጋዊ ሁኔታ

ህጋዊ ሁኔታዎች በአለም አቀፍ የንግድ ልውውጥና ግንኙነቶች ላይ ገኘር ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ተፅዕኖዎች ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ከዚህ አኳያ አገራችን ከሌሎች አገሮች ጋር የምታደርጋቸው ስምምነቶችም ሆነ ሌሎች ህጎች በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረቱ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ስምምነቶች መኖራቸዉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ከሃገራችን አኳያም ኢንቨስትመንትን፣ የበጎ አድራጎት ስራዎችን እና አጠቃላይ ልማትን ለማካሄድ የሚያስችሉ ልዩ ልዩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መኖራቸዉ እንዲሁም በክልል ደረጃ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ መገባቱ እንደ መልካም አጋጣሚ ይወሰዳል፡፡ በዚህም ለኢንዶዉመንቱም ሆነ ለሌሎች ተመሳሳይ የልማት ድርጅቶችና የግል ባለሃብቱ የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መጠናከርና መስፋፋት አቅም እየፈጠረ ይገኛል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ምቹ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተወሰደዉን የዉጭ ምንዛሬ ተመን ማስተካከያ ተከትሎ የግንባታ ግብዓቶች አቅርቦት ስርዓት መዛባት ከመከሰቱም ባሻገር በግብዓቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ መከሰቱና ይህን ነባራዊ ሀቅ ሊለዉጥ የሚችል ክልላዊ የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ፣ በሀገር ደረጃ የኤክስፖርት ሽያጭን በዱቤ የሚፈቅድ ህጋዊ ማዕቀፍ ባለመኖሩ የአበባ ምርትን በመካከለኛዉ ምስራቅ ገበያ ዉስጥ በስፋት ለማስገባት ማነቆ መሆኑ፣ የጉልበት ሠራተኞች የጡረታ ዋስትና አዋጅ ተቋማት ላይ ተፅዕኖ እያሳረፉ በመሆኑ በቀጣይ በጋፋት ኢንዶዉመንት ኩባንያዎች እንቅስቃሴና ትርፋማነት ላይ ስጋት ማሳደራቸዉ አይቀርም፡፡

## 1.4. የጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚና ስጋት ትንተና ማጠቃለያ

| | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|
| ውስጣዊ ሁኔታ | **1. ስትራቴጂ (Strategy)** | |
| | ✓ ኢንዶውመቱና ኩባንያዎቹ በስትራቴጅክ እቅድ እንዲመሩ መደረጉ፣<br>✓ ስትራቴጅው ከኢንዶዉመንቱ ወደ ኩባንያዎች ተሸንሽኖ (Cascade) መውረድ መቻሉ፤<br>✓ እንደ ኢንዶዉመንት በየዓመቱ ዕቅድ በጋራ መድረክ እየተገመገመ ወደ ትግበራ እንዲገባ መደረጉ፤<br>✓ ዓመታዊ ዕቅድን በየአመቱ እንዲሁም አፈጻፀምን ደግሞ በየሩብ ዓመቱ ለስራ አመራር ቦርዱ እያቀረቡ በማስገምገምና በማፀደቅ፣የስራ አቅጣጫዎችን በመያዝ ወደ ስራ መገባቱ፤<br>✓ በኢንዶዉመንት ደረጃ እቅድና አፈጻፀም በየሩብ ዓመቱ በጋራ መድረክ እየገመገሙ መሄድ መቻሉ፤<br>✓ ገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ከኢንዶዉመንት ጽ/ቤቱ ጋር ወርሃዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን እየገመገሙ መሄድ መቻሉ፤ | ✓ ስትራቴጅክ እቅዱን በየጊዜው እየፈተሹ መከለስ አለመቻልና አመታዊ እቅዶችን ከስትራቴጅው ጋር ሙሉ በሙሉ ማስተሳሰር አለመቻል፤<br>✓ የተዘጋጀዉን ዕቅድ ለሥራ ክፍሎችና ለፈፃሚዎች በተገቢው መንገድ ማውረድ(Cascading) አለመቻል፤<br>✓ የባላንስድ ስኮር ካርድ አውቶሜሽን ስርዓት አለመዘርጋቱ፣<br>✓ ስትራቴጅያዊ እርምጃዎችን(Strategic Initiatives) በተሟላ መንገድ መዘርጋትና መተግበር አለመቻል፤<br>✓ ተቋማት ዕቅዱን ውጤታማ በሆነ መልኩ የመፈፀም ክፍተት የታየባቸዉ መሆኑ፤<br>✓ እቅዱን እስከ ግለሰብ ፈጻሚ ድረስ ማዉረድና በአፈጻጸም ዉጤት መሰረት ከሽልማት ጋር ማስተሳሰር አለመቻል፣ |
| | **2. አደረጃጀት (structure)** | |
| | ✓ በኢንዶውመንቱ በተለያዩ ጊዜያት ከወቅታዊ ሁኔታዉ ጋር ሊሄድ የሚችል የሰው ኃይል አደረጃጀት መዋቅር ማሻሻያዎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ መደረጋቸው፤<br>✓ የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ውጤታማ የሚያደርጋቸውን ድርጅታዊ መዋቅር ማሻሻያዎችን አዘጋጅተውና በባለአክስዮኖች አፀድቀው ስራ ላይ እንዲውል ማድረጋቸዉ፤<br>✓ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመዳሰስ ለኩባንያዎች የሚያስፈልጉ የሰው ሃይል መዋቅርና ጥቅማጥቅም ሁኔታዎችን እያሻሻሉ ለመሄድ የተደረገው ጥረት የሚበረታታ መሆኑ፤ | ✓ ለኢንዶዉመንቱ ለተልእኮ ስኬት አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶችን በበጀት እጥረትና ተያያዥ ምክንያቶች የሰው ኃብት አለማሟላት፣<br>✓ የገበያ ልማት ስራዎችን በባለቤትነት ይዞ ሊመራ የሚችል የተጠናከረ አደረጃጀት በገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ላይ መፍጠር አለመቻል፤<br>✓ በአበባ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ዘርፍ ቴክኒካል አማካሪ እንዲኖር የሚያስችል አደረጃጀት አለመኖር፤ |

| | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|
| | ✓ የተቋማቱ የሰው ኃብት ውጤታማ እንዲሆን ሊያግዙ የሚችሉ ልዩ ልዩ ንኡስ አደረጃጀቶችን በማደራጀት ወደ ስራ እንዲገቡ መደረጉ፤ | |
| | **3. አሰራር ሥርዓት** (system) | |
| | ✓ በየተቋሙ የሚያስፈልጉትን የአሰራር ስርዓቶች በመለየት በአዳዲስ መዘርጋታቸው፣<br>✓ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸዉን የአሰራር ስርዓቶች እየፈተሹ በየጊዜው ማሻሻያዎች መደረጋቸው፤<br>✓ የስራ እና የግብዓት ስታንዳርዶችን በመዘርጋት ወደ ተግባር መግባቱ፣<br>✓ እንደ ኢንዶዉመንት ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መዘርጋቱ፣<br>✓ በኢንዶዉመንት ደረጃ የለውጥ መሳሪያዎችን በመለየት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩ፣ | ✓ በየተቋሙ የሚያስፈልጉ የአሰራር ስርዓቶችን ከማሟላት አኳያ አሁንም ድረስ ጉድለት መኖሩ፣<br>✓ የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን በተሟላ ሁኔታ አለመተግበርና በአፈጻጸም ሂደት መሸራረፍ፤<br>✓ የስራና የግብአት አጠቃቀም ስታንዳርዶችን በቁርጠኝነት ተግብሮ ብክነትንና ብልሹ አሰራሮችን አሟልቶ አለመከላከል፣<br>✓ የለውጥ መሳሪያዎችን ከመተግበር አኳያ አመራሩ በትኩረት አለመያዝና ፈፀሚው በአመለካከት ባለቤት አለመሆን፣<br>✓ የመረጃና ሪፖርት ቅብብሎሽ ስርዓቱ የተደራጀና የተቀናጀ አለመሆን፣ |
| | **4. የጋራ እሴቶች** (Shared value) | |
| | ✓ በአመራርና ፈፃሚ አካላት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚመሰረትባቸዉ መርሆዎችና በተቋሙ ዉስጥ የሰረጹ እምነቶች፣ አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን የሚያንጸባርቁ እሴቶችን በመቅረፅ ወደ ስራ መግባቱ፤<br>✓ የኢንዶዉመንቱን እሴቶች ወደ ተግባር ለመቀየር ከተቋማት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር እየዳበረ የመጣ መሆኑ፤<br>✓ የጋራ ተቋማዊ አስተሳሰብ ለመፍጠር የሚያስችሉ እና የሰራተኞችን የስራ መስተጋብር ሊያሳድጉ የሚችሉ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች መፈጠራቸዉ፡፡ (የመረዳጃ ማኅበር፣ የሰራተኞች ብድርና ቁጠባ ማኅበር) | ✓ እንደኢንዶዉመንት በአመራሩና በፈጻሚዉ ዘንድ በሚፈለገው ደረጃ ሰርፀው የዕለት ተዕለት የሥራ ባህልና መመሪያ ሆነው ማገልገል አለመቻል፤ |

| | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|
| | **5. የአመራር ሁኔታ (Leadership Style)** | |
| | ✓ የኢንዶዉመንቱ አመራር ዕቅድን አሳታፊ በሆነ አግባብ እንዲዘጋጅ የማድረግና ሥራዎችን ከፋፍሎ በመስጠትና በጋራ እየገመገሙ የመምራት አቅም እየተሻሻለ መምጣት፣<br>✓ የፈፃሚ ኃይሉን ክፍተት የመለየትና ጉድለቱን በመሙላት በኩል የአመራር ልምድ እያዳበረ መምጣት፣<br>✓ ለውጤት ሊያበቃ የሚያስችል የድጋፍና ክትትል ስርዓት መዘርጋቱ፣<br>✓ የስራ ግብዓቶችን አቅም በፈቀደ መልኩ ማሟላት መቻሉ፤<br>✓ ተቋማቱ የአሰራር ስርዓትን መዘርጋት፣ ማሻሻልና መተግበር መቻሉ፣<br>✓ ኢንዶዉመንቱ የተቋቋመበትን ዓላማ እና ክልላዊ ተልዕኮ እንዲያሳካ በአመራሩ ዘንድ የተያዘዉ ቁርጠኝነት፣ | ✓ ዉሳኔ በሚያስፈልጋቸዉ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ በቁርጠኝነት አለመወሰን፣<br>✓ የለዉጥ መሳሪያዎችን በትኩረት ይዞ አለመምራት፣<br>✓ የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱን ችግር ፈች በማድረግ ተግባራት በወጣላቸዉ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ተሟልተዉ እንዲፈጸሙ አለመቻል፣<br>✓ በኩባንያ አመራር ደረጃ ስራዎችን በተገቢው ሁኔታ አደራጅቶ በበቂ ቅድመ ዝግጅት መምራት ላይ ውስንነት መኖሩ፣<br>✓ ፈፃሚውን በሚፈለገዉ ደረጃ አለማብቃት፣<br>✓ የኩባንያዎችን ሁለንተናዊ አቅም በማሳደግ ህልዉናቸዉ አስተማማኝና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ እንዲሄድ ለማድረግ ስትራቴጅክ ሆኖ መምራት አለመቻል፤<br>✓ በየደረጃዉ ተኪ አመራር ከማፍራት አኳያ ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ አለመሆን፤<br>✓ ኪራይ ሰብሳቢነትን ቀድሞ ከመከላከል አኳያ የግንዛቤ ፈጠራ ስራዉም ሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ላይ ውስንነት የሚታይበት መሆኑ፤<br>✓ የስራ ግብዓቶችን ቀድሞ በማቀድ አደራጅቶና በቅንጅት በመስራት ስራ በማያስቆሙበት መንገድ ማሟላት አለመቻል፤ |
| | **6. የሰው ሐብት (Staff)** | |
| | ✓ የሰው ሃይሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣትና በኢንዶዉመንት ደረጃ በአመዛኙ ወጣት የሰው ኃይል መኖሩ፣<br>✓ ብቃት ያላቸው ሙያተኞችን ለመሳብ እየተደረገ ያለው ጥረት፣<br>✓ የሰው ሃብቱ በትምህርት ደረጃ እና ልምድ እየተሻሻለ መምጣቱ፤<br>✓ የሰራተኞችን ጥቅማጥቅሞች ለመምራት የሚያስችሉ ተቋማዊ መመሪያዎች መኖር፣<br>✓ አዲስ ለሚቀጠሩ ሰራተኞች የግንዛቤ ፈጠራ ፕሮግራም (Induction Program) ተመቻችቶ አመለካከትን ለመቅረጽ ጥረት ሲደረግ መቆየቱ፡፡ | ✓ በየዘርፉ የሰለጠነና ልምድ ያካበተ የባለሙያ እጥረት ያለ መሆኑ፤<br>✓ የሰራተኛ ፍልሰት መኖር፣<br>✓ የሰራተኞች የባለቤትነት ስሜት በሚፈለገው ደረጃ ላይ ያልደረሰ መሆኑ፣<br>✓ የምርትና የአገልግሎት ጥራትን ጠብቆ ከመሄድ ይልቅ በሰራተኛው ዘንድ አልፎ አልፎ የሚታየው ግዴለሽነት፣<br>✓ ግብዓቶችን በቁጠባና በጥንቃቄ ከመጠቀም ይልቅ የማባከን ችግር መኖሩ፤ |

| | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|
| | **7. ክህሎትእና አመለካከት (Skill & Attitude)** | |
| | ✓ ክህሎትን ሊያዳብሩ የሚችሉ የሀገር ዉስጥና የዉጭ ሀገር የልምድ ልዉዉጥ ፕሮግራሞች፣ የእርስ በእርስ የመማማሪያ አደረጃጀቶችን በመፍጠር እና በሌሎችም አግባቦች የሠራተኛዉን እዉቀትና ክህሎት የመገንባት ስራ መሰራቱ፤<br>✓ በስራ ላይ ስልጠናዎችና ክትትልና ድጋፍ በመነሳት ግምገማዊ ስልጠናዎችን በመስጠት የክህሎትና የአመለካከት ክፍተቶችን ለመሙላት መቻሉ፣<br>✓ የረጅም እና በልዩ ልዩ አጫጭር የሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት የክህሎትና የአመለካከት ችግሮችን የመቅረፍ ስራዎች መሰራታቸው፣<br>✓ በፈጻሚዉ በኩል በአበባ አመራረትና አያያዝ፣ በመስኖና ንፁህ መጠጥ ዉሀ ተቋማት ግንባታ፣ በጥናትና ዲዛይን በጥራትና በፍጥነት ሰርቶ በማጠናቀቅ፣ በዉሃ ጉድጓድ ቁፋሮና የግንባታ ስራዎች በማሽነሪና ተሽከርካሪ ጥገና ስራዎች ላይ እውቀትና ክህሎት እየተሻሻለ መምጣት፣<br>✓ ፈፃሚው ትርፍ ጊዜውን ጭምር በመጠቀም ተልዕኮውን ለመወጣት የሚያሳየው ተነሳሽነት መሻሻሉ፤ | ✓ በአመራሩ በኩል የሚያጋጥሙ ዉስጣዊና ዉጫዊ ፈተናዎችን የመፍታት ክህሎትና ልምድ የዳበረ አለመሆን፤<br>✓ አመራሩ በገበያ ዉድድር መርህ ላይ ተመስርቶ ቢዝነስን ለመምራት የሚያስችል የአመለካከትና ክህሎት ክፍተት ያለበት መሆኑ፣<br>✓ በእቅድ በመመራት፣ ስራዎችን በተቀመጠው የጊዜ መርሃ ግብር ማጠናቀቅ አለመቻል፣<br>✓ ወጪ ቆጣቢ እና ከብክነት የፀዳ የግብዓት አጠቃቀም ስልት መከተል አለመቻል፣<br>✓ የተዘርጉ ስታንዳርዶችን በመተግበር የቀን ተቀን ትርፍና ኪሰራ እየተነተኑ ማስቀመጥ አለመቻል፣<br>✓ የድርጊት መርሃ-ግብር እና የክፍያ ሰነድ ዝግጅት የክህሎት ክፍተት መኖሩ፣<br>✓ የለዉጥ መሳሪያዎችን ባለቤት በመሆን አስተሳስሮ መስራት አለመቻል፣<br>✓ ከብክነት የጸዳና በተቆርቋሪነት ስሜት የታነጸ የሀብት አጠቃቀም አለመከተል፣<br>✓ ችግሮችን ወደ ዉስጥ አይቶ በመፍታትና ከጠባቂነት ተላቆ በራስ ተነሳሽነት መስራት አለመቻል፤ |

| | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|
| **8. አገልግሎት አሰጣጥ (Service Delivery)** | | |
| | ✓ አመራሩ የመልካም አስተዳደርና እና ለስነ-ምግባር ግንባታ ስራዎችን በእቅዱ ዉስጥ አካቶ በትኩረት በመያዝ ለመስራት የሚያደርገው እንቅስቃሴ፤<br>✓ የዉጭ ደንበኞችና አጋር አካላት በኩባንያዎች ሁለንተናዊ አገልግሎት አሰጣጥና አፈፃፀም ዙሪያ ያላቸውን አተያይ በግልጽ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን እድል ማመቻቸት መጀመሩ፤<br>✓ ሰራተኛው ለደንበኞች ያለው ክብር እና አያያዝ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤ | ✓ በሰራተኞች አጠቃላይ አያያዝ፣ ጥቅማጥቅም አከፋፈል፣ የሰራተኛ ቅጥርና ስንብት፣ ዋስትና አያያዝ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ አዋጆችን፣ ደንቦችን እንዲሁም በየተቋማቱ የተቀመጡ መመሪያዎችንና አሰራሮችን ትኩረት ሰጥቶ ባለመተግበር የቅሬታ ምንጭ መሆኑ፤<br>✓ የደንበኞችን እርካታ የበለጠ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መድረኮችን በማዘጋጀት ተግባራዊ አለማድረግ፣<br>✓ የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ዘላቂ በሆነ መንገድ መዘርጋትና  መተግበር አለመቻል፤<br>✓ ተከታታይነት ባለው አግባብ የደንበኞች እርካታ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ አለመቻል፤<br>✓ የደንበኛ እርካታ ዳሰሳ ጥናት በየጊዜው ወይም በየዓመቱ  ማድረግ አለመቻል፡፡ |
| **9. የፋይናንስ አስተዳደር** | | |
| | ✓ ለአዳዲስ ኢንቨስትመንት ማቋቋሚያ እና ለነባር ኩባንያዎች ማስፋፊያ የሚሆን ፋይናንስ ከባለሀብቶች በሪኢንቨስትመንት፣ ከለጋሽ አካላት እና ከፋይናንስ ተቋማት ብድር ለማሟላት የተደረገው ጥረት፤<br>✓ ኩባንያዎቻችን  ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላት ከባንክ ብድር የማግኘት አቅማችዉ እየተጠናከረ መምጣት፣<br>✓ ኩባንያዎቻችን ከባንክ የሚያገኙትን ብድር በወቅቱ የመመለስ አቅማቸው  ከዓመት ዓመት መሻሻል ያሳየ መሆኑ፣ | ✓ ከተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች ገቢ ለማሰባሰብ በታቀደው ልክ መፈፀም ባለመቻሉ የፋይናንስ እጥረት ማጋጠሙ፣<br>✓ ኢንዶዉመንቱ በገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ያለውን የትርፍ ክፍፍል ድርሻ በወቅቱ ተከታትሎ ገቢ አለማድረግ፣<br>✓ የመስሪያ ገንዘብ እጥረቱን መቅረፍ ባለመቻል በኩባንያዎች በኩል ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ገንብቶ ማስረከብ አለመቻል፤<br>✓ በገቢ አሰባሰብና ክትትል፣ በሒሳብ ምዝገባና ሪፖርት አያያዝ፣ ህጋዊ ሰነዶችን አሟልቶ በመያዝና የሒሳብ ሰነዶችን በማወራረድ ወዘተ ከስህተት የፀዳ አለመሆን፤ |

| | መልካም አጋጣሚዎች | ሥጋቶች |
|---|---|---|
| | 1. ፖለቲካዊና ሁኔታዎች | |
| ውጫዊ ሁኔታዎች | ✓ ዓለማችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ፖለቲካዊ ብዝሃነትን በፍጥነት እያስተናገደች በመምጣቷ በዚህ ነባራዊ የዓለም ፖለቲካዊ ለንግድና ኢንቨስትመንትን ከተለያዩ ሀገራት ጋር ለማካሄድ ሰፊ እድል የሚፈጥር መሆኑ፣<br>✓ ሀገራችን ከተለያዩ ሀገሮች ጋር ያላት መልካም ግንኙነት በቀጣይ ለኢንዶዉመንቱ ምርቶችና አገልግሎቶች ሰፊ የገበያ እድል ሊፈጥር የሚችል መሆኑ፤<br>✓ በሀገር ደረጃ እየተካሄደ ያለዉ የፖለቲካ ለዉጥ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የሚስችሉ ልዩ ልዩ የማበረታቻ ስርዓቶች እንዲዘረጉ ምቹ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑ፤<br>✓ በአገራችን ሊያሰራ የሚችል ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና ስትራቴጅ መኖሩና ከዚህ ጋር ተያይዞ ኢንቨስትመንትን ሊደግፉና ሊያበረታቱ የሚችሉ ተቋማት በየዘርፉ መደራጀታቸዉ፤<br>✓ የክልሉ መንግስት ኢንዶዉመንቱንና በስሩ የተደራጁትን የገቢ ማስገኛ ተቋማትን እንደ አንድ የልማት አቅም በመቁጠር በማንኛዉም መልኩ ለመደገፍና አብሮ ለመስራት እያሳዩ ያለዉ አቋም፤<br>✓ በክልል ደረጃ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ ተቀርፆ ወደ ስራ መገባቱ፣<br>✓ በዓለም አገራት ዘንድ የአገራችን ተሰሚነት እያደገና ገጽታዋ እየተቀየረ መምጣቱ ከውጭ ባለሃብቶች ጋር በሽርክና ለመስራት የሚቻልበት እድል እየሰፋ መምጣቱ፣<br>✓ እንደሃገር የወጣዉ የበጎ አድራጎት ማኀበራት መመዝገቢያና ማስተዳደሪያ አዋጅ ኢንዶዉመንቱንና መሰል የልማት ድርጅቶችን ለበለጠ ውጤታማነት የሚያግዝ መሆኑ፤ | ✓ በአዉሮፓ፣ በእስያና በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ሀገራት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ለመያዝ የሚያደርጉት የእርስ በርስ ሽኩቻ፣<br>✓ በመካከለኛዉ ምስራቅ ሀገራት ያለዉ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት በተለይ በአበባ ገበያ ላይ ስጋት መሆኑ፤<br>✓ በጎረቤት ሀገራት በተለይም በግብጽ በኩል የሚታየዉ ጫና ለማሳረፍ የሚደረግ ሙከራ በአበባ ገበያ መዳረሻዎች ላይ የጎላ ተጽኖ ሊያሳድር የሚቸል መሆኑ፣<br>✓ በሀገር ዉስጥ የሚታየዉ የሰላም እጦትና አለመረጋጋት፣<br>✓ የከፍተኛ ፖለቲካ አመራሩ ቶሎ ቶሎ መቀያየር፣<br>✓ በየደረጃዉ የሚገኝ አካል ፈጣን ዉሳኔ መስጠት አለመቻል፤<br>✓ በተመሳሳይ አሁንም ድረስ በሀገራችን የሚታየዉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲሁም ሙስናና ብልሹ አሰራር መኖሩ፤ |

| | መልካም አጋጣሚዎች | ሥጋቶች |
|---|---|---|
| | **2. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች** | |
| | ✓ ዓለም በተወሰኑ ሀገራት ስትመራ ከነበረበት የኢኮኖሚ የበላይነት ስርዓት ወጥቶ ኢኮኖሚያቸው በፍጥነት እያደጉ ያሉ አገሮች ጭምር ጉልህ ተጽእኖ ፈጣሪ እየሆኑ መምጣት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገራት የተለያዩ አማራጮችንና ልምዶችን በኢንቨስትመንት፣ በቴክኖሎጂ፣ በእውቀትና ክህሎት ግንባታ እንዲሁም በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ትስስር ለመፍጠር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ፤<br>✓ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትስስሩን ለማጠናከርና የተለያዩ የትብብር ስምምነቶች መፈረማቸዉ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ ኢንዶዉመንቱ ከዉጭ ባለሀብቶች ጋር በሽርክና መስራት የሚቻልበት እድል ሰፊ መሆኑ፤<br>✓ በአገር ደረጃ ትልልቅ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች (የመንገድ፣ የኃይል አቅርቦት፣ የቴሌኮም ወዘተ) መስፋፋት፣<br>✓ በተመረጡ ቦታዎች ላይ ኢንዱስትሪዉን ለማሳደግ የኢንዱስትሪ ፓርኮች መገንባታቸው፣<br>✓ በኮንስትራክሽን ዘርፍ እያደገ የመጣዉ የመልማት ፍላጎትና የተሰጠዉ ትኩረት፣<br>✓ የአገራችን ኢኮኖሚ እያደገ መምጣቱና የዜጎች የመሰረተ ልማት ፍላጎት እያደገ መምጣቱ ኢንዶዉመንቱ በተሰማራባቸዉ የስራ መስኮች ሰፊ የገበያ ዕድል የሚፈጥር መሆኑ፣<br>✓ በአካባቢው በአበባ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ኢንቨስትመንት እየተሰማሩ ያሉ የባለሃብቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣<br>✓ በክልላችን በርካታ የኢንቨስትመንት ሃብቶችና አማራጮች መኖራቸዉ፣<br>✓ ለአምራች ዘርፉ የብድር አቅርቦቱ እየተሻሻለ መምጣቱ፤ | ✓ በዓለም አቀፍ ደረጃ በየጊዘዉ የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ እና በኃያላን ሀገራት መካከል እታያ ያለዉ የንግድ ጦርነት፣<br>✓ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተዉ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የንግድ እንቅስቃሴ መስተጓጎል፣<br>✓ የዉጭ ምንዛሬ በየጊዜዉ ማደግና ከዉጭ ሀገር በሚገቡ ግብዓቶች ዋጋ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ መሆኑ እና የውጭ ምንዛሬ ግኝት እጥረት የሚታይበት መሆኑ፣<br>✓ የኢንቨስትመንት ወጭ በየጊዜዉ መጨመር፣<br>✓ ጤናማ ያልሆኑ የግብይት ስርዓት መስፈን፣<br>✓ የኃይል አቅርቦት በበቂ ሁኔታ አለመኖር፤<br>✓ የዋጋ ግሽበት መኖሩ፣ |

| | መልካም አጋጣሚዎች | ሥጋቶች |
|---|---|---|
| | **3. ማኅበራዊ ሁኔታዎች** | |
| | ✓ በሀገራችንም ሆነ በክልላችን በህብረተሰቡ ዘንድ ሰርቶ ለመለወጥና ኑሮውን ለማሻሻል የሚተጋበት ሁኔታ እየተፈጠረ መምጣት፤<br>✓ የትምህርትና የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የጤና፣ የአነስተኛና ጥቀቃቅን ኢንተርፕራይዞች በማስፋፋት በተለያዩ ሙያዎች የሰለጠነ፣ ጤነኛና አምራች የህብረተሰብ ክፍል ለመፍጠር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ፤<br>✓ የህብረተሰቡ አብሮ የመኖርና የመረዳዳት ባህል፣ በየአካባቢው ለልማት አጋዥ የሚሆኑ አደረጃቶች ለምሳሌ የወጣቶች፤ የሴቶች የህብረት ስራ ማህበራት እና ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች (እቁብ ፤ እድር …ወዘተ ) መኖራቸው የኢንዶውመንቱ የገቢ ማስገኛ ተቋማት የሚካሂዱት ኢንቨስትመንት እንደ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርመሆኑ፤<br>✓ በግሎባላይዜሽንና በመረጃ ቴክኖሎጂ ትስስር ማደግ ምክንያት በዓለም ላይ የተፈጠረው ማህበራዊ ቁርኝት የተጠናከረ በመሆኑ ጠንካራ የሥራና ተቋማዊ ባህል ለመገንባት እድል የሚሰጥ መሆኑ፣<br>✓ አምራች የሰው ኃይል ከአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር አንጻር ከፍተኛ መሆኑና በተነጻጻሪ ርካሽ የሰዉ ጉልበት መኖሩ፣ | ✓ ገበያዉ በሚፈልገዉ አግባብ በቂ እውቀትና ክህሎት ያለዉ የሰለጠነ የሰው ኃብት አለመገኘት፣<br>✓ ይሁን እንጅ የህብረተሰቡ የስራ ባህል በሚፈለገው ደረጃ አለማደግ እንዲሁም የጊዜ አጠቃቀም ባህሉና ግንዘቤ አናሳ መሆን፤<br>✓ ወጣቱ በተለያዩ መጤ ባህሎች ሰለባ መሆንና የውጭ ባህል ወረራ ተጠቂ መሆን እና አደንዛዥ እጽ መስፋፋት፤<br>✓ ብልሹ አሰራርና ሙስናን ከመታገል አኳያ በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ንቃተ-ህሊና በሚፈለገው ደረጃ የደረሰ አለመሆን፤<br>✓ የሃይማታዊ በዓላት አከባበር ችግር፤<br>✓ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስርጭት መስፋፋት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየጨመረ የመጣው ኮቪድ-19 ወረርሽኝ፤ |
| | **4. ቴክኖሎጂያዊ ሁኔታዎች** | |
| | ✓ በዓለም ላይ ቴክኖሎጅን በመጠቀም በመረጃ ልውውጥና በንግድ እንቅስቃሴ ትስስር በመፍጠር ከመቼውም ጊዜ በላይ ቅርርብ የተፈጠረበት ሁኔታ መኖሩ፤<br>✓ በዓለም ላይ የቴክኖሎጅ አማራጮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ መምጣታቸዉና የማያቋርጥ የቴክኖሎጅ እድገት መኖር፣<br>✓ በቴክኖሎጅ እዉቀት ሽግግር ለማምጣት በመንግስት በኩል እየተደረገ ያለዉ ጥረትና በአገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጅ ዘርፍ ትኩረታቸዉን ማዕከል ያደረጉ | ✓ ቴክኖሎጅ ለመጠቀም የግንዛቤና እውቀት ውስንነት መኖር፣<br>✓ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ አገራዊ የእዉቀት ዉስንነት መኖር፣<br>✓ ቴክኖሎጅ በፍጥነት መለዋወጥና የአንዳንድ ቴክኖሎጅዎች ዋጋ መናር፣<br>✓ ለአላስፈላጊ የውጭ ባህሎች ወረራ በር እየከፈተ መሆኑ፣<br>✓ ተስማሚ ቴክኖሎጅ ከመምረጥ አንጻር የፋይናንስ፣ የእውቀትና አቅም ውስንነቶች ሊኖር ይችላል፣ |

| | መልካም አጋጣሚዎች | ሥጋቶች |
|---|---|---|
| | ዩኒቨርሲቲዎች መከፈታቸዉ፣<br>✓ የቴክኒዮሎጅ አቅራቢ ተቋማት እየተስፋፉ መምጣት ቴክኒዮሎጅን አላምዶ ለመጠቀም የሚቻልበት እድል የሚፈጥር መሆኑ፤<br>✓ በአገራችን ቴክኖሎጅን ለመኮረጅ የሚያስችል አቅም እየተፈጠረ መምጣቱና መንግስት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት፤<br>✓ የገበያ ስርዓትን ለማቀላጠፍ እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል የመረጃ ቅብብሎሽን ሊያሳድጉ የሚችሉ የቴክኖሎጅ አማራጮች እየሰፉ መምጣታቸዉ፤<br>✓ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅና ሥራዎቻቸውን ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ግብአቶች መኖራቸው፣ | ✓ የአንዳንድ ቴክኖሎጅዎች ዋጋ ውድ መሆን፣<br>✓ ተስማሚ ቴክኖሎጅን ከመለየትና ከመምረጥ አኳያ ክፍተት መኖር፤<br>✓ የውጭ የቴክኖሎጅ አመንጪዎች ቴክኖሎጅዉን በተሟላ ሁኔታ ከማስተላለፍ አኳያ የሚኖራቸዉ ፍላጎት አነስተኛ ሊሆን ይችላል፤ |
| | 5. አካባቢያዊ ሁኔታዎች | |
| | ✓ በመንግስትና በህዝቡ በኩል ለአካባቢ ጥበቃና ለተፈጥሮ ሃብት ልማት የተሰጠው ትኩረት፣<br>✓ ክልላችን ሰፊ እና እምቅ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት መሆኗ፣<br>✓ በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ አካላት ከአካባቢ ደህንነትና ጥበቃ ጋር ተያይዞ ያለው ክትትልና ቁጥጥር፣<br>✓ ከአበባ ምርት ሂደት ጋር ተያይዞ የምንጠቀማቸዉ ኬሚካሎችና ማዳበሪያዎች በአካባቢ ላይ የጎላ ተፅዕኖ እንዳያሳድሩ ለማድረግ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተቀርጸዉ ተግባራዊ ማድረግ መጀመሩ፤ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩት ተቋማት በትኩረት ተይዘዉ እየተሰሩ መሆኑ፤ | ✓ በዓለም ላይ ያለው ፍትሃዊ ያልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና ተፈጥሮን ግምት ውስጥ ያላስገባ የልማት እንቅስቃሴ፣<br>✓ መጠነ ሰፊ የካርቦን ልቀት በመኖሩ ለምድራችን ከምንጊዜውም በላይ ከፍተኛ ስጋት የተጋረጠባት መሆኑ፤<br>✓ የከርሰ ምድርና የገፀ ምድር ውሃ መጠን እየቀነሰ መምጣት፣ |

| | መልካም አጋጣሚዎች | ሥጋቶች |
|---|---|---|
| | **6. ሕጋዊ ሁኔታዎች** | |
| | ✓ አገራችን ከሌሎች አገሮች ጋር የምታደርጋቸው በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረቱ የንግድ እና የኢንቨስትመንት ስምምነቶች መኖራቸዉ፤<br>✓ በአገራችን ኢንቨስትመንትንም ሆነ ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ህጎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መኖራቸዉ፣<br>✓ የበጎ አድራጎት ማኅበራትን ሊገዛና ሊያስተዳድር የሚችል እንዲሁም የግብረሰናይ ስራዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራት የሚያስችል አዋጅና ደንብ መኖሩ፣<br>✓ እንደ ጋፋትና መሰል ድርጅቶች በስራቸው ለንግድ የተቋቋሙ ኩባንያዎችን ከመምራትና ከማስተዳደር አኳያ ሊያግዝ የሚችል የህግ ማዕቀፍ መኖር፤ | ✓ የተደረገዉን የዉጭ ምንዛሬ ተመን ማስተካከያ ተከትሎ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ መከሰቱና ይህን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የማካካሻ ክልላዊ የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ፣<br>✓ በሀገር ደረጃ የኤክስፖርት ሽያጭን በዱቤ የሚፈቅድ ህጋዊ ማዕቀፍ አለመኖሩ የአበባ ምርትን በመካከለኛዉ ምስራቅ ገበያ ዉስጥ በስፋት ለመግባት ማነቆ መሆኑ፣<br>✓ የጉልበት ሠራተኞች የጡረታ ዋስትና አዋጅ ተቋማት ላይ ተፅዕኖ እያሳረፉ በመሆኑ በቀጣይ በጋፋት ኢንዶዉመንት ኩባንያዎች እንቅስቃሴና ትርፋማነት ላይ ስጋት ማሳደራቸዉ አይቀርም፡፡<br>✓ ክፍለ አህጉራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የንግድ ህጎችን በማወቅና የተሟላ ግንዛቤ ይዞ በመንቀሳቀስ ረገድ ክፍተት የሚታይ መሆኑ፣ |

## 1.5. የአስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ማጠቃያ

| አስቻይ ሁኔታዎች(ጥንካሬ + መልካም አጋጣሚ) | ፈታኝ ሁኔታዎች(ድክመት + ስጋት) |
|---|---|
| ❖ የዓለም ኢኮኖሚ በፍጥነት እያደጉ ባሉ አገሮች ጭምር እየተመራ መምጣቱ እና አገራችን ከሌሎች አገሮች ጋር የፈጠረቻቸው ግንኙነቶችና የተደረሰባቸዉ ስምምነቶች ለኢንዶዉመንቱ ምርቶች ገበያ ከመፍጠር ባሻገር ከውጭ ባለሃብቶች ቴክኖሎጅ፣ እውቀትና ልምድ የሚገኝበትን ዕድል የሚፈጥር መሆኑ፣<br>❖ በአገራችን ሊያሰራ የሚችል ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና ስትራቴጅ መኖሩና ከዚህ ጋር ተያይዞ ኢንቨስትመንትን ሊደግፉና ሊያበረታቱ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎች መኖራቸው በክልሉ ውስጥ ስትራቴጅክ በሆኑና የገበያ ጉድለት በሚታይባቸዉ የኢንቨስትመንት መስኮች ለመሰማራት እድል የሚፈጥር መሆኑ፣<br>❖ በክልላችን ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆኑ የህግ ማዕቀፎች መኖራቸዉና ልዩ ልዩ ድጋፎች እየተደረጉ መሆኑ ጋፋት ኢንዶዉመንት በክልሉ ዉስጥ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ለያዘው ዓላማና ቁርጠኝነት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ መሆኑ፣<br>❖ የአገራችን ኢኮኖሚ እያደገ መምጣቱና የሕዝባችን የመሰረተ ልማት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ ጋፋት ኢንዶዉመንት በተሰማራባቸው የኮንስትራክሽን የስራ ዘርፎች ምቹ የገበያ ዕድል የሚፈጥር መሆኑ፣<br>❖ በአገራችን ለትምህርትና ጤና እንዲሁም ለሳይንስና ቴክኖሎጅ ትኩረት መሰጠቱ ኢንዶውመንቱ ለተሰማራባቸው የስራ ዘርፎች የሰለጠነና ጤናማ የሰው ኃብት ለማግኘት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣<br>❖ በመንግስትና በህዝቡ በኩል ለአካባቢ ጥበቃና ለተፈጥሮ ሃብት ልማት የተሰጠው ትኩረት እንዲሁም በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ አካላት ከአካባቢ ደህንነትና ጥበቃ ጋር ተያይዞ ያለው ክትትልና ቁጥጥር ስርዓት እየተገነባ | ❖ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከሰተ ያለው ብጥብጥና አለመረጋጋት በቀጣይ ለኢንዶዉመንቱም ሆነ ለገቢ ማስገኛ ተቋማት የስራ እንቅስቃሴ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፣<br>❖ እንደ ሃገር ያለው የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት እንዲሁም በየደረጃው ያለውን የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ የተንዛዛ በማድረግ እና የመልካም አስተዳደር ችግር በመፍጠር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ለሚደረገው ጥረት እንቅፋት የሚፈጥር መሆኑ፣<br>❖ በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ያለው የዋጋ ግሽበት እየጨመረ መምጣት እና በዶላር ምንዛሬ ጭማሪ ምክንያት የማምረቻ ወጪዎች ሊንሩ የሚችሉበት እድል እየሰፋ ሊሄድ የሚችል መሆኑ፣<br>❖ በግሎባላይዜሽን ምክንያት ጎጅ የሆኑ የውጭ ልማዳዊ ድርጊቶችን ወደ አገራችን የማስገባቱ እድል እየሰፋ በመምጣቱ ማኅበራዊ እሴቶቻችንን በተለይም የወጣቱን የስራ ተነሳሽነት እየጎዳ የመጣ መሆን፣<br>❖ በአለም የአየር ንብረት መዛባት ምክንያት የተፈጥሮ አደጋዎች እየተባባሱ የመጡ በመሆኑ ኢንዶዉመንቱ በተለይም በግብርናው ዘርፍ ለሚያካሂደው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እንቅፋት ሊፈጥር ይችላል፣<br>❖ የአገራችን የንግድ ህግ የሚሻሻል ካልሆነና እንደ ጋፋት ኢንዶዉመንት አይነት በኮርፖሬት ማዕከልነት ራሳቸዉን ይበልጥ አጠናክረዉ የሚሄዱበት እድል ካልተፈጠረ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ኩባንያዎችን ለመከታተል፣ ለመደገፍና ተገቢዉን የማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ለመሄድ እንቅፋት መፍጠሩ፣<br>❖ ቴክኖሎጅን ለማላመድና ለመጠቀም፣ ኢንቨስትመንትንና ኩባንያዎችን በአግባቡ ለመምራት የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት መኖሩ፣ |

| አስቻይ ሁኔታዎች(ጥንካሬ + መልካም አጋጣሚ) | ፈታኝ ሁኔታዎች(ድክመት + ስጋት) |
| --- | --- |
| በመሆኑ የኢንዶዉመንቱ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያይዞ ለያዘው ዓላማ መሳካት አጋዥ መሆኑ፣<br>❖ እንደሃገር የወጣዉ የበጎ አድራጎት ማኅበራት መመዝገቢያና ማስተዳደሪያ አዋጅ ኢንዶዉመንቱንና መሰል የልማት ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ለመስራትና ውጤታማ የሆኑ የግብረ ሰናይ ስራዎችን ለመስራት የሚያግዝ መሆኑ፣<br>❖ በአገራችን በአሰሪና ሰራተኞች መካከል ያለውን ግንኙነት እና መስተጋብር የተስተካከለ ለማድረግ፣ የኢንዶዉመንቱን ራዕይ የተጋሩና ለተቋማቱ እድገት ጠንክረው የሚሰሩ ሰራተኞችን ለመፍጠርና በኢንዶዉመንት ደረጃ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ያለው ቁርጠኝነት የኢንዱስትሪ ሰላምን አስፍኖ ለመሄድ ለሚደረገው ጥረት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣<br>❖ የገበያ ጉድለት በክልሉ ውስጥ በስፋት የሚታይ መሆኑ ከሌሎች ምቹ ሁኔታዎች ጋር ተዳምሮ ጋፋት ኢንዶዉመንት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ለያዘው ስትራቴጅ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑ፣<br>❖ እንደ ጋፋት የክትትልና ድጋፍ ስርዓት እየተጠናከረ መምጣት ለኢንዶዉመንቱ ተልዕኮዎች መሳካት አጋዥ ሁኔታን የሚፈጥሩ መሆኑ፣ | ❖ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት፣ የውጭ ባለሃብቶችን በአጋርነት ለመሳብ፣ ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎችን ገዝቶ ለመጠቀም፣ የበጎ አድራጎት ስራዎችን በተስፋፋና በተጠናከረ መንገድ ለማስኬድ እና ለመሰል ጉዳዮች የኢንዶዉመንቱ የፋይናንስ አቅም በሚፈለገው ደረጃ የዳበረ አለመሆኑ፤<br>❖ ስራዎችን አቅዶ፣ አደራጅቶና ተገቢዉን የክትትልና ድጋፍ ስርዓት ዘርግቶ ስራዎችን አቀናጅቶ ከመምራት አኳያ በኩባንያ አመራሩና በፈጻሚው ዘንድ የሚታየው የአመለካከት፣ የክህሎት ውስንነት፣<br>❖ የዉጭ ምንዛሬ ተመን ማስተካከያ ተከትሎ የግንባታ ግብዓቶች አቅርቦት ስርዓት መዛባትና ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ጭማሪ መከሰቱና እንዲሁም ይህን ሊያካክስ የሚችል ክልላዊ የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ ኮንስትራክሽን ኩባንያዎችን ለኪሳራ የሚዳርግ መሆኑ<br>❖ በሀገር ደረጃ የኤክስፖርት ሽያጭን በዱቤ የሚፈቅድ ህጋዊ ማዕቀፍ አለመኖሩ ከአበባ ምርት አኳያ በመካከለኛዉ ምስራቅ ገበያ ዉስጥ በስፋት ለመግባት ማነቆ መሆኑ፣<br>❖ የጉልበት ሠራተኞች የጡረታ ዋስትና አዋጅ በቀጣይ በጋፋት ኢንዶዉመንት ኩባንያዎች እንቅስቃሴና ትርፋማነት ላይ ፈታኝ ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል፡፡ |

## 1.6. የተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ትንተና

ጋፋት ኢንዶዉመንት እና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች ተልዕኳቸውን በመወጣት ተቋማዊ ራዕያቸዉን ያሳኩ ዘንድ ተገልጋዮች እና ባለድርሻ አካላት ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ደንበኞችና ባለድርሻ አካላት በኢንዶዉመንቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ላይ በአዎንታዊም ይሁን በአሉታዊ ጎን ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተጽዕኖ በአግባቡ መገምገምና መተንተን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት በሚቀጥሉት አምስት አመታት (እ.አ.አ. ከ2021-2025) ለመተግበር ባዘጋጀው ስትራቴጅክ እቅድ ላይ የተገልጋዮችን እና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት፣ ኢንዶውመንቱ ከእነርሱ የሚጠብቀውን ቅድመ ሁኔታ እና የሚኖራቸዉን የተጽዕኖ ደረጃ ሊያሳይ የሚችል የተገልጋይ እና የባለድርሻ አካላት ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የኢንዶውመንቱ ደንበኞች/ተገልጋዮች፡-**

- ምርት/አገልግሎት ፈላጊዎች
- መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት
- የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች
- የኢንዶዉመንቱ ሰራተኞች
- ዜጎች

**ባለድርሻ አካላት፡-**

- የክልሉ መንግስት
- የኢንዶዉመንቱ ስራ አመራር ቦርድ
- ባለአክስዮኖች
- ዜጎች

አጋር/ ተባባሪ አካላት

- የፋይናንስ ተቋማት
- መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች
- የግል ባለሃብቶች
- ከፍተኛ የትምህርት፣ የምርምርና ስልጠና ተቋማት

## 1.6.1. የተገልጋዮች፤ ባለድርሻ እና አጋር አካላት ፍላጎት ትንተና

| ተ.ቁ | ደንበኞች/ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት | ኢንዶዉመንቱ ከተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸዉ ባህርያት | ኢንዶዉመንቱ የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ባያሟላ ሊገጥመዉ የሚችል ችግር | የተገል ጋዮች/ባ ለድርሻ አካላት የተጽዕ ኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተገልጋዮች | | | | |
| 1.1 | ምርት/አገል ግሎት ፈላጊዎች | ➢ ጥራት ያለዉ የአበባ ምርት፣ ዲዛይንና ቁጥጥር እና ግንባታ ስራዎች ማግኘት፣<br>➢ በተመጣጣኝ ዋጋ ቀልጣፋ የምርት/አገልግሎት ማግኘት<br>➢ ቀጣይነት ያለው ደንበኝነት፣ | ➢ ግልጽና ፍትሀዊ የስራ ግብዣ (የዉድድር ዕድል) መፍጠር፣<br>➢ ፕሮጀክቶችንና ስራዎችን በወቅቱ የማሳወቅና የስራ ትዕዛዝ የመስጠት፣<br>➢ የምርት/የአገልግሎት ክፍያዎች በወቅቱ መፈጸም፣<br>➢ የኢንዶዉመንቱ አሰራር የማክበር፣<br>➢ ወቅታዊ ግብረመልስ መስጠት፣<br>➢ አስተማማኝ ደንበኝነት፣ | ➢ የደንበኛን አመኔታና ገበያ ማጣት፣<br>➢ አላስፈላጊ የምርት ክምችትና ብልሽት፣<br>➢ የስራ ሽፋንና የምርት ሽያጭ በመቀነስ ትርፍ መቀነስ/ኪሳራ፣<br>➢ አዳዲስ ደንበኞችን አለማግኘት፣ | ከፍተ ኛ |
| 1.2 | የበጎ አድራጎት ድጋፍ የሚሹ አካላት | ➢ ለበጎ አድራጎት የሚዉል ሐብት ማግኘት፣<br>➢ ግልጽነትና አሳታፊነትን የተላበሰ የተጠቃሚዎች ልየታ መኖር፣<br>➢ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ስርዓት እንዲኖር ይፈልጋሉ፣<br>➢ የበጎ አድራጎት ገንዘቡ በተቀመጠዉ ስምምነት መሰረት እንዲለቀቅላቸዉ ይፈልጋሉ፣ | ➢ በኢንዶዉመንቱ የበጎ አድራጎት ማስፈፀሚያ መመሪያ መሰረት የፕሮጀክት ሰነድ የማቅረብ፣<br>➢ በተቀመጠው ስምምነት መሰረት ፕሮጀክቶችን መፈፀም፣<br>➢ የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት ማረጋገጥ፣<br>➢ ወቅቱን የጠበቀ፣ ጥራት ያለውና የተሟላ የአፈጻፀም ሪፖርት የማቅረብ፣ | ➢ የኢንዶዉመንቱ የገጽታ ግንባታ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፣<br>➢ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር ተጠያቂነትን ያስከትላል፣<br>➢ የለጋሽ አካላትን ተአማኒነት ያሳጣል፣ | ከፍተ ኛ |
| 1.3 | ዜጎች | ➢ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚነታቸዉን ማረጋገጥ፣ | ➢ የልማት ፍላጎት መኖር እና ሰርቶ ለመለወጥ መነሳሳት፣<br>➢ በኢንዶዉመንቱ የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ባለቤትና አጋዥ መሆን፣<br>➢ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን መታገል፣ | ➢ ተልዕኮዉን በአግባቡ ላያሳካ ይችላል፣<br>➢ በተቋሙ ላይ አመኔታ ሊያጡ ይችላሉ፣<br>➢ የሀብት ብክነትን ያስከትላል፣<br>➢ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ስራዉ ውጤታማ ላይሆን ይችላል፣ | ከፍተ ኛ |
| 1.4 | የክልሉ መንግሰትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት | ➢ በክልሉ ኢንቨስትመንት ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ ማድረግ፣<br>➢ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የበጎ አድራጎት ስራዎች ላይ መሳተፍ፣<br>➢ የግብር እና ሌሎች ተያያዥ ግዴታዎችን መወጣት፣<br>➢ ግልጸኝነትና አሳታፊነትን መከተል፣<br>➢ የኢንቨስትመንት ስራዎች የአካባቢዉን | ➢ ቀልጣፋ መንግስታዊ አገልግሎት፣<br>➢ ምቹ መሰረተ ልማትን ማሟላት፣<br>➢ ለኢንዶዉመንቱ ዓላማ ማስፈፀሚያ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ<br>➢ ፕሮጀክቶችንና ስራዎችን በወቅቱ የማሳወቅና የስራ ትዕዛዝ የመስጠት፣<br>➢ ከውጭ ባለሃብቶች ጋር ለሚደረግ ግንኙነት ምቹ ሁኔታን መፍጠርና ተገቢውን ድጋፍ | ➢ የደንበኛን አመኔታና ገበያ ማጣት፣<br>➢ ለኢንዶዉመንቱ ዓላማ ማስፈፀሚያዎች የሚሆን በቂ ሃብት ላይገኝ ይችላል፤<br>➢ ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት አኳያ የኢንዶዉመንቱን ዓላማ ለማሳካት ያስቸግራል፣<br>➢ ተቋማዊ አመኔታን ማጣትና በህግ የመጠየቅ፣ | ከፍተ ኛ |

| ተ.ቁ | ደንበኞች/ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት | ኢንዶዉመንቱ ከተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸዉ ባህርያት | ኢንዶዉመንቱ የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ባያሟላ ሊገጥመዉ የሚችል ችግር | የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የተጽዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ስነ-ምህዳር ጠብቀዉ እንዲሰሩ ማድረግ፣<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲፈጠር፣ | ማድረግ፣<br>➢ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ማድረግ፣<br>➢ ሰላማዊ የስራ አካባቢ መፍጠር፣ | ➢ እቅዶቹን ለማስፈፀም የአቅም ውስንነት ይገጥመዋል፣<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ | |
| 1.5 | የኢንዶዉመንቱ አመራሮችና ሰራተኞች | ➢ የጋፋት ኢንዶዉመንት ራዕይና ተልዕኮዎች እዉን ሆነው ማየት፣<br>➢ መልካም አስተዳደር መስፈን፣<br>➢ ወቅታዊና ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያና ጥቅማጥቅም፣<br>➢ የስራ ዋስትና የማግኘት፣<br>➢ ምቹ የስራ አካባቢ እንዲፈጠር፣<br>➢ የስራ ግብዓቶች እንዲሟሉላቸዉ፣<br>➢ አቅማቸዉ እንዲጎለብት የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና የመፈለግ፣<br>➢ ሊያሰራ የሚችልአደረጃጀት ይፈልጋሉ፣ | ➢ የስራ ተነሳሽነትና ዉጤታማነት፣<br>➢ ሚስጥር ጣባቂነት፣<br>➢ ከኪራይ ሰብሳቢነት የፀዳ አመለካከትና ተግባር፣<br>➢ የአፈጻፀም ብቃታቸዉን በማያቋርጥ ሁኔታ ለማሳደግ መጣርን፣<br>➢ የመረዳዳት፣ የመተጋገዝና እርስበርስ የመማማር ባህልን ማሳደግ፣<br>➢ የኢንዶዉመንቱን የአሰራር ስርዓቶችና የስነ-ምግባር ደንቦች አክብሮ መንቀሳቀስ፣ | ➢ የስራ መጓተት ይፈጠራል፣<br>➢ የሰራተኛ ፍልሰት ይኖራል፣<br>➢ የስራ ሞራል፣ ምርታማነትና ውጤታማነት መቀነስ፣<br>➢ የኢንዱስትሪ ሰላም ይጠፋል፣<br>➢ ኢንዶዉመንቱ ራዕይና ተልዕኮውን ለማሳካት ይቸገራል፣<br>➢ በአመራሩና በሰራተኛዉ መካከል መደጋገፍና መናበብ ይጠፋል፣ | ከፍተኛ |
| 1.6 | የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች | ➢ ግልጽና አሳታፊ የግዥ ስርዓት፣<br>➢ ፍላጎትን በወቅቱ ማሳወቅ፣<br>➢ ግብዓቱ በወቅቱ እንዲነሳላቸዉ፣<br>➢ ወቅታዊ የአቅርቦት ክፍያ፣<br>➢ ቋሚ ደንበኝነት፣ | ➢ በሚፈለገዉ ጥራት፣ መጠንና ዓይነት ግብዓትን በወቅቱ የማግኘት፣<br>➢ ገበያን መሰረት ያደረገ ዋጋ የማቅረብ፣<br>➢ ቀጣይነት ያለዉና አስተማማኝ አቅርቦት፣<br>➢ ቋሚና ዘላቂ ደንበኝነት፣<br>➢ ቀልጣፋ አገልግሎት ማግኘት፣<br>➢ ህጋዊና ትክክለኛ ሰነድ የማሟላት፣ | ➢ የደንበኛ ዓመኔታ ማጣት፣<br>➢ ለኪራይ ሰብሳቢነት በር ሊከፍት ይችላል፣<br>➢ የግብዓት አቅርቦት መጓተት እና እጥረት ሊፈጠር ይችላል፣<br>➢ ግብዓትን በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ጥራት እና በሚፈልገዉ ጊዜ ላይገኝ ይችላል፣ | ከፍተኛ |
| 2 | ባለድርሻ አካላት | | | | |
| 2.1 | የክልሉ መንግስት | ➢ ኢንዶዉመንቱ በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ይፈልጋል፣<br>➢ የልማት ስራዎች በጥራትና በወቅቱ ተሰርተዉ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ይፈልጋል፣<br>➢ የኢንዶዉመንቱ አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ይፈልጋል፣<br>➢ በክልሉ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ የስራ እድል መፍጠር እና የቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲመጣ ይፈልጋል፣<br>➢ የመንግስት፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች | ➢ ቀልጣፋ አገልግሎት ማግኘት እና መሰረተ ልማቶች እዲሟሉ ይፋልጋል፣<br>➢ በፋይናንስና በሌሎች የድጋፍ ዓይነቶች መታገዝ፣<br>➢ ፍትሃዊ የሆነ የገበያ ውድድር ስርዓት እንዲኖር፣<br>➢ በቅንጅት መስራት፣<br>➢ ህብረተሰቡን ለልማት ማነሳሳትና ማደራጀት፣<br>➢ ሰላም እና መልካም አስተዳድር እንዲሰፍን፣ | ➢ የኢንዶዉመንቱ ዓላማ በታሰበዉ መልኩ ውጤታማ አይሆንም፣<br>➢ የኢንዶዉመንቱን ተልዕኮ ከማሳካት አንጻር ተጽዕኖ ሊፈጠር ይችላል፣<br>➢ የኢንዶዉመንቱን ህልዉና ጥያቄ ዉስጥ ያስገባል፣ | ከፍተኛ |

| ተ.ቁ | ደንበኞች/ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት | ኢንዶዉመንቱ ከተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸዉ ባህርያት | ኢንዶዉመንቱ የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ባያሟላ ሊገጥመዉ የሚችል ችግር | የተገል ጋዮች/ባ ለድርሻ አካላት የተጽዕ ኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሳይሸራረፉ እንዲተገበሩ ይፈልጋል፣ | | | |
| 2.2 | የኢንዶዉ መንቱ ስራ አመራር ቦርድ | ➢ ኢንዶዉመንቱ በዕቅድ እንዲመራ ይፈልጋል፣<br>➢ ወቅታዊና ጥራት ያለዉ የኢንዶዉመንቱን እንቅስቃሴ የሚያሳይ ሪፖርትና መረጃ፣<br>➢ ኢንዶዉመንቱ የበጎ አድራጎት ስራዎችን በስፋትና ዉጤታማ በሆነ መንገድ እንዲሰራ ይፈልጋል፣<br>➢ የኢንዶዉመንቱ ዓላማዎች ስኬታማና ውጤታማ እንዲሆኑ ይፈልጋል፣<br>➢ በተቋሙ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር እንዲኖር ይፈልጋል፣<br>➢ መልካም የስራ፣ ግንኙነት እንዲኖር ይፈልጋል<br>➢ የኢንዶዉመንቱ የሂሳብ እቅስቃሴ በውጭ ኦዲተሮች እንዲመረመር ይፈልጋል፣<br>➢ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በቅንጅት እንዲሰራ ይፈልጋል፣ | ➢ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ለኢንዶዉመንቱ ተጨማሪ ሃብት ማፈላለግ፣<br>➢ የተጠናከረ ድጋፍና ስትራቴጅካዊ የስራ አቅጣጫዎችን የመስጠት<br>➢ ፈጣንና ወቅታዊ ውሳኔዎችን የማሳለፍ<br>➢ የኢንዶዉመንቱ ተግዳሮቶችን የመፍታት<br>➢ የኢንዶውመንቱን ገጽታ የመገንባት፣ | ➢ የኢንዶዉመንቱ ቀጣይነት /ዘላቂነት/ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፣<br>➢ በየደረጃው ባለ አካል ላይ ተጠያቂነትን ያስከትላል፣ | ከፍተ ኛ |
| 2.3 | ባለአክስዮኖ ች | ➢ ያቋቋሟቸዉ ኩባንያዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ይፈልጋሉ፣<br>➢ ግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ሰፍኖ ማየት ይፈልጋሉ፣<br>➢ የትርፍ ክፍፍል ድርሻቸውን በወቅቱ ማግኘት፣<br>➢ የኩባንያዎች የሂሳብና ህጋዊነት እንቅስቃሴ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ይፈልጋሉ፣ | ➢ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ማድረግና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በትብብር መፍታት፣<br>➢ ለኩባንያው መስፋፋትና መጠናከር በጥሬ ገንዘብም ይሁን በዓይነት የአክስዮን ድርሻን ማሳደግ፣<br>➢ በባለ አክስዮኖች ሊወሰኑ የሚገባቸዉን ውሳኔዎች በአፋጣኝ የመወሰን፣<br>➢ መመሪያዎች፣ ደንቦችና አሰራሮች እንዲወጡና እንዲጸድቁላቸዉ ማድረግ፣<br>➢ የውጭ ኦዲተር በወቅቱ እንዲሰየም ማድረግ፣ | ➢ ሪኢ-ንቨስትመንት መጠን መቀነስ<br>➢ የአክሲዮን ድርሻቸዉ፣ ሊቀንስ፣ ሊሸጥ/መዉጣት<br>➢ የኩባንያዎች አፈጻፀም ሊንተት ይችላል፣<br>➢ የኩባንያዎች ትርፋማነት ሊቀንስ ይችላል፣<br>➢ ኩባንያዉ የመሸጥ፣ የመታጠፍ ዕጣ ፈንታ ሊገጥመዉ ይችላል፣ | ከፍተ ኛ |

| ተ.ቁ | ደንበኞች/ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ፍላጎት | ኢንዶዉመንቱ ከተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸዉ ባህርያት | ኢንዶዉመንቱ የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ባያሟላ ሊገጥመዉ የሚችል ችግር | የተገል ጋዮች/ባ ለድርሻ አካላት የተጽዕ ኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | አጋር/ተባባሪ አካላት | | | | |
| 3.1 | የፋይናንስ ተቋማት | ➢ አዋጭ በሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ ተመስርቶ ተገቢ መረጃዎችን ያሟላ የብድር ጥያቄ ማቅረብ፣<br>➢ የተፈቀደ ብድር ለታለመለት አላማ እንዲውል ይፈልጋሉ፣<br>➢ ብድር በወቅቱ መመለስ፣<br>➢ ለሰጡት ብድር ተገቢውን ወለድ ማግኘት፤<br>➢ የአርቦን ክፍያዎች በወቅቱ እንዲፈፀምና ወጭ የመተካት ጥያቄ በወቅቱ እንዲቀርብ፤<br>➢ ሰብዓዊና ቁሳዊ ሃብቶች በጥንቃቄና በአግባቡ መያዝና ማስተዳደር፤ ችግር ከተፈጠረም ከተገቢው መረጃ ጋር በወቅቱ ማቅረብ፣ | ➢ ቀልጣፋ፣ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራርና አገልግሎት ማግኘት፣ (በውጭ ምንዛሬ፣ በገንዘብ ዝውውር በኤልሲ ወዘተ..)<br>➢ ተፈላጊዉን ብድር በወቅቱና በተመጣጣኝ ወለድ ማግኘት፣ በቂ የመመለሻ ጊዜ እና የእፎይታ ጊዜ፤<br>➢ በፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣<br>➢ ዝቅተኛ የሆነ የአርቦን ክፍያ፣<br>➢ ወጪ ማካካሻን በወቅቱ ማግኘት፣ | ➢ የኢንቨስትመንትና የመስሪያ ካፒታል እጥረት ሊገጥም ይችላል፣<br>➢ የፕሮጀክቶች ውጤታማነት መቀነስና በእዳ የመሸጥ ችግር ሊከሰት ይችላል፣<br>➢ የህወይትና የንብረት ዋስትና ማጣት ሊከሰት ይችላል፣ | ከፍተኛ |
| 3.2 | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች | ➢ በአጋርነትና በቅንጅት የመስራት፣<br>➢ ግልጽነት የተላበሰ አሰራር፣<br>➢ ተሞክሮና ልምድ መለዋወጥ፣<br>➢ የቴክኖሎጅ ሽግግር፣<br>➢ የልማት ስራዎችን በትብብር መስራት፤ | ➢ ልምድ የመቅሰምና የቴክኖሎጅ ሽግግር፣<br>➢ በሽርክና የመስራት፣<br>➢ በአጋርነትና በቅንጅት የመስራት፣<br>➢ ለበጎ አድራጎት ስራዎች ፋይናንስ ማግኘት፤<br>➢ የጋራ ፎረምና የምክክር መድረክ እንዲኖር፤ | ➢ የኢንዶዉመንቱ ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፣<br>➢ የበጎ አድራጎት ስራዎችን በስፋት መስራት አለመቻል፤<br>➢ የልማት አጋር ማግኘት አለመቻል፤ | መካከለኛ |
| 3.3 | አየር መንገድ፣ የጭነትና የመኪና ኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች | ➢ የማጓጓዝ ፍላጎትን ቀድሞ ማሳወቅ፣<br>➢ ግልፅ የስራ ትዕዛዝና ስምሪት በወቅቱ መስጠት<br>➢ የአገልግሎት ክፍያን በወቅቱ ማግኘት፣<br>➢ በወቅቱ ጭነት እንዲራገፍላቸዉ ይፈልጋሉ፣<br>➢ ግልጽነትና ከሙስና የጸዳ አሰራር፣ | ➢ ምርትንና ግብዓት በአስተማማኝ፣ በጥራትና በወቅቱ ማጓጓዝ፣<br>➢ ጥራት ያለው የኪራይ አገልግሎት፣<br>➢ ተመጣጣኝ ዋጋ የማቅረብ፣<br>➢ ታማኝነትና አስፈላጊ መረጃዎችን ማሟላት፣<br>➢ በስነ-ምግባር የታነፀ ባለሙያ እንዲመደብ፣ | ➢ ምርትና ግብዓት በሚፈለገው ጊዜ እና መጠን ከሚፈለገው ቦታ ላይደርስ ይችላል፣<br>➢ የምርትና ግብዓቶች ብልሽትና ብክነት ይከሰታል፤<br>➢ በስራ ሂደት መጓተቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፣<br>➢ ከገበያ መውጣት ያጋጥማል፣<br>➢ ትርፍ ይቀንሳል፣ ለኪሳራም ሊያጋልጥ ይችላል፣ | ከፍተኛ |
| 3.4 | ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ቴክኒክና ሙያ፣ የምርምርና የሥልጠና ተቋማት | ➢ የስልጠና ፍላጎትን ቀድሞ መለየትና ማሳወቅ፣<br>➢ ለጥናትና ምርምር የሚሆኑ መነሻ ሃሳቦችን አደራጅቶ ማቅረብ፣<br>➢ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ማግኘት፣<br>➢ ለሰልጣኞች የተግባር ልምምድ ትብብር እንዲያገኙ፤<br>➢ ለተመራቂ ተማሪዎች የስራ እድል እንዲፈጠርላቸው፣ | ➢ ብቃት ያለውና ተወዳዳሪ የሰለጠነ ባለሙያ፣<br>➢ ምርትንና አገልግሎትን ሊያሳድጉ የሚችሉ የምርምርና ማማከር አገልግሎቶችን በማግኘት የቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲፈጠር፣<br>➢ ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያና ግልጽነት የሰፈነበት አሰራር፣ | ➢ የምርትና አገልግሎት እድገት ይቀንሳል፣<br>➢ ብቁና ተወዳዳሪ ተቋማትን መገንባት አያስችልም፣<br>➢ በአዳዲስ ቴክኖሎጅ ውጤታማና ተወዳዳሪ መሆን አለመቻል፤<br>➢ በሙያው ብቃት ያለውና የሰለጠና የሰው ሃይል ማግኘት አለመቻል፣ | መካከለኛ |

## 1.6.2. የደንበኞች/ተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት ትንተና ማጠቃለያ

| ተ.ቁ | ደንበኛ/ ተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት | አገልግሎት/ምርት | የምርቱ/ አገልግሎቱ ባህሪይ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የአገልግሎቱ /ምርቱ ጠቀሜታ /ለምን አላማ ይፈለጋል/ | ጥራት | ምርቱን አገልግሎቱን ለማቅረብ/ ለመስጠት | ለምርቱ/አገልግሎት የሚከፈለው ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የተቋሙ ገጽታ |
| 1 | ምርት/አገልግሎት ፈላጊዎች | አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ | ለፍጆታ፣ ለማህበራዊ መስተጋብርና እርካታ | ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀና በአበባ ጥራት ስታንዳርድ መሰረት | በደንበኞች ፍላጎት መሰረትና በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት | ወቅታዊ ገበያን መሰረት ያደረገ | ግልጽ፤ ቅልጥፍና የደንበኛን ፍላጎት መሰረት ያደረገ | የተቋሙን አመኔታ ያተረፈ |
| | | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ ተቋማት እና የመስኖ ልማት አውታሮች ግንባታ | ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፤ የዜጎችን የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፤ | በተቀመጠው የስራ ዝርዝር መሰረት እና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት | በተገባዉ ኮንትራት ውል መሰረት | ወቅታዊ ገበያን መሰረት ያደረገና በውሉ መሰረት | በመርህ ላይ የተመሰረት፤ግልጽ ፤ ቅልጥፍና የደንበኛን ፍላጎት መሰረት ያደረገ | የደንበኛን ፍላጎትና የአጋርነት መንፈስን ያዳበረ |
| | | የድልድይ፣ የመንገድና የህንጻ ግንባታ | ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለመፍጠር፤ የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፤ | በተቀመጠው የስራ ዝርዝር መሰረት እና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት | በተገባዉ ኮንትራት ውል መሰረት | ወቅታዊ ገበያን መሰረት ያደረገና በውሉ መሰረት | አሰራር መሰረት ያደረገ ግልጽ፤ ቅልጥፍና የደንበኛን ፍላጎት መሰረት ያደረገ | የደንበኛን ፍላጎትና የአጋርነት መንፈስን ያዳበረ |
| | | የማሽነሪና ተሽከርካሪ ኪራይ፣ | ለግንባታ ስራዎች፣ ለማንንዣ አገልግሎት | በስራ ስታንዳርድ በኖርማላይዜሽን መሰረት | በውል ስምምነቱ መሰረት | በተቀመጠው የኪራይ ዋጋ እና ገበያን መሰረት ያደረገ፤ | አከራይ ተከራይ ግንኙነት | የተቋሙን አመኔታ ያተረፈ |
| | | የጥናት፣ ዲዛይንና ማማከር ስራዎች | ልዩ ልዩ የግንባታ ሥራዎች መስራት | በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት | በውሉ ጊዜ መሰረት | ተመጣጣኝና ገበያን መሰረት | ደንበኝነት | ተአማኒነትን ያተረፈ |
| 2 | የበጎ አድራጎት ድጋፍ የሚሹ አካላት | ፋይናንስ | ለበጎ አድራጎት ስራዎች | ቀልጣፋ አገልግሎት | በፕሮጀክት ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት | ነፃ ሆኖ የፕሮፖዛሉ ተቀባይነት | አጋርነትና ትብብር | ተአማኒነትን ያተረፈ |
| 3 | ዜጎች | የስራ እድል ፈጠራና ሌሎች ልዩ ልዩ አገልግሎቶች | የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት | የልማት ተጠቃሚነትና እርካታ | በስትራቴጅክ እቅዱ ዘመን | የለውም | መደጋገፍና መተጋገዝ | ተአማኒነትን ያተረፈ ተቋም |

| ተ.ቁ | ደንበኛ/ ተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት | አገልግሎት/ምርት | የምርቱ/ አገልግሎቱ ባህሪይ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የአገልግሎቱ /ምርቱ ጠቀሜታ /ለምን አላማ ይፈለጋል/ | ጥራት | ምርቱን አገልግሎቱን ለማቅረብ/ ለመስጠት | ለምርቱ/አገልግሎት የሚከፈለው ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የተቋሙ ገጽታ |
| 4 | የክልሉ መንግሰትና መንግስታዊ ተቋማት | ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ የበጎ አድራጎት ስራዎች ማከናወን፣ የስራ ዕድል መፍጠር፣ የመንግስት ህጋዊ ግዴታዎችን መወጣት | ለዜጎች ተሳትፎና ተጠቃሚነትና የክልሉን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማፋጠን | የመንግስት እና የህዝብ እርካታና ተጠቃሚነት | በዕቅድ ትግበራ ዘመኑ | የለውም | አጋርነት፣ ትብብርና ቅንጅት | አመኔታን ያተረፈ ተቋም |
| 5 | የኢንዶዉመንቱ አመራሮችና ሰራተኞች | ተመጣጣኝ የስራ ክፍያ፣ ምቹ የስራ ከባቢና የአቅም ግንባታ ስራዎች | የኑሮ ደረጃን ለማሻሻል፣ ለገቢ ምንጭነት፣ | ቅሬታ የሌለበት አገልግሎት ሳቢና ማራኪ ክፍያ | በተቀመጠው አሰራርና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት | የለውም | የባለቤትነት ስሜትን የተላበሰ | ለስራ ምቹ ተቋም |
| 6 | የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች | ግልጽነትና ፍትሃዊነት የተላበሰ አሰራር፤ ቀልጣፋ የክፍያ አገልግሎት | ለግብዓት/አገልግት ሽያጭ | በስፔስፊኬሽን መሰረት | በውለታው መሰረት | ተመጣጣኝና ወቅታዊ ገበያን መሰረት ያደረገ | ደንበኝነት | የተቋሙን አመኔታ ያተረፈ |
| 7 | የኢንዶዉመንቱ ስራ አመራር ቦርድ | እቅድና ወቅታዊ የስራ ሪፖርት፤ ውጤታማ ተቋም | ተቋሙን ውጤታማ ለማድረግና የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ | የተቋሙን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ ገላጭ ወቅታዊ ሪፖርት እና ተወዳዳሪና ውጤታማ ተቋም | በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ | የለውም | በባለቤትነት፣ በአጋርነት፣ መተባበር | አመኔታን ያተረፈ ተቋም |
| 8 | ባለአክስዮኖች | የትርፍ ክፍፍል | ለአዋጡት የካፒታል መዋጪ ተገቢውን ገቢ ለማግኘት | (ROI), የትርፋማነት ደረጃ | በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ | የለውም | ባለቤትነት፣ አጋርነትና ድጋፍ | አመኔታን ያተረፈ ተቋም |
| 9 | አየር መንገድ፣ የጭነትና የመኪና ኪራይ አገልግሎት ሰጪዎች | የሚጓጓዝ ምርትና ግብዓት፤ የትራንስፖርት አገልግሎት ጥያቄ፤ ክፍያን በወቅቱ እንዲፈጸም | ለገቢ ምንጭነት፤ | ፈጣን፤ ከብክትና ጉዳት የፀዳ አገልግሎት | በውል ስምምነቱ መሰረት | ተመጣጣኝና ገበያን መሰረት ያደረገ | ደንበኝነትና አጋርነት | አመኔታን ያተረፈ ተቋም |

| ተ.ቁ | ደንበኛ/ ተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት | አገልግሎት/ምርት | የምርቱ/ አገልግሎቱ ባህሪይ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የአገልግሎቱ /ምርቱ ጠቀሜታ /ለምን አላማ ይፈለጋል/ | ጥራት | ምርቱን አገልግሎቱን ለማቅረብ/ ለመስጠት | ለምርቱ/አገልግሎት የሚከፈለው ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የተቋሙ ገጽታ |
| 10 | የፋይናንስ ተቋማት | አዋጭነት ያለው የፕሮጀክት ሃሳብና የቢዝነስ ዕቅድ፤ ወቅታዊ የሆኑ የሂሳብ መግለጫዎች፤ ብድርን በወቅቱ መመለስ፤ የአርቦን ክፍያ እንዲፈፀምላቸዉ | ደንበኛ ለማፍራትና ትርፋማ ለመሆን | ወቅታዊ ክፍያና አገልግሎት | በተገባዉ ውል ስምምነት መሰረት | ተመጣጣኝ ወለድና የአርቦን ክፍያ | አጋርነት | አመኔታን ያተረፈ ተቋም |
| 11 | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች | ለበጎ አድራጎት ፕሮጀክቶች ፋይናንስ፣ ተሞክሮ፣ በትብብር መስራት | ለያዙት ዓላማ ማስፈጸሚያና ስኬት | በተዘረጋ የአሰራር ስርዓት መሰረት | በፕሮጀክት ስምምነቱ መሰረት እና በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ | የለውም | አጋርነትና ትብብር | አመኔታን ያተረፈ ተቋም |
| 12 | ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ቴክኒክና ሙያ፣ የምርምርና የሥልጠና ተቋማት | የምርምር ሃሳቦችንና የስልጠናት/ት ፍላጎት፤ የሰው ሃይልና የቁሳቁስ ትብብር፤ | የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት፣ ለዜጎች ተጠቃሚነት | ችግር ፈች የምርምርና የቴክኖሎጅ ውጤቶች | በስትራቴጅክ እቅድ ዘመኑ | የለውም | የአጋርትና የትብበር | አመኔታን ያተረፈ ተቋም |

## 1.7. ከሁኔታ ትንተና ተጨምቀዉ የወጡ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች (Strategic Issues)

1.7.1. ሰፊ የኢንቨስትመንት አማራጮች እና መልካም አጋጣሚዎች ያሉ ቢሆንም ለአዳዲስና ነባር ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ የሚሆን እንዲሁም ለበጎ አድራጎት ስራ የሚውል የፋይናንስ እጥረት መኖር፤

1.7.2. የኢንዶውመንቱ ገቢ ማስገኛ ኩባንያዎች በተሰማሩበት የስራ ዘርፎች ምርትና ማርታማነትን ወይም አገልግሎትን በማሳደግ ትርፋማነትን ቀጣይነት ባለው መልኩ በማሻሻል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ውስኑነት መኖሩ፡፡

1.7.3. በአለም የአበባ ገበያ ላይ በስፋት ለመግባት እንዲሁም በኮንስትራክሽን ኩባንየያዎች በገበያ ተወዳዳሪ ሆኑ ፕሮጅክቶችን የመያዝ ውኑነት መኖሩ፤

1.7.4. ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ገንብቶ ለማስረከብ እና ለአቅራቢዎች ወቅታዊ ክፍያ ለመፈፀም የመስሪያ ገንዘብ እጥረት ማነቆ መሆን፤

1.7.5. በአሰሪ መ/ቤቶች በኩል የስራ ክፍያ በውቅቱ አለመልቀቅ፣የውጭ ምንዛሬ ተመን ማሻሻያን ተከትሎ በየጊዜው ለሚከሰት ግሽበት የዋጋ ማስተካከያ አለማድረግ፤

1.7.6. ለኢንዶዉመንቱ ራዕይና ተልዕኮ መሳካት በአመራሩና በሰራተኛዉ ዘንድ ተነሳሽነት ያለ ቢሆንም ፕሮጀክቶችን ከመምራት አኳያ የአመለካከት፣ የክህሎትና የእውቀት ውስንነት ያለ መሆኑ፤

1.7.7. የብልሹ አሰር ዝንባሌና ተግባር የኢንዶዉመንቱ ፈተና ሆኖ መገኘቱ፤

1.7.8. ለተቋማት የግብ ስኬት አጋዥ የሆነ ከዘመኑ ጋር ሊሄድ የሚችል የቴክኖሎጅ አጠቃቀም ከመገንባት አኳያ ውስንነት ያለ መሆኑ፤

1.7.9. በክልሉ ውስጥ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን የሚሹና ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች መኖራቸዉ፤

## 1.8. ተልዕኮ፣ ራዕይና እሴቶች

### ተልዕኮ

- መንግስት ትኩረት በሰጠባቸውና የገበያ ክፍተት በሚታይባቸው የልማት ዘርፎች ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት፣ ተወዳዳሪና ትርፋማ ኩባንያዎችን በመፍጠር፣ ከለጋሽ አካላት ሃብት በማሰባሰብ ስትራቴጅክ በሆኑ ዘርፎች መልሶ ኢንቨስት በማድረግ እና የስራ እድል በመፍጠር የዕውቀትና የቴክኖሎጅ ሽግግር በማምጣት እንዲሁም በማህበራዊ ልማት ስራዎች በመሳተፍ ለክልሉ ህዝብ የኑሮ ደረጃ መሻሻል እገዛ ማድረግ፤

### ራዕይ

- በ2035 በክልሉ እድገት ትርጉም ያላቸው የኢንቨስትመንትና የማህበራዊ ልማት ስራዎችን በማስፋፋት በሀገር ደረጃ ግንባር ቀደም የልማት አጋር ሆኖ ማየት፡፡

### እሴቶች

- ትጋት!
- ታማኝነት
- አርዓያነት!
- ዘለቄታዊነት!
- በለዉጥ እናምናለን!
- ውጤታማነት
- ቅልጥፍና
- ግልጽነትና ተጠያቂነት!
- ከባቢያዊ ደህንነት!
- ሕዝባዊ ወገንተኝነት!

# ክፍል ሁለት፡- የትኩረት መስኮችና ስትራቴጅያዊ ዕይታዎች

## 2.1. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ፡

ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ የኢንዶዉመንቱን ተልዕኮዎች በመፈጸም ራዕይ እውን ከማድረግ አኳያ ውጤት የሚያስገኝና የተቋሙን ሙሉ የስራ ትኩረት ሊያገኝ የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የትኩረት መስኮቹን ከአገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች እንዲሁም መሪ የልማት እቅድ ጋር በማጣጣም፤ የኢንዶዉመንቱን ያለፈ የስትራቴጅክ እቅድ የስራ እንቅስቃሴ በመገምገምና ከተለዩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች በመነሳት የደንበኞች፣ ባለድርሻ እና አጋር አካላትን ሁኔታ በመተንተን በአጠቃላይ ከውስጣዊና ዉጫዊ ዳሰሳና ትንተና ተጨምቀዉ የመጡ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የስትራቴጅክ ዘመኑ የኢንዶዉመንቱ የትኩረት መስኮች ከዚህ እንደሚከተለው ተለይተው ቀርበዋል፡፡

**ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስኮችና ዉጤት፡-**

| ተ.ቁ | ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ | ስትራቴጅያዊ ውጤት |
|---|---|---|
| 1 | ተቋማዊ ልህቀት | ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነት |
| 2 | ኢንቨስትመንት ተኮር ሀብት ፈጠራ | ጠንካራ ክልላዊ የኢንቨስትመንት አቅም |
| 3 | የዳበረ ማህበራዊ ልማት | ያደገ የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት |

## 2.2. የስትራቴጅያዊ የትኩረት መስኮች መግለጫ

### 2.2.1. ተቋማዊ ልህቀት፡-

የዚህ ትኩረት መስክ ዉጤት ኢንዶዉመንቱና የገቢ ማስገኛ ተቋማትን በዓለምአቀፍ ደረጃ ብቁና ተወዳዳሪ ማድረግ ነዉ፡፡ ይህን ለማሳካት የተቋማቱን የሰው ኃብት በአመለካከት፣ በዕውቀት እና በክህሎት በመገንባት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ከወቅቱና ከሁኔታዎች ጋር የተናበበና ሊያሰራ የሚችል ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር፤ የተሟላ የስራ መሳሪያና ግብዓት በማሟላት፣ የምርምር፣ስልጠና እና ልማት በማካሄድ፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን እና ስነ-ምግባርን በመገንባት፣ ቴክኖሎጅ እና ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም በአግባቡ በመምረጥና ስራ ላይ በማዋል ተወዳዳሪ ተቋማትን መፍጠር የሚያስችል አቅም መገንባትን ያካተተ ነዉ፡፡

### 2.2.2. ኢንቨስትመንት ተኮር ሀብት ፈጠራ፡-

በዚህ የትኩረት መስክ መንግስት ትኩረት ባደረገባቸው የልማት ዘርፎች በተለይም የአምራች ኢንዱስትሪዎች፤ በግብርና እና አገልግሎት ዘርፍ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋትን፤ በነባር ኩባንያዎች ላይ በጥናት ላይ ተመስርቶ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ማካሄድን፤ በክልሉ የቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲመጣ እና የስራ ዕድል እንዲፈጠር በማድረግና ሃብት በመፍጠር ጠንካራ ክልላዊ የኢንቨስትመንት አቅም መገንባትን ትኩረት አድርጎ የተቀረፀ ነው፡፡

### 2.2.3. የዳበረ ማህበራዊ ልማት

የዚህ የትኩረት መስክ ዋናዉ ዉጤት በክልላችን የማህበራዊ ልማት ስራዎችን በማካሄድ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነዉ፡፡ ስለሆነም ከማህበራዊ ልማት አኳያ (በማህበራዊ መሰረተ ልማት) በመሰረተ ልማት  በተለይ በጤና፣ በትምህርትና በዉሃ ተቋማት ግንባታ በመሳተፍ፣ በስራ ዕድል ፈጠራ ላይ የተለያዩ ተግባራትን በማከናዎን፣ በምርት ሂደትም ሆነ የግንባታ ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ ተጽኖ እንዳያስከትሉ በማድረግ፣ በማህበረሰቡ ዉስጥ ልዩ ትኩርት የሚሹ አካላትን ተጠቃሚነት የሚየጎለብቱ ስራዎችን ማከናዎን ያጠቃልላል፡፡

## 2.3. የአፈጻጸም አመላካች ዕይታዎች (Perspectives)

የአፈፃፀም አመላካች ዕይታዎች የተቋሙን ዉጤት በተለያዩ ፈርጆች ለማየትና ለመለካት የሚያስችሉ ማሳያዎች (Lenses) ሲሆኑ ኢንዶዉመንቱ የሚያከናዉናቸዉን ተግባራት መሰረት በማድረግ እንደሚከተለዉ ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ | ተቋማዊ የዕይታ መስኮች | የተመረጡበት ዋና ዋና ምክንያት |
|---|---|---|
| 1 | ደንበኛ/ተገልጋይ | ኢንዶዉመንቱ አስተማማኝ የፋይናንስ አቅም በመፍጠር የክልሉን ልማት በማፋጠን የደንበኞቻችንና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በማጎልበት ተደራሽ መሆን አስፈላጊ በመሆኑ፤ |
| 2 | ፋይናንስ | ኢንዶዉመንቱ ተልዕኮዎቹን በመፈጸም ራዕዩን ለማሳካት ዘላቂነት ያለው ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ለማህበራዊ ልማት ስራዎች አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭ ሊኖረዉ ስለሚገባ፤ |
| 3 | የውስጥ አሰራር | የኢንዶዉመንቱን ተልዕኮ ለማሳካትና ራዕዩን እውን ለማድረግ የተቋማትን አሰራር ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ፣ ዉጤታማና ተወዳዳሪ ማድረግ ወሳኝ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም ብቁና ተወዳደሪ የሚያደርጉ የአሰራር ስርዓቶችን በመለየትና ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤ |
| 4 | መማማርና እድገት | በተቋማዊ ልህቀት ግንባታ ሂደት የሰው ኃብቱን በአመለካከት፣ በዕውቀት፣ በክህሎት መገንባት፣ ምርምርና ስልጠናና ልማት በማካሄድ፣ መልካም-አስተዳደርን በማስፈንና ስነ-ምግባርን በመገንባት፣ ቴክኖሎጅና ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም በአግባቡ በመምረጥና ስራ ላይ በማዋል ተወዳዳሪ ተቋማትን መፍጠር የሚያስችል አቅምን ለመገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፤ |

# ክፍል ሦስት፡- ስትራቴጅያዊ ግቦች

ስትራቴጅያዊ ግቦች የኢንዶውመንቱን የትኩረት መስኮች ውጤቶች ለማሳካት የተመረጡ እና የትኩረት መስክን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችሉ ሲሆኑ አፈፃፀማቸውም ሊለካ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም ስትራቴጅያዊ ግቦች ከእያንዳንዱ የትኩረት መስክ አንጻር ተቃኝተውና እይታዎችን መሰረት አድርገዉ ከነውጤታቸዉ በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡

## 3.1. ስትራቴጅያዊ ግቦች ከእይታዎች አንጻር

### 3.1.1. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ አንድ፡- ተቋማዊ ልህቀት፡-

**ስትራቴጅያዊ ውጤት፡- ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነት**

| ተ.ቁ | ዕይታዎች | ስትራቴጅያዊ ግቦች |
|---|---|---|
| 1 | ደንበኛ/ተገልጋይ | ➢ የደንበኞችን እርካታ ማሳደግ<br>➢ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ |
| 2 | ይፋይናንስ | ➢ ትርፍና ትርፋማነትን ማሳደግ<br>➢ ገቢን ማሳደግ<br>➢ የገቢ መሰረቶችን ማስፋት<br>➢ የሃብት ብክነትን መቀነስ |
| 3 | የውስጥ አሰራር | ➢ የተቋማትን የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ማሻሻል<br>➢ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል<br>➢ የምርምር ዉጤቶችን ስርጸት ማጎልበት<br>➢ ተቋማዊ ገጽታ ግንባታን ማሻሻል<br>➢ የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ |
| 4 | መማማርና ዕድገት | ➢ የፈፃሚውን ብቃት ማሳደግ<br>➢ የአመራር አቅም ማጎልበት<br>➢ የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሻሻል፤ |

## የትኩረት መስክ አንድ የግቦች መግለጫ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | የደንበኞችን እርካታ ማሳደግ | የኢንዶዉመንቱ ምርትና አገልግሎት የተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ጥራትና ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚስችል አሰራርን በመከተል ብቁና ተወዳዳሪ ተቋም በመፍጠር ከተወዳዳሪዎች ልቆ በመገኘት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል፣ | ያደገ ደንበኞች እርካታ |
| 2 | የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ | በስራ እድል ፈጠራ፣ በማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲሁም በሌሎች የልማት ዘርፎች ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፤ | ያደገ የዜጎች ተጠቃሚነት |
| 3 | ትርፍና ትርፋማነትን ማሳደግ | ምርታማነትን በማሳደግ እና አገልግሎትን በፍጥነትና በጥራት በማቅረብ፣ የወጪ ቅነሳ ስትራቴጅን በመከተል፣ የተሻሻሉ የአሰራር ስርዓቶችን በመተግበር ትርፍና ትርፋማነትን ማሳደግ፣ | ያደገ ትርፍ፣<br><br>ትርፋማነት ከአጠቃላይ ሃብት፣ ትርፋማነት ከካፒታል መዋጮ |
| 4 | ገቢን ማሳደግ | የምርት/አገልግሎት ሽያጭን በማሳደግ አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን በስፋት በማስተዋወቅና ወደ ገበያ በመግባት እንዲሁም የገበያ መዳረሻ ቦታዎችን በማስፋት ገቢን በማሳደግ፣ | ያደገ ገቢ |
| 5 | የገቢ መሰረቶችን ማስፋት | ምርትና አገልግሎትን በጥራትና በመጠን አሳድጎ በመሸጥ፣ የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት፣ አዳዲስ ኩባንያዎችን በማቋቋም፣ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በመተግበር፣ | ያደገ ተጨማሪ የስራ መስክና ፕሮጀክቶች |
| 6 | የሐብት ብክነትን መቀነስ | የግብዓት አጠቃቀምን በተቀመጡ ስታንዳርዶች በመፈፀም፣ ምርታማነት በማሳደግ፣ የወጭ ቅነሳ ስትራቴጅ በመቀየስና ተግባራዊ በማድረግ፣ የተጠናከረ የፋይናንስ፣ የግዥና ንብረት አያያዝና አጠቃቀም ስርዓትን በማሻሻል፣ ዉጤታማ የፕሮጀክት ፋይናንስ ስርዓት በመከተል፣ | የቀነሰ ወጪ እና ከብክነት የዳነ ሃብት |
| 7 | የተቋማትን የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ማሻሻል፤ | አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋትና በመተግበር፤ እንዲሁም በትግበራ ሂደት በመፈተሸ እና ቀጣይነት ባለው መንገድ በማሻሻል፣ የጉልበትና የግብዓት ስታንዳርድን በመተግበር፣ የምርት/አገልግሎት ጥራት ማሻሻያ አሰራሮችን በመተግበር፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሸና ተግባራዊ በማድረግ፣ ተስማሚ የለዉጥ መሳሪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ፤ በሶፍት ዌር፣ በመረጃ ቋት፣ በዌብሳይት ልማትን በመተግበር ብቁና ተወዳዳሪ ለማድረግ፣ እንዲሁም ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉትን አደረጃጀትና መዋቅር በመፈተሸና በመዘርጋት፤ | ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርዓቶችና አደረጃጀቶችን፤በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም እና በቴክኖሎጅ አጠቃቀም የዳበሩ ተቋማት፣ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 8 | የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል | የተገልጋዮችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድ በማዘጋጀት፣ የደንበኞችን የእርካታ ደረጃ በመዳሰስ እና ቀጣይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያዎችን ማድረግ፣ በየደረጃዉ የጋራ የምክክር መድረኮችን በመፍጠር የተገልጋዮችን ተሳትፎ እያረጋገጡ መሄድ፣ | በደንበኞች ዘንድ አመኔታን ያተረፈ ተቋም |
| 9 | የምርምር ዉጤቶችን ስርጸት ማጎልበት | ከምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጎልበት የምርት ሂደትን ለማሻሻል፣ የአገልግሎት ቅልጥፍናንና ጥራትን ለማረጋገጥ፣ አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን ለመፍጠር የሚያስችሉ የምርምርና ልማት ስራዎችን በማከናወን እና በማስረጽ የተቋማቱን ተወዳዳሪነትና ብቃት በማሳደግ፣ | በየተቋማቱ የሰረጹ ምርምር ዉጤቶች |
| 10 | ተቋማዊ ገጽታ ግንባታን ማሻሻል | ኢንዶመንቱንና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎችን ምርትና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅና ገጽታ ለመገንባት የሚያስችሉ የህትመት ዉጤቶች በማዘጋጀት፣ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀምና የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር የተቋማቱን መልካም ስም መገንባትን ያካትታል | ያደገ ተቋማዊ ገጽታ |
| 11 | የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ | በኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በሚሰሩ የጥናት፣ የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የጉድጓድ ቁፋሮ እንዲሁም የማማከርና የቁጥጥር ፕሮጀክቶችን የስራ ላይ ደህንነት ግብዓቶችን በማሟላት፣ በተያዘላቸው ጊዜና በጥራት የማጠናቀቅ ወቅቱን ጠብቆ ለደንበኞች የመጀመሪና የመጨረሻ ዙር ርክክብ በማድረግ፣ | ድህንነታቸዉ የተጠበቁ ሰራተኞች እና በጥራትና በጊዜዉ ተጠናቀዉ ርክክብ የተፈጸመላቸዉ ፕሮጀክቶች |
| 12 | የፈፃሚውን ብቃት ማሳደግ | የአጫጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የተለያዩ የመማማሪያ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የልምድና ተሞክሮ መለዋወጫ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት፣ የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱን በማጠናከር፣ ሰራተኞችን በውጤት በመለካትና በማበረታታት፣ የሰራተኞችን አመለካከት፣ ክህሎትና እውቀት በመገንባት ለጋራ ራዕይ፣ ተልዕኮና እሴቶች የሚረባረብ ፈጻሚ ኃይል መፍጠር ነው፡፡ | ያደገ የመፈጸም ብቃት |
| 13 | የአመራሩን አቅም ማጎልበት | አጫጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በማመቻቸት፣ የተለያዩ የመማማሪያ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የልምድና ተሞክሮ መለዋወጫ ፕሮግራሞችን በማመቻቸት፣ የክትትልና ድጋፍ ስርዓቱን በማጠናከር፣ የተኪ አመራሮችን ቁጥር በመጨመር፣ ምቹ የስራ አካባቢ በመፍጠር የማስፈፀም ብቃቱ ያደገ አመራር መገንባት፣ | ያደገ የማስፈፀም አቅም |
| 14 | የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሻሻል፤ | የአመራሩንና የሰራተኛዉን የቴክኖሎጅ አጠቃቀም አቅም በመገንባት፣ የተቋሙን የቴክኖሎጅ አጠቃቀም አቅም ማሳደግ | ስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጅዎች |

### 3.1.2. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ ሁለት፡- ኢንቨስትመንት ተኮር ሀብት ፈጠራ

**ስትራቴጅያዊ ውጤት፡- ጠንካራ ክልላዊ የኢንቨስትመንት አቅም**

| ተ.ቁ | ዕይታዎች | ስትራቴጅያዊ ግቦች |
|---|---|---|
| 1 | ደንበኛ/ተገልጋይ | • የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ<br>• የደንበኛ እርካታን ማሳደግ<br>• ደንበኞችን መሳብና ዘላቂነትን ማሻሻል |
| 2 | ፋይናንስ | • የካፒታል መጠንን ማሳደግ<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• የሃብት ብክነትን መቀነስ |
| 3 | የውስጥ አሰራር | • የኢንቨስትመንት ተሳትፎን ማሳደግ<br>• የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ማሻሻል<br>• ማህበራዊ ኃላፊነትን ማሳደግ<br>• ተቋማዊ ግንኙነትን ማሳደግ<br>• የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ |
| 4 | መማማርና ዕድገት | • የሰራተኛዉን የመፈጸም አቅም ማሳደግ<br>• የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት |

## የትኩረት መስክ ሁለት የግቦች መግለጫ

| ተ.ቁ | የስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ | አዳዲስ ኩባንያዎችን በማቋቋም፣ ነባሮችን በማስፋፋት ለዜጎች በቋሚ፣ በኮንትራትና በጊዜያዊነት የስራ ዕድል መፍጠር እንዲሁም ከአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ጋር አስተሳስሮ በመስራት ተጠቃሚ ማድረግ፣ | ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች |
| 2 | የደንበኛ እርካታን ማሳደግ | ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ምርት/አገልግሎት በሚፈለገዉ የጥራት ደረጃ፣ መጠን፣ ዋጋና ጊዜ በማቅረብ፣ የደንበኛን ቅሬታ በመቀበል በመፍታትና ምላሽ በመስጠት በአጠቃላይ ከተወዳዳሪዎቻችን ልቆ በመገኘት የደንበኞቻችን የእርካታ ደረጃ በማሳደግ፣ | ያደገ ደንበኞች እርካታ |
| 3 | ደንበኞችን መሳብና ዘላቂነትን ማሻሻል | አዳዲስ ምርት/አገልግሎቶችን በማስፋፋት፣ በማስተዋወቅ፣ በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ፣ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ልቆ በመገኘት አዳዲስ ደንበኞችን መሳብና ያሉትን ፍላጎታቸዉን በማሟላት በዘላቂነት በማስቀጠል፣ | በአዲስ የተያዙና በዘላቂነት የቀጠሉ ደንበኞች |
| 4 | የካፒታል መጠንን ማሳደግ | አዳዲስ ኩባንያዎችን በማቋቋም የሀብት መሰረትን በማስፋት፣ ከነባር ኩባንያዎች የሚገኝን ትርፍ መልሶ ለኢንቨስትመንት በማዋል፣ የባለአክስዮኖችን የድርሻ መጠን በማሳደግ፤ ኢንዶዉመንቱ በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጭ ባለሀብቶች ጋር በጋራ በመስራት የካፒታል ፍሰትን በመጨመር፣ የባንክ ብድር በማግኘትና ስራ ላይ በማዋል፣ የነባር ኩባንያዎችን የስራ ዘርፍ በማስፋትና አቅም በማሳደግ፣ | ያደገ የካፒታል አቅም |

| ተ.ቁ | የስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 5 | ገቢን ማሳደግ | የምርት/አገልግሎት ሽያጭን በማሳደግ አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን በስፋት በማስተዋወቅና ወደ ገበያ በመግባት እና የገበያ መዳረሻ ቦታዎችን በማስፋት ገቢን በማሳደግ፣ | ያደገ ገቢ |
| 6 | የሃብት ብክነትን መቀነስ | የምርትና አገልግሎት ጥራትን በማሳደግ፣ የግብዓት አጠቃቀምን በተቀመጡ ስታንዳርዶች ስራ ላይ በማዋል፣ የምርታማነት ደረጃን በማሳደግ፣ የወጭ ቅነሳ ስልት በመቀየስና በመተግበር፣ ዉጤታማ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት በመተግበር፣ የሐብትና ንብረት አያያዝና አጠቃቀምን በማሻሻል፣ የለዉጥ ስራዎችን በመዘርጋት፣ | ያደገ ምርታማነት፣<br>ያደገ ገቢ፣<br>የቀነሰ ወጪ፣<br>ያደገ ትርፍ፣ |
| 7 | የኢንቨስትመንት ተሳትፎን ማሳደግ | አዳዲስ ፕሮክቶችን በማጥናትና አዋጭ የሆኑትን ወደ ተግባር በማሻጋገር፣ ነባር ኩባንያዎችን በማስፋፋት በክልሉ የኢንቨስትመንት ድርሻ በማሳደግ፣ | ያደገ ክልላዊ የኢንቨስትመንት ተሳትፎ |
| 8 | የተቋማትን አሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ማሻሻል | ተቋማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የገበያ ልማት ስትራቴጅ፣ የቴክኖሎጅ መረጣ፣ ማላመድና ትግበራ፣ የፕሮጀክት ዉጤታማነት የሚያረጋግጡ ስታንዳርዶችና አሰራሮች፣ የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም(MIS)፣ የለዉጥ መሳሪያዎችን፣ ገቢያን ለማስፋፋት የሚያግዙ ሰርቲፊኬሽኖች እንዲሁም የክትትልና ድጋፍ የሚያሳልጡ የአሰራር ስርዓቶችን በመለየት፣ በመዘርጋትና በማሻሻል ተግባራዊ በማድረግ፣ ሊያሰሩና ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ አደረጃጀቶችን ስራ ላይ ማዋል፣ | የተዘረጉ፣<br>የተሻሻሉና<br>የተተገበሩ የአሰራር ስርዓቶችና<br>አደረጃጀቶች |
| 9 | ማህበራዊ ኃላፊነትን ማሳደግ | በፕሮጀክቶች ትግበራና በኩባንያዎች የስራ እንቅስቃሴ ሂደት ለአካባቢና ለአየር ንብረት ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የዉሃና ሌሎች ማህበራዊ ልማት ስራዎች ላይ አስዋፅኦ በማበርከት፣ | ያደገ የማህበራዊ ልማት ስራዎች ተሳትፎ |
| 10 | ተቋማዊ ግንኙነትን ማሳደግ | በክልሉ ውስጥ እንዲሁም ከክል ውጭ ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ አቅራቢዎች፣ አሰሪዎች፣ ፋይናንስ እና ሌሎች አምራች/አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችሉ ስትራቴጅዎችን ቀይሶ ተግባራዊ በማድረግ እንዲሁም በኩባንያዎች መካከል የእርስበርስ ግንኙነትን በማጠናከር ሊጋራ አላማ እንዲሰለፉ በማድረግ፣ በተቋም ውስጥ በስራ መሪዎችና በሰራተኞች መካከል ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በመዘርጋት የመልካም አስተዳደር ብሎም የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን በመስራት፣ | የጎለበተ ተቋማዊ ቅንጅት |
| 11 | የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ | በኮንስትራክሽን ኩባንያዎች የሚሰሩ የጥናት፣ የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የጉድጓድ ቁፋሮ እንዲሁም የማማከርና የቁጥጥር ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜና በጥራት በማጠናቀቅ ወቅቱን ጠብቆ ለደንበኞች የመጀመሪና የመጨረሻ ዙር ርክክብ በማድረግ፣ | በጥራትና በጊዜዉ ተጠናቀዉ ርክክብ የተፈጸመላቸዉ ፕሮጀክቶች |
| 12 | የሰራተኛዉን የመፈጸም አቅም | የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠዎችን በማመቻቸትና በመስጠት፣ የልምድ ልዉዉጥ በሀገር ዉስጥና በዉጭ ሀገር በማካሄድ፣ የእርስ | የማስፈጸምና የመፈጸም አቅሙ |

| ተ.ቁ | የስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| | ማሳደግ | በርስ መማማሪያ መደርኮችን በመፍጠር፣ የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን በማሳደግ የሰዉ ኃይሉን ብቁና ተወዳዳሪ በማድረግ፣ | ያደገ አመራርና ፈጻሚ |
| 13 | የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሻሻል | በአዳዲስም ሆነ በነባር ኢንቨስትመንቶች ወቅቱ የደረሰበትን ተስማሚ ቴክኖሎጅዎችን በመለየት፣ በመምረጥና ጥቅም ላይ በማዋል ለኢንቨስትመንት ማስፋፋት ተቋማዊ አቅም መፍጠር፤ | ስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጅዎች |
| 14 | ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት | ተቋማትን ውጤታማና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ አደረጃጀቶች፤ የተለያዩ የአሰራር ስልቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ተሞክሮና ልምድ በመቅሰምና ወደ ተቋማቱ በማላመድ የምርት/አገልሎት ጥራትን ማሻሻል እንዲሁም ቅልጥፍናና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፤ | የተተገበሩ ውጤታማ ተሞክሮዎች ብዛት |

### 3.1.3. ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ ሦስት፡- የዳበረ የማህበራዊ ልማት

### ስትራቴጅያዊ ውጤት፡- ያደገ የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት

| ተ.ቁ | ዕይታዎች | ስትራቴጅያዊ ግቦች |
|---|---|---|
| 1 | ደንበኛ/ተገልጋይ | • የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚዎችን ማሳደግ<br>• የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚዎችን እርካታ መጨመር |
| 2 | ፋይናንስ | • ለማህበራዊ ልማት የሚዉለዉን በጀት መጠን ማሳደግ |
| 3 | የውስጥ አሰራር | • የማህበራዊ ልማት ማስፈፀሚያ ስርዓትን ማሻሻል<br>• ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት<br>• የማህራዊ ልማት ስራዎችን አፈጻጸም ማሻሻል<br>• የማህበራዊ ልማት ክትትልና ድጋፍን ማሻሻል |
| 4 | መማማርና ዕድገት | • የማህበራዊ ልማት ስራዎች ማስፈፀም አቅምን ማሳደግ |

## የትኩረት መስክ ሦስት የግቦች መግለጫ

| ተ.ቁ | የስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚዎችን ማሳደግ | በስራ እድል ፈጠራ፤ በወጣቶች፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ላይ ያተኮሩ፤ ለትግበራ ቀላልና አመች የሆኑ፤ የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ፕሮጀክቶችን ቀርጸው ለሚያቀርቡ አካላት የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በማሳደግ፤ | ያደገ የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚ ዜጎች |
| 2 | የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚዎችን እርካታ መጨመር | የተጠቃሚዎችን ፍላጎትና ተሳትፎ ያረጋገጠ ውጤታማ የማህራዊ ልማት ስራዎችን በማከናወን እርካታቸዉን በማሳደግ፤ | ያደገ እርካታ |
| 3 | ለማህበራዊ ልማት የሚዉለዉን በጀት መጠን ማሳደግ | ከኢንቨስትመንት ከሚገኝ ትርፍ ለማህበራዊ ልማት የሚመደበውን የበጀት መጠን በማሳደግ፤ ሌሎች የገቢ ማስገኛ አማራጮችን በማስፋት፣ ለማህበራዊ ልማት ሊውል የሚችለውን የፋይናንስ አቅም ማሳደግ፤ | ያደገ የማህበራዊ ልማት በጀት መጠን |

| ተ.ቁ | የስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 4 | የማህበራዊ ልማት ማስፈፀሚያ ስርዓት ማሻሻል | ግልጽነት፣ ፍትሃዊነትና ተጠያቂነት እንዲሁም ውጤታማነትን የሚያረጋግጥ የማህበራዊ ልማት ስራዎችን ማስፈፀም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፤ | የተዘረጋ የማህበራዊ ልማት ማስፈጸሚያ አሰራር ስርዓት |
| 5 | ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት | የማህበራዊ ልማት ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀምና ለማስፈፀም እንዲሁም የፋይናንስ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ አጋር አካላትን በመለየት በትብብርና በቅንጅት ለመስራት የሚያስችሉ አሰራሮችን መዘርጋትና በመተግበር | የተፈጠረ ቅንጅታዊ አሰራር |
| 6 | የማህበራዊ ልማት ስራዎችን አፈጻጸም ማሻሻል | በተለያዩ የማህበራዊ ልማት ስራዎች ማለትም በትምህርት፤ በጤና፤ በውሃ ተቋማት ግንባታ እና ስራ እድል ፈጠራ ...ወዘተ በስፋት አቅዶ ለመስራትና አፈጻጸማቸውን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሻሻል፤ | ያደገ የማህበራዊ ልማት አፈጻጸም |
| 7 | የማህበራዊ ልማት ክትትልና ድጋፍን ማጠናከር፤ | የማህበራዊ ልማት ስራዎችን አፈጻጸም ውጤታማ ለማድረግ አሳታፊ፣ ቀጣይነት ያለው፣ ችግር ፈች የክትትል ድጋፍና ግምገማ ስርዓትን በማጠናከር፤ | የተጠናከረ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት |
| 8 | የማህበራዊ ልማት ስራዎች የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ | ከፕሮጀክት ልየታ ጀምሮ እስከ ውጤት ግምገማ እና ተሞክሮ መቀመርና ማስፋት ድረስ ያሉትን ሂደቶች መፈጸም የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም በመገንባት፤ | ያደገ የማስፈጸም ብቃት |

# ክፍል አራት፡- ስትራቴጅያዊ ማፕ

## 4.1. ስትራቴጅያዊ ማፕ ከየትኩረት መስክ አንፃር

ስትራቴጅያዊ ማኘ በተለያዩ ዕይታዎች ስር የሚቀረጹ ስትራቴጅያዊ ግቦች በምክንያትና ውጤት ተሳስረው እንዴት ተጨማሪ እሴት በመፍጠር ስትራቴጅያዊ ውጤትን እንደሚያሳኩ የምንመለከትበት ምስል ነው፡፡ ይህ ማኘ የግቦች ተመጋጋቢነት የሚታይበትና ስትራቴጅው በአጭሩ የሚተረክበት ስዕላዊ መግለጫ ሲሆን፣ ስትራቴጅውን በትክክል ለመግለፅና ለማስገንዘብ ብሎም ሁሉም ፈፃሚዎች የራሳቸው እንዲያደርጉት የሚያግዝ መሣሪያ ነው፡፡

በመሆኑም እንደ ኢንዶውመንት ለተቀመጡ የትኩረት መስኮች ለእያንዳንዳቸው ስትራቴጅያዊ ማኘ የተዘጋጀ ሲሆን በመቀጠልም ለሦስቱ የትኩረት መስኮች የተዘጋጁ ስትራቴጅያዊ ግቦችን በማዋሃድና በማዋዋዋ የተጠቃለለ ስትራቴጅያዊ ማኘ ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡


ዕይታዎች
ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ አንድ፡- ተቋማዊ ልህቀት
ስትራቴጅያዊ ውጤት፡- ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነት
ደንበኛ
የደንበኞችን እርካታን ማሳደግ
የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ
ፋይናንስ
ትርፍና ትርፋማነትን ማሳደግ
ገቢን ማሳደግ
የሐብት ብክነትን መቀመቀነስ
የገቢ መሰረቶችን ማስፋት
የውስጥ አሰራር
የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ
የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል
የተቋማትን አሰራር ስርዓትና አደረጃጀት ማሻሻል
ተቋማዊ ገፅታ ግንባታን ማሻሻል
የምርምር ዉጤቶችን ስርጸት ማጎልበት
መማማር እና እድገት
የፈፃሚውን ብቃት ማሳደግ
የአመራር አቅም ማጎልበት
የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሻሻል


ዕይታዎች
ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ ሁለት፡- ኢንቨስትመንት ተኮር ሀብት ፈጠራ
ስትራቴጅያዊ ውጤት፡- ጠንካራ ክልላዊ የኢንቨስትመንት አቅም
ደንበኛ
የደንበኞችን እርካታን ማሳደግ
ደንበኞችን መሳብና ዘላቂነትን ማሻሻል
የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ
ፋይናንስ
የካፒታል መጠንን ማሳደግ
ገቢን ማሳደግ
የሃብት ብክነትን መቀነስ
የውስጥ አሰራር
የኢንቨስትመንት ተሳትፎን ማሳደግ
ማኀበራዊ ኃላፊነትን ማጎልበት
የአሰራርስርዓትና አደረጃጀት ማሻሻል
ተቋማዊ ግንኙነትን ማሳደግ
የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ
መማማር እና እድገት
የፈፃሚዎችን ብቃት ማሳደግ
ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት
የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሻሻል


ዕይታዎች
ስትራቴጅያዊ የትኩረት መስክ ሦስት፡- የተጠናከረ የማህበራዊ ልማት ስራዎች
ስትራቴጅያዊ ውጤት፡- ያደገ የህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት
ደንበኛ
የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚዎችን እርካታ
የማህበራዊ ልማት ተጠቃሚዎችን ማሳደግ
ፋይናንስ
ለማህበራዊ ልማት የሚዉለዉን በጀት መጠን ማሳደግ
የውስጥ አሰራር
ቅንጅታዊ አሰራርን ማጎልበት
የማህራዊ ልማት ስራዎችን አፈጻጸም ማሻሻል
የማህበራዊ ልማት ማስፈፀሚያ ስርዓትን ማሻሻል
የማህበራዊ ልማት ክትትልና ድጋፍን ማሻሻል
መማማር እና እድገት
የማህበራዊ ልማት ስራዎች ማስፈፀም አቅምን ማሳደግ

## 4.2. የተጠቃለሉ ስትራቴጅያዊ ግቦች፤ የግብ መግለጫና ማፕ

እንደ ኢንዶውመንት ለተቀመጡ የትኩረት መስኮች ለእያንዳንዳቸው ስትራቴጅያዊ ግብና ማፕ የተዘጋጀ ሲሆን በመቀጠልም ለሦስቱ የትኩረት መስኮች የተዘጋጁ ስትራቴጅያዊ ግቦችን ተመሳሳዮችን በማዋሃድ ተቀራራቢዎችን ደግሞ በማዋዋጥ የተጠቃለለ ስትራቴጂያዊ ግቦችና መግለጫ እንዲሁም ማፕ ተዘጋጅቷል፡፡

### 4.2.1. የተጠቃለሉ ስትራቴጂያዊ ግቦች

| ተ.ቁ | ዕይታዎች | ስትራቴጅያዊ ግቦች |
|---|---|---|
| 1 | ደንበኛ/ተገልጋይ | 1. የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ<br>2. የደንበኛ እርካታን ማሳደግ<br>3. ደንበኞችን መሳብና ዘላቂነትን ማሻሻል |
| 2 | ፋይናንስ | 4. የካፒታል መጠንን ማሳደግ<br>5. ትርፍና ትርፋማነት ማሳደግ<br>6. ገቢን ማሳደግ<br>7. የገቢ መሰረቶችን ማስፋት<br>8. ለማህበራዊ ልማት የሚውለውን የበጀት መጠን ማሻሻል<br>9. የሃብት ብክነትን መቀነስ |
| 3 | የውስጥ አሰራር | 10. የኢንቨስትመንት ተሳትፎን ማሳደግ<br>11. የአሰራር ስርዓትና አደረጃጀትን ማሻሻል<br>12. የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል<br>13. የማህበራዊ ልማት ስራዎችን አፈፃፀም ማሻሻል<br>14. ተቋማዊ ግንኙነትን ማሳደግ<br>15. የምርምር ዉጤቶችን ስርጸት ማጎልበት<br>16. ተቋማዊ ገጽታ ግንባታን ማሻሻል<br>17. የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ |
| 4 | መማማርና ዕድገት | 18. የፈፃሚውን አቅም ማሳደግ<br>19. የአመራሩን ብቃት ማሳደግ<br>20. የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሳደግ<br>21. ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት |

### 4.2.2. የተጠቃለሉ ስትራቴጅያዊ ግቦች መግለጫ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | የዜጎችን ተጠቃሚነት ማሳደግ | አዳዲስ ኩባንያዎችን በማቋቋም፣ ነባሮችን በማስፋፋት ለዜጎች ለተወሰነ እና ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ዕድል መፍጠር እንዲሁም ከአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ጋር አስተሳስሮ ስራ በመስጠት፣ በማህበራዊ ተቋማት ግንባታና፤ በወጣት የስራ እድል ፈጠራ ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ልዩ ትኩረት ለሚሹ የህ/ሰብ ክፍል ድጋፍ በማድረግ ተጠቃሚ ማድረግ፣ | በኢንዶውመንቱ ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎች |
| 2 | የደንበኛ እርካታን ማሳደግ | ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ምርት/አገልግሎት በሚፈለገዉ የጥራት ደረጃ፣ መጠን፣ ዋጋና ጊዜ በማቅረብ፣ የደንበኛን ቅሬታ በመቀበል በመፍታትና ምላሽ በመስጠት በአጠቃላይ ከተወዳዳሪዎቻችን ልቆ በመገኘት የደንበኞቻችን የእርካታ ደረጃ በማሳደግ፣ እንዲሁም በማህበራዊ ተቋማት ግንባታና በወጣት ስራ እድል ፈጠራና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን ተጠቃሚ በማድረግ የህብረተሰቡን የእርካታ ደረጃ በማሳደግ፣ | የረኩ ደንበኞች |
| 3 | ደንበኞችን መሳብና ዘላቂነትን ማሻሻል | አዳዲስ ምርት/አገልግሎቶችን በመስፋፋት፣ በማስተዋወቅ፣ በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ፣ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ልቆ በመገኘት አዳዲስ ደንበኞችን መሳብና ያሉትንም ፍላጎታቸዉን በማሟላት በዘላቂነት በማስቀጠል፣ | በአዲስ የተያዙና በዘላቂነት የቀጠሉ ደንበኞች |
| 4 | የካፒታል መጠንን ማሳደግ | አዳዲስ ኩባንያዎችን በማቋቋም የሀብት መሰረትን በማስፋት፣ ከነባር ኩባንያዎች የሚገኝን ትርፍ መልሶ ለኢንቨስትመንት በማዋል፣ የባለአክስዮኖችን የድርሻ መጠን በማሳደግ፣ ኢንዶዉመንቱ በበሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጭ ባለሀብቶች ጋር በጋራ በመስራት የካፒታል ፍሰትን በመጨመር፣ የነባር ኩባንያዎችን የስራ ዘርፍ በማስፋትና አቅም በማሳደግ፣ | ያደገ የካፒታል አቅም |
| 5 | ትርፍና ትርፋማነትን ማሳደግ | ምርታማነትን በማሳደግ እና አገልግሎትን በፍጥነትና በጥራት በማቅረብ፣ የወጪ ቅነሳ ስትራቴጅን በመከተል፣ የተሻሻሉ የአሰራር ስርዓቶችን በመተግበር ትርፍና ትርፋማነትን ማሳደግ፣ | ያደገ ትርፍ፣ ትርፋማነት ከአጠቃላይ ሃብት፣ ትርፋማነት ከካፒታል መዋጮ |
| 6 | ገቢን ማሳደግ | የምርት/አገልግሎት ሽያጭን በማሳደግ አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን በስፋት በማስተዋወቅና ወደ ገበያ በመግባት፣ የገበያ መዳረሻ ቦታዎችን በማስፋት እንዲሁም ከለጋሽ አካላት ሃብት በማሰባሰብ ገቢን በማሳደግ፣ | ያደገ ገቢ |
| 7 | የገቢ መሰረቶችን ማስፋት | አዳዲስ ኩባንያዎችን በማቋቋም፣ በነባር ኩባንያዎች ደግሞ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን በመተግበር፣ ምርትና አገልግሎትን በጥራትና በመጠን አሳድጎ በመሸጥ፣ የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት፣ | ያደገ ተጨማሪ የስራ መስክ፤ ያደገ ገበያ መዳረሻ እና ፕሮጀክቶች |
| 8 | ለማህበራዊ ልማት የሚዉለዉን በጀት መጠን ማሳደግ | ከኢንቨስትመንት ከሚገኝ ትርፍ ክፍፍል ለማህበራዊ ልማት የሚመደበውን የበጀት መጠን በማሳደግ፤ ሌሎች የገቢ ማስገኛ አማራጮችን በማስፋት፣ ለማህበራዊ ልማት ሊውል የሚችለውን የፋይናንስ አቅም ማሳደግ፤ | ያደገ የማህበራዊ ልማት በጀት መጠን |
| 9 | የሃብት ብክነትን መቀነስ | የምርትና አገልግሎት ጥራትን በማሳደግ፣ የግብዓት አጠቃቀምን በተቀመጡ ስታንዳርዶች መሰረት ስራ ላይ በማዋል፣ ምርታማነትን በማሳደግ፣ የወጭ ቅነሳ ስልት በመቀየስና በመተግባር፣ ዉጤታማ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት በመከተል፣ የሐብትና ንብረት አያያዝና አጠቃቀምን በማሻሻል፣ የለዉጥ ስራዎችን በመዘርጋትና በመተግበር፣ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች በመጠቀም፡፡ | የቀነሰ ወጪ፣ ከብክነት የዳነ ሃብት |
| 10 | የኢንቨስትመንት ተሳትፎን ማሳደግ | አዳዲስ ፕሮክቶችን በማጥናትና አዋጭ የሆኑትን ወደ ተግባር በማሸጋገር፣ ነባር ኩባንያዎችን በማስፋፋት፣ የአክሲዮን ግዥ ላይ በመሳተፍ በክልሉ ውስጥ የኢንቨስትመንት ድርሻ ማሳደግን ያካትታል፣ | ያደገ ክልላዊ የኢንቨስትመንት ተሳትፎ |
| 11 | አሰራር ስርዓትና አደረጃጀት | ሊያሰሩና ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ አደረጃጀቶችን ስራ ላይ ማዋል እና በሂደትም እየፈተሹ በማሻሻል፣ ተቋማትን ውጤታማ የሚያደርጉ የገበያ ልማት ስትራቴጅዎችን፣ የቴክኖሎጅ መረጣ፣ ማላመድና ትግበራ፣ የፕሮጀክት ዉጤታማነት የሚያረጋግጡ | የተዘረጉና የተሻሻሉ አደረጃጀቶች፣ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግብ | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|---|
| | ማሻሻል | ስታንዳርዶችና አሰራሮች፣ የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም(MIS)፣ የለዉጥ መሳሪያዎችን፣ የገቢ.ያ መዳረሻዎችን ለማስፋፋት የሚያግዙ ሰርቲፊኬሽኖች እንዲሁም የክትትልና ድጋፍ የሚያሳልጡ የአሰራር ስርዓቶችን በመለየት፣ በመዘርጋትና በማሻሻል ተግባራዊ በማድረግ፣ | አሰራሮች እንዲሁም የቴክኖሎጅና ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም |
| 12 | የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል | የተገልጋዮችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድ በማዘጋጀት፣ የደንበኞችን የእርካታ ደረጃ በመዳሰስ እና ቀጣይነት ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያዎችን በማድረግ፣ በየደረጃዉ የጋራ የምክክር መድረኮችን በመፍጠር የተገልጋዮችን ተሳትፎ እያረጋገጡ በመሄድ፣ | በደንበኞች ዘንድ አመኔታን ያተረፈ ተቋም |
| 13 | የማህበራዊ ልማት ስራዎችን አፈፃፀም ማሻሻል | የትምህርት፣ የጤና፣ የዉሃና ሌሎች ማህበራዊ ስራዎች ላይ በመሳተፍና አስተዋፅኦ በማድረግ የወጣት የስራ እድል ፈጠራ በመስራት፣ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች ድጋፍ በማድረግ፤ በፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደትና በኩባንያዎች የስራ እንቅስቃሴ ሂደት ለአካባቢና ለአየር ንብረት ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት፣ | ያደገ የማህበራዊ ልማት አፈጻጸም |
| 14 | ተቋማዊ ግንኙነትን ማሳደግ | በክልሉ ውስጥና ውጭ ከሚገኙ የልማት ድርጅቶች፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፤ አቅራቢዎች፤ አሰሪዎች፤ ፋይናንስ እና ሌሎች አምራች/አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችሉ ስትራቴጅዎችን ቀይሶ ተግባራዊ በማድረግ፤ እንዲሁም በኩባንያዎች መካከል የእርስበርስ ግንኙነትን በማጠናከር ለጋራ አላማ እንዲሰለፉ በማድረግ፤ በተቋም ውስጥ በስራ መሪዎችና በሰራተኞች መካከል ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር በመዘርጋት የመልካም አስተዳደር ብሎም የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን በመስራት፤ | የጎለበተ ተቋማዊ ቅንጅት |
| 15 | የምርምር ዉጤቶችን ስርጸት ማጎልበት | ከምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጎልበት የምርት ሂደትን ለማሻሻል፣ የአገልግሎት ቅልጥፍናንና ጥራትን ለማረጋገጥ፣ አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን ለመፍጠር የሚያስችሉ የምርምርና ልማት ስራዎችን በማስረጽ የተቋማቱን የተወዳዳሪነት ብቃት ለማሳደግ፣ | በየተቋማቱ የሰረጹ የምርምር ዉጤቶች |
| 16 | ተቋማዊ ገጽታ ግንባታን ማሻሻል | ኢንዶመንቱንና የገቢ ማስገኛ ኩባንያዎችን ምርትና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅና ገጽታ ለመገንባት የሚያስችሉ የህትመት ዉጤቶች በማዘጋጀት፣ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀምና የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር የተቋማቱን መልካም ስም መገንባትን ያካትታል | ያደገ ተቋማዊ ገጽታ |
| 17 | የስራ ቅልጥፍናና ጥራትን ማሳደግ | በኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በሚሰሩ የጥናት፣ የዲዛይን፣ የግንባታ፣ የጉድጓድ ቁፋሮ እንዲሁም የማማከርና የቁጥጥር ፕሮጀክቶችን የስራ ላይ ደህንነት ግብዓቶችን በማሟላት፣ በተያዘላቸው ጊዜና በጥራት የማጠናቀቅ ወቅቱን ጠብቆ ለደንበኞች የመጀመሪና የመጨረሻ ዙር ርክክብ በማድረግ፣ | ድህንነታቸዉ የተጠበቁ ሰራተኞች፣ በጥራትና በጊዜ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች |
| 18 | የፈፃሚውን አቅም ማሳደግ | ለፈፃሚ ሰራተኞች የአጭርና የረጅ ጊዜ ስልጠዎችን በማመቻቸትና በመስጠት፣ የልምድ ልዉዉጥ በሀገር ዉስጥና በዉጭ ሀገር በመፍጠር፣ የእርስ በርስ መማማሪያ መደርኮችን በመፍጠር፣ የቴቴክኖሎጅ አጠቃቀምን በማሳደግ የሰዉ ኃይሉን ብቁና ተወዳዳሪ በማድረግ፣ | አፈፃፀማቸው የተሻሻሉ ፈጻሚዎች |
| 19 | የአመራሩን የማስፈጸም አቅም ማሳደግ | የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በማመቻቸትና በስጠት፣ የልምድ ልዉዉጥ በሀገር ዉስጥና በዉጭ ሀገር በማካሄድ፣ የእርስ በርስ መማማሪያ መድረኮችን በመፍጠር፣ የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን በማሳደግ የሰዉ ኃይሉን ብቁና ተወዳዳሪ በማድረግ፣ | የማስፈጸም አቅሙ ያደገ አመራር |
| 20 | የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን ማሳደግ | በአዳዲስም ሆነ በነባር ኢንቨስትመንቶች ወቅቱ የደረሰበትን ተስማሚ ቴክኖሎጅዎችን በመለየት፣ በመምረጥና ጥቅም ላይ በማዋል ለኢንቨስትመንት ማስፋፋት ተቋማዊ አቅም በመፍጠር፤ | ስራ ላይ የዋሉ ቴክኖሎጅዎች |
